# የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

ሲል፥ “የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ
የሚወለደው[፩] በመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን
ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ፳፩ልጅም ትወ
ልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድ
ናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።” ፳፪ይህም
ሁሉ የሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ በነቢይ የተ
ነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው፤ እንዲህ ሲል፦
፳፫“እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፤ ልጅም ትወ
ልዳለች፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል፤ ትር
ጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት
ነው።” ፳፬ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የእግዚ
አብሔር መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፤ እጮኛ
ውን ማርያምንም ወሰዳት። ፳፭የበኵር ልጅዋ
ንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙ
ንም ኢየሱስ አለው።

## ምዕራፍ ፪

### ስለ ሰብአ ሰገል መምጣት

፩በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በይሁዳ ክፍል
በቤተ ልሔም ጌታችን ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ፥
እነሆ፥ ሰብአ ሰገል ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም
መጡ። ፪እንዲህ ሲሉ፥ “ኮከቡን በምሥራቅ
አይተን እንሰግድለት ዘንድ መጥተናልና፥ የተወ
ለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?” ፫ንጉሥ
ሄሮድስም በሰማ ጊዜ ደነገጠ፤ ኢየሩሳሌምም
በመላዋ ከእርሱ ጋር ደነገጠች። ፬የካህናት አለ
ቆችንና የሕዝቡን ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ “ክር
ስቶስ በየት ይወለዳል?” ብሎ ጠየቃቸው።
፭እንዲህም አሉት፤ “በይሁዳ ክፍል በቤተ
ልሔም ነው፤ በነቢይ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአ
ልና። ፮የይሁዳ ምድር[፪] አንቺ ቤተ ልሔም ከይ
ሁዳ አለቆች[፫] ከቶ አታንሺም፤ ሕዝቤን እስራ
ኤልን የሚጠብቅ ንጉሥ ከአንቺ ይወጣልና።”
፯ከዚህም በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን በስውር
ጠራቸው፤ ኮከቡ የታየበትንም ዘመን ከእነርሱ
ተረዳ። ፰“ሂዳችሁ የዚያን ሕፃን ነገር ርግ
ጡን መርምሩ፤ ያገኛችሁትም እንደ ሆነ እኔም
መጥቼ እሰግድለት ዘንድ በእኔ በኩል ተመል
ሳችሁ ንገሩኝ” ብሎ ወደ ቤተ ልሔም ሰደ
ዳቸው። ፱እነርሱም ከንጉሡ ሰምተው ሄዱ፤
እነሆ፥ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ በአለበት
ቦታ ላይ ደርሶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው
ነበር። ፲ኮከቡንም አይተው ታላቅ ደስታ ደስ
አላቸው። ፲፩ወደ ቤትም በገቡ ጊዜ ሕፃኑን
ከእናቱ ከማርያም ጋር አገኙት፤ ወድቀውም
ሰገዱለት፤ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው ወርቅና
ዕጣን፥ ከርቤም፥ እጅ መንሻ አቀረቡለት።
፲፪ወደ ሄሮድስም እንዳይመለሱ በሕልም ነገራ
ቸው፤ በሌላ መንገድም ወደ ሀገራቸው ሄዱ።

### ሕፃኑ ወደ ግብፅ ምድር ስለ መግባቱ

፲፫እነርሱም ከሄዱ በኋላ እነሆ፥ የእግዚአብ
ሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ፥ “ሄሮ
ድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይሻዋልና ተነሣ፤ ሕፃ
ኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ምድረ ግብፅ ሽሽ፤
እስክነግርህም ድረስ በዚያ ኑር” አለው፤
፲፬እርሱም በሌሊት ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን
ይዞ ወደ ግብፅ ሄደ። ፲፭ከእግዚአብሔር ዘንድ
“ልጄን ከግብፅ ጠራሁት” ተብሎ በነቢይ የተ
ነገረው ይፈጸም ዘንድ፤ ሄሮድስም እስኪሞት
ድረስ በዚያ ኖረ።

### ስለ ሕፃናት መገደል

፲፮ከዚህም በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገል እንደ
ተዘባበቱበት ባየ ጊዜ እጅግ ተቈጣና ጭፍራ
ዎቹን ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን
ልክ ሁለት ዓመት የሆናቸውን፥ ከዚያም የሚ
ያንሱትን፥ በቤተ ልሔምና በአውራጃዎችዋ
ሁሉ የነበሩትን ሕፃናት አስገደለ። ፲፯ያን ጊዜ፥
በነቢዩ በኤርምያስ የተነገረው ተፈጸመ፤ እንዲህ
ሲል፦ ፲፰“ራሔል ስለ ልጆችዋ ስታለቅስ ብዙ
ልቅሶና ዋይታ በራማ ተሰማ፤ መጽናናትንም
እንቢ አለች፤ ልጆችዋ የሉምና።”
፲፱ሄሮድስም በሞተ ጊዜ እነሆ፥ የእግዚአ
ብሔር መልአክ በግብፅ ሀገር ለዮሴፍ በሕ
ልም ታየው። ፳እንዲህ ሲል፥ “የሕፃኑን ነፍስ
የሚሹ ሙተዋልና፥ ተነሥተህ ሕፃኑንና እናቱን
ይዘህ ወደ እስራኤል ሀገር ሂድ።” ፳፩እርሱም
ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ እስራኤል

---

[፩] ግሪኩ “የተፀነሰው” ይላል።

[፪] አንዳንድ ዘርዕ “የኤፍራታ ምድር” ይላል።

[፫] አንዳንድ ዘርዕ “ነገሥታት” ይላል።

፩፡፳፩ ሉቃ ፩፡፴፩። ፩፡፳፫ ኢሳ ፯፡፲፬። ፩፡፳፭ ሉቃ. ፪፡፳፩።
፪፡፪ ኤር. ፳፫፡፭፤ ዘካ. ፱፡፱፤ ዘኍ. ፳፬፡፲፯። ፪፡፮ ሚክ. ፭፡፪። ፪፡፲፭ ሆሴዕ ፲፩፡፩።
፪፡፲፰ ኤር. ፴፩፡፲፭።

ምድር ገባ። ፳፪አርኬላኦስም በአባቱ በሄሮድስ
ፋንታ በይሁዳ እንደ ነገሠ በሰማ ጊዜ፥ ወደዚያ
ለመሄድ ፈራ፤ በሕልምም ተገልጦለት ወደ
ገሊላ አውራጃ ሄደ። ፳፫በነቢያት "ልጁ ናዝራዊ
ይባላል" የተባለው ይፈጸም ዘንድ ናዝሬት ወደ
ምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ።

## ምዕራፍ ፫

### ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ስብከት
(ማር. ፩፥፩-፰፤ ሉቃ. ፫፥፩-፲፰)

፩በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይሁዳ
ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ። ፪እንዲህ ሲል፥
"መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ።
፫የእግዚአብሔርን መንገድ አዘጋጁ፤ ጥርጊያው
ንም አስተካክሉ እያለ በምድረ በዳ የሚያስተ
ምር የዐዋጅ ነጋሪ ቃል" ተብሎ በነቢዩ በኢ
ሳይያስ የተነገረለት ይህ ነውና። ፬የዮሐንስም
ልብሱ የግመል ጠጕር ነበር፤ በወገቡም የጠ
ፍር መታጠቂያ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና የጣ
ዝማ ማር ነበር። ፭ያን ጊዜ በይሁዳና በኢየሩ
ሳሌም፥ በዮርዳኖስም አውራጃዎች ያሉ ሰዎች
ሁሉ ወደ እርሱ ይሄዱ ነበር። ፮ኀጢአታቸው
ንም እየተናዘዙ ሁሉም በዮርዳኖስ ወንዝ ከእ
ርሱ ይጠመቁ ነበር።
፯ነገር ግን፥ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን
ወገን ወደ ጥምቀቱ ሲመጡ ብዙ ሰዎችን
ባየ ጊዜ እንዲህ አላቸው፥ "እናንተ የእፉኝት
ልጆች፥ ከሚመጣው ቍጣ ትሸሹ ዘንድ ማን
አመለከታችሁ? ፰እንግዲህስ ለንስሓ የሚያበቃ
ችሁን በጎ ሥራ ሥሩ። ፱አብርሃም አባት አለን
በማለት የምታመልጡ አይምሰላችሁ፤ እግዚአ
ብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች
ማስነሣት እንዲቻለው እነግራችኋለሁ። ፲እነሆ፥
ምሳር በዛፎች ግንድ ላይ ሊወድቅ ተቃጥቶአ
ልና፥ መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረ
ጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል።
፲፩"እኔ ለንስሓ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤
ጫማውን ለመሸከም የማይገባኝ ከእኔ በኋላ
የሚመጣው እርሱ ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤
እርሱ በመንፈስ ቅዱስ፥ በእሳትም ያጠምቃ
ችኋል። ፲፪ዐውድማውን የሚያጠራበት መንሽ
በእጁ ነው፤ ስንዴውንም በጎተራ ይሰበስባል፤
ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥላል።"

### ስለ ጌታችን ኢየሱስ ጥምቀት

፲፫ያን ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠ
መቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ፲፬ዮሐንስ
ግን "እኔ በአንተ ልጠመቅ እሻለሁ፤ አንተ
ወደ እኔ ትመጣለህን?" ብሎ አይሆንም
አለው። ፲፭ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ "አሁ
ንስ ተው፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም
ይገባናልና" አለው፤ ከዚህም በኋላ ተወው።
፲፮ጌታችን ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ፥ ወዲ
ያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆ፥ ሰማይም ተከፈተ
ለት፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በርግብ አም
ሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ አየ። ፲፯እነ
ሆም፥ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወድደው ልጄ
ይህ ነው" የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ።

## ምዕራፍ ፬

### ጌታችን እንደ ጾመና በዲያብሎስ እንደ ተፈተነ
(ማር. ፩፥፲፪-፲፫፤ ሉቃ. ፬፥፩-፲፫)

፩ከዚህም በኋላ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ
መንፈስ ጌታችን ኢየሱስን ወደ ምድረ በዳ ወሰ
ደው። ፪አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ጾመ፤ ከዚ
ህም በኋላ ተራበ። ፫የሚፈታተነውም ቀርቦ፥
"አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህስ እነዚህ
ድንጋዮች ዳቦ እንዲሆኑ እዘዝ" አለው። ፬ጌታ
ችን ኢየሱስም መልሶ፥ "ሰው የሚኖረው ከእ
ግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ
በእንጀራ ብቻ እንዳይደለ ተጽፎአል፤" አለው።
፭ከዚህም በኋላ፥ ዲያብሎስ ወደ ቅድስት
ከተማ ወስዶ በቤተ መቅደሱ ጫፍ ላይ አቆ
መው። ፮"አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ
ከሆንህስ ከዚህ መር ብለህ ወደ ታች ውረድ፤
ይጠብቁህ ዘንድ ስለ አንተ መላእክቱን ያዝዝ
ልሃል፤ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰነካከል በእ

---

፪፡፳፫ ኢሳ. ፲፩፡፩፤ ማር. ፩፡፳፬፤ ሉቃ. ፪፡፴፱፤ ዮሐ. ፩፡፵፭።  ፫፡፪ ማቴ. ፬፡፲፯፤ ማር. ፩፡፲፭።
፫፡፫ ኢሳ. ፵፡፫።  ፫፡፬ ፪ነገ. ፩፡፰፤ ዘካ. ፲፫፡፬፤ ዘሌ. ፲፩፡፳፪።  ፫፡፯ ማቴ. ፲፪፡፴፬፤ ፳፫፡፴፫።
፫፡፱ ዮሐ. ፰፡፴፫።  ፫፡፲ ማቴ. ፯፡፲፱።
፫፡፲፯ ዘፍ. ፳፪፡፪፤ መዝ. ፪፡፯፤ ኢሳ. ፵፪፡፩ ማቴ. ፲፪፡፲፰፤ ፲፯፡፭፤ ማር. ፩፡፲፩፤ ሉቃ. ፱፡፴፭።
፬፡፩ ዕብ. ፪፡፲፰፤ ፬፡፲፭።  ፬፡፪ ዘፀ. ፴፬፡፳፰፤ ፩ነገ. ፲፱፡፰።  ፬፡፬ ዘዳ. ፰፡፫።
፬፡፭ ነህ. ፲፩፡፩፤ ዳን. ፱፡፳፬።  ፬፡፮ መዝ. ፺፡፲፩-፲፪።

ጃቸው ያነሡሃል ተብሎ ተጽፎአልና” አለው።
፯ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ “አምላክህ እግዚ
አብሔርን አትፈታተነው ተብሎ ደግሞ ተጽፎ
አል” አለው። ፰ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ እጅግ
ረዥም ወደ ሆነ ተራራ አውጥቶ የዓለሙን
ሁሉ መንግሥታት፥ ክብራቸውንም ሁሉ አሳ
የው። ፱“ብትሰግድልኝ፥ እጅ ብትነሳኝም ይህን
ሁሉ እሰጥሀለሁ” አለው። ፲ከዚህም በኋላ ጌታ
ችን ኢየሱስ፥ “አንተ ሰይጣን ከአጠገቤ ሂድ፤
ለጌታህ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ እርሱንም ብቻ
አምልክ ተብሎ ተጽፎአል” አለው። ፲፩ከዚህም
በኋላ ዲያብሎስ ተወው፤ እነሆም፥ መላእክት
ሊያገለግሉት መጡ።

## ከናዝሬት ወደ ቅፍርናሆም ስለ መሄዱ
(ማር. ፩፥፲፬-፲፭፤ ሉቃ. ፬፥፲፬-፲፭)

፲፪ጌታችን ኢየሱስም ዮሐንስ እንደ ተያዘ
በሰማ ጊዜ ወደ ገሊላ አውራጃ ሄደ። ፲፫ናዝሬ
ትንም ትቶ መጣና በዛብሎንና በንፍታሌም አገ
ሮች መካከል በምትገኝ በባሕር አጠገብ ባለች
በቅፍርናሆም ኖረ። ፲፬በነቢዩ በኢሳይያስ የተነ
ገረው ይፈጸም ዘንድ፥ እንዲህ ሲል፦ ፲፭“የዛ
ብሎን ምድርና የንፍታሌም ምድር፥ የባሕር
መንገድ፥ የዮርዳኖስ ማዶ አሕዛብ የሚኖሩበት
ገሊላ። ፲፮በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ታላቅ ብርሃ
ንን አየ፤ በጨለማና በሞት ጥላ ለነበሩም ብር
ሃን ወጣላቸው።”

## ስለ መጀመሪያዪቱ ትምህርትና ስለ አራቱ ደቀ መዛሙርት መጠራት
(ማር. ፲፮፥፳፤ ሉቃ. ፭፥፩-፲፩)

፲፯ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስ
“መንግሥተ ስማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ”
እያለ ይሰብክ ጀመረ። ፲፰በገሊላ ባሕር ዳር
ሲመላለስም፥ ሁለቱን ወንድማማቾች ጴጥሮስ
የተባለ ስምዖንንና ወንድሙን እንድርያስን መረ
ባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፤ ዓሣ አጥማ
ጆች ነበሩና። ፲፱ጌታችን ኢየሱስም፥ “ኑ ተከ
ተሉኝ፤ ሰውን የምታጠምዱ እንድትሆኑ አደር
ጋችኋለሁ” አላቸው። ፳ወዲያውኑ መረባቸውን
ትተው ተከተሉት። ፳፩ከዚያም ጥቂት እልፍ
ብሎ ሌሎችን ሁለት ወንድማማቾች የዘብዴ
ዎስ ልጅ ያዕቆብንና ወንድሙን ዮሐንስን ከአባ
ታቸው ከዘብዴዎስ ጋራ በታንኳ ውስጥ ሆነው
መረባቸውን ሲያበጁ አየና ጠራቸው። ፳፪እነ
ርሱም ወዲያውኑ ታንኳቸውንና አባታቸውን
ትተው ተከተሉት።

## በሕሙማን ላይ ስለ ተደረገው ተአምር
(ሉቃ. ፮፥፲፯-፲፱)

፳፫ጌታችን ኢየሱስም በምኵራባቸው እያስተ
ማረ፥ የመንግሥቱንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝ
ብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በመ
ላው ገሊላ ይመላለስ ነበር። ፳፬ዝናውም በመ
ላው ሶርያ ተዳረሰ፤ የታመሙትን ሁሉ፥ የተ
ጨነቁትንም፥ ደዌያቸውም ልዩ ልዩ የሆነውን፥
አጋንንትም ያደሩባቸውን፥ ጨረቃ እያየ የሚ
ጥላቸውን፥ ልምሾዎችንም ሁሉ አመጡለት፤
ሁሉንም ፈወሳቸው። ፳፭ብዙ ሕዝብም ከገሊላና
ዐሥር ከተማ ከሚባል አገር፥ ከኢየሩሳሌምና
ከይሁዳ፥ ከዮርዳኖስም ማዶ ተከተሉት።

## ምዕራፍ ፭

### አንቀጸ ብፁዓን

፩ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ ወደ ተራራ ወጥቶ
ተቀመጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ
ቀረቡ። ፪አፉንም ከፈተ፤ እንዲህም ብሎ አስ
ተማራቸው። ፫“በመንፈስ ነዳያን የሆኑ ብፁዓን
ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።
፬ዛሬ የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ መጽናናትን
ያገኛሉና። ፭የዋሃን ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ
ምድርን ይወርሳሉና። ፮ስለ ጽድቅ የሚራቡና
የሚጠሙ[፩] ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ ይጠግባ
ሉና። ፯የሚራሩ ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ ምሕ
ረትን ያገኛሉና። ፰ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁ
ዓን ናቸው፤ እነርሱ እግዚአብሔርን ያዩታልና።
፱ዕርቅን የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው፤ እነርሱ
የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። ፲ስለ ጽድቅ
የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት
የእነርሱ ናትና። ፲፩በሚሰድቧችሁና በሚያሳድዱ
አችሁ ጊዜ፥ ስለ እኔም እየዋሹ ክፉውን ሁሉ

---

፩ ግሪኩ “ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ” ይላል።

፬፥፯ ዘዳ. ፮፥፲፮። ፬፥፲ ዘዳ. ፮፥፲፫። ፬፥፲፪ ማቴ. ፲፬፥፫፤ ማር. ፮፥፲፯፤ ሉቃ. ፫፥፲፱-፳።
፬፥፲፫ ዮሐ. ፪፥፲፪። ፬፥፲፭-፲፮ ኢሳ. ፱፥፩-፪። ፬፥፲፯ ማቴ. ፫፥፪። ፬፥፳፫ ማቴ. ፱፥፴፭፤ ማር. ፩፥፴፱።
፭፥፬ ኢሳ. ፷፩፥፪። ፭፥፭ መዝ. ፴፯፥፲፩። ፭፥፮ ኢሳ. ፶፭፥፩-፪። ፭፥፰ መዝ. ፳፬፥፫-፬።
፭፥፲ ፩ጴጥ. ፫፥፲፬። ፭፥፲፩ ፩ ጴጥ. ፬፥፲፬።

በሚናገሩባችሁ ጊዜ ብፁዓን ናችሁ። ፲፪ደስ ይበላችሁ፤ ሐሤትንም አድርጉ፤ ዋጋችሁ በሰማያት ብዙ ነውና፤ ከእናንተ አስቀድሞ የነበሩ ነቢያትንም እንዲሁ አሳድደዋቸው ነበርና።

፲፫"እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን እንግዲህ በምን ይጣፍጣል? እንግዲህ የሚጠቅመው የለም፤ ሰዎች ወደ ውጭ አውጥተው ይጥሉታል፤ በእግራቸውም ይረግጡታል እንጂ።

፲፬"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፤ በተራራ ላይ የተሠራች ከተማ መሰወር አይቻላትም። ፲፭ከእንቅብ በታች ሊያኖሯት መብራትን አያበሩም፤ በመቅረዝዋ ላይ አኑረዋት በቤት ላሉት ሁሉ ታበራለች እንጂ። ፲፮መልካሙን ሥራችሁን አይተው፥ በሰማያት ያለውን አባታችሁን ያመሰግኑት ዘንድ እንዲሁ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ።

## ስለ ብሉይ ኪዳን መጽናት

፲፯"ኦሪትንና ነቢያትን ልሽራቸው የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽማቸው ነው እንጂ ልሽራቸው አልመጣሁም። ፲፰እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ አታልፍም። ፲፱ከእነዚህ ከጥቃቅኑ ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር፥ ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግና የሚያስተምር ግን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል። ፳አሁንም ጽድቃችሁ ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደማትገቡ እነግራችኋለሁ።

## ስለ ስድስቱ ቃላት

፳፩"ለቀደሙት ሰዎች 'አትግደል፥ የገደለም እርሱ ይፈረድበታል' የተባለውን ሰምታችኋል። ፳፪እኔ ግን እላችኋለሁ፤ በወንድሙ ላይ በከንቱ የሚቈጣ ሁሉ እርሱ ይፈረድበታል፤ ወንድሙንም ጨርቅ ለባሽ የሚለው በአደባባይ ይፈረድበታል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ በገሃነመ እሳት ይፈረድበታል። ፳፫መባህን በመሠውያው በምታቀርብበት ጊዜ፥ በዚያም ሳለህ የተጣላህ ወንድምህ እንዳለ ብታስብ፥ ፳፬መባህን ከዚያ በመሠውያው ፊት ትተህ ሂድና አስቀድመህ ከወንድምህ ጋር ታረቅ፤ ከዚህ በኋላም ተመልሰህ መባህን አቅርብ። ፳፭በመንገድ ከእርሱ ጋር ሳለህ ከባለጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባለጋራህ ለዳኛ እንዳይሰጥህ፤ ዳኛውም አሳልፎ ለሎሌው ይሰጥህል፤ ወደ እስር ቤትም ትገባለህ። ፳፮እውነት እልሀለሁ፤ የመጨረሻውን ትንሽ ገንዘብ እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም። ፳፯ለቀደሙት ሰዎች 'አታመንዝር' የተባለውን ሰምታችኋል። ፳፰እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን አይቶ የተመኘት ሁሉ ፈጽሞ በልቡ አመነዘረባት። ፳፱ቀኝ ዐይንህ ብታስትህ፥ ከአንተ አውጥተህ ጣላት፤ ሁለት ዐይና ሆነህ ወደ ገሃነመ እሳት ከምትገባ ይልቅ፥ አንድ ዐይና ሆነህ ወደ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና። ፴ቀኝ እጅህም ብታስትህ፥ ቈርጠህ ከአንተ ጣላት፤ አካልህ ሁሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካልህ አንዱ ቢጠፋ ይሻላልና።[፬] ቀኝ እግርህም ብታስትህ ቈርጠህ ከአንተ ጣላት፤ አካልህ ሁሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካልህ አንዱ ቢጠፋ ይሻላልና።

፴፩"ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ፥ የፍችዋን ደብዳቤ ይስጣት ተብሏል። ፴፪እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ እርሱ ራሱ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።

፴፫"ዳግመኛም ለቀደሙት ሰዎች፥ መሐላችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ እንጂ በሐሰት አትማሉ የተባለውን ሰምታችኋል። ፴፬እኔ ግን እላችኋለሁ፦ ከቶ አትማሉ፤ በሰማይም ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና። ፴፭በምድርም ቢሆን፥ የእግሩ መረገጫው ናትና፤ በኢየሩሳ

---

፬ ቀጣዩ በግሪኩ የለም።

፭፥፲፪ ፪ዜ.መ. ፴፮፥፲፮፤ ሐ.ሥ. ፯፥፶፪። ፭፥፲፫ ማር. ፱፥፶፤ ሉቃ. ፲፬፥፴፬-፴፭። ፭፥፲፬ ዮሐ. ፰፥፲፪፤ ፱፥፭።

፭፥፲፭ ማር. ፬፥፳፩፤ ሉቃ. ፰፥፲፮፤ ፲፩፥፴፫። ፭፥፲፮ ፩ጴጥ. ፪፥፲፪። ፭፥፲፰ ሉቃ. ፲፮፥፲፯።

፭፥፳፩ ዘፀ. ፳፥፲፫፤ ዘዳ. ፭፥፲፯፤ ፲፮፥፲፰። ፭፥፳፯ ዘፀ. ፳፥፲፬፤ ዘዳ. ፭፥፲፰።

፭፥፳፱ ማቴ. ፲፰፥፱፤ ማር. ፱፥፵፯። ፭፥፴ ማቴ. ፲፰፥፰፤ ማር. ፱፥፵፫።

፭፥፴፩ ዘዳ. ፳፬፥፩-፬፤ ማቴ. ፲፱፥፯፤ ማር. ፲፥፬።

፭፥፴፪ ማቴ. ፲፱፥፱፤ ማር. ፲፥፲፩-፲፪፤ ሉቃ. ፲፮፥፲፰፤ ፩ቆሮ. ፯፥፲-፲፩።

፭፥፴፫ ዘሌ. ፲፱፥፲፪፤ ዘኁ. ፴፥፪፤ ዘዳ. ፳፫፥፳፩። ፭፥፴፬ ያዕ. ፭፥፲፪፤ ኢሳ. ፷፮፥፩፤ ማቴ. ፳፫፥፳፪።

፭፥፴፭ ኢሳ. ፷፮፥፩፤ መዝ. ፵፰፥፪።

ሌምም ቢሆን፥ የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና።
፴፮በራሳችሁም ቢሆን አትማሉ፤ ከራስ ጠጉ
ራችሁ አንዲቱን ነጭ ማድረግ ወይም ጥቍር
ማድረግ አትችሉምና። ፴፯ነገር ግን ቃላችሁ
አዎን አዎን፥ ወይም አይደለም አይደለም
ይሁን፤ ከእነዚህም የወጣ ከክፉ ወገን ነው።
፴፰“ለቀደሙት ሰዎች ዐይን ስለ ዐይን፥ ጥር
ስም ስለ ጥርስ የተባለውን ሰምታችኋል። ፴፱እኔ
ግን እላችኋለሁ፤ ክፉን በክፉ፫ አትቃወሙት፤
ቀኝ ፊትህን ለሚመታህ ግራ ፊትህን መልስ
ለት። ፵ቀሚስህንም ሊቀማህ ለሚሻ መጐናጸፊ
ያህን ተውለት። ፵፩አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ
ቢያስገድድህ ሁለት ምዕራፍ አብረኸው ሂድ።
፵፪ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ፤ ከአንተም ሊበደር
የሚወደውን አትከልክለው።
፵፫“ባልንጀራህን ውደድ፤ ጠላትህንም ጥላ
የተባለውን ሰምታችኋል። ፵፬እኔ ግን እላችኋ
ለሁ፤ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሙአች
ሁን መርቁ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድ
ርጉ፤ ስለሚበድሉአችሁና ስለሚያሳድዱአች
ሁም ጸልዩ። ፵፭በሰማያት ላለው አባታችሁ
ልጆች ትሆኑ ዘንድ፤ እርሱ ለክፉዎችና ለደ
ጎች ፀሐይን ያወጣልና፥ ለጻድቃንና ለኃጥአ
ንም ዝናምን ያዘንማልና። ፵፮የሚወዱአችሁ
ንማ ብትወዱ ዋጋችሁ ምንድን ነው? እንደዚ
ህማ ቀራጮችስ ያደርጉ የለምን? ፵፯ወንድሞቻ
ችሁን ብቻ እጅ ብትነሡ፥ ምን ብልጫ ታደ
ርጋላችሁ? አሕዛብስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን?
፵፰እንግዲህ ሰማያዊው አባታችሁ ፍጹም እንደ
ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።”

## ምዕራፍ ፮

### አንቀጸ ምጽዋት

፩“ለሰዎች ትታዩ ዘንድ፥ ምጽዋታችሁን በሰ
ዎች ፊት እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰ
ማያት ባለው በአባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም።
፪ምጽዋታችሁንም በምታደርጉበት ጊዜ፥ ግብ
ዞች በሰዎች ዘንድ ሊመሰገኑ በምኵራብና በአ
ውራ ጎዳና እንደሚያደርጉት በፊታችሁ መለ
ከት አታስነፉ፤ እውነት እላችኋለሁ፤ ዋጋቸውን
ተቀብለዋል። ፫አንተስ ምጽዋትህን በምታደርግ
በት ጊዜ ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ።
፬ምጽዋትህ በስውር ይሁን፤ በስውር የሚያይህ
አባትህም በግልጥ ዋጋህን ይሰጥሃል።

### አንቀጸ ጸሎት
(ሉቃ. ፲፩፥፪-፬)

፭“በምትጸልዩበትም ጊዜ እንደ ግብዞች አት
ሁኑ፤ እነርሱ ለሰው ይታዩ ዘንድ፥ በምኵራ
ብና በአደባባይ መዓዝን መቆምንና መጸለይን
ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፤ ዋጋቸውን
ተቀብለዋል። ፮አንተ ግን በምትጸልይበት ጊዜ
ወደ ቤትህ ግባ፤ ደጅህንም ዘግተህ በስውር
ወደ አባትህ ጸልይ፤ በስውር የሚያይህ አባት
ህም በግልጥ ዋጋህን ይሰጥሃል። ፯ስትጸልዩም
እንደ አሕዛብ ነገርን አታብዙ፤ እነርሱ ነገራቸ
ውን በማብዛታቸው የሚሰማቸው ይመስላቸዋ
ልና። ፰አትምሰሏቸው፤ ሰማያዊው አባታችሁ
ሳትለምኑት የምትሹትን ያውቃልና። ፱እናን
ተስ በምትጸልዩበት ጊዜ እንዲህ በሉ፦ ‘አባታ
ችን ሆይ፥ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ።
፲መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ
ሆነ እንዲሁ በምድር ይሁን። ፲፩የዕለት ምግባ
ችንን ዛሬ ስጠን። ፲፪በደላችንን ይቅር በለን፤
እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል። ፲፫አቤቱ
ወደ ፈተና አታግባን፤ ከክፉ ሁሉ አድነን
እንጂ፤ መንግሥት የአንተ ናትና ኀይል፥ ምስ
ጋና፥ ለዘለዓለሙ አሜን።’ ፲፬ለሰዎች በደላቸ
ውን ይቅር ብትሉ፥ ሰማያዊው አባታችሁ በደ
ላችሁን ይቅር ይላችኋልና። ፲፭ነገር ግን ለሰዎች
በደላቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም በደላች
ሁን ይቅር አይላችሁም።

### አንቀጸ ጾም

፲፮“በምትጾሙበት ጊዜ እንደ ግብዞች አት
ጠውልጉ፤ እነርሱ እንደ ጾሙ ለሰው ይታዩ
ዘንድ መልካቸውን ይለውጣሉና፥ እውነት እላ
ችኋለሁ፤ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። ፲፯እናንተስ
በምትጾሙበት ጊዜ ራሳችሁን ቅቡ፤ ፊታችሁ
ንም ታጠቡ። ፲፰በስውር ለሚያይ ለአባታችሁ
እንጂ፥ ለሰዎች እንደ ጾማችሁ እንዳትታዩ፤ በስ

---

፫ “በክፉ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፭፥፴፫ ዘሌ. ፲፱፥፲፪፤ ዘኁ. ፴፥፪፤ ዘዳ. ፳፫፥፳፩። ፭፥፴፰ ዘፀ. ፳፩፥፳፬፤ ዘሌ. ፳፬፥፳፤ ዘዳ. ፲፱፥፳፩።
፭፥፵፪ ዘዳ. ፲፭፥፰፤ ምሳ. ፳፬፥፳፱። ፭፥፵፫ ዘሌ. ፲፱፥፲፰። ፭፥፵፬ ምሳ. ፳፭፥፳፩-፳፪።
፭፥፵፰ ዘሌ. ፲፱፥፪፤ ፲፰፤ ዘዳ. ፲፰፥፲፫። ፮፥፩ ማቴ ፳፫፥፭። ፮፥፭ ሉቃ. ፲፰፥፲-፲፬።
፮፥፯ ፩ነገ. ፲፰፥፳፭-፳፱። ፮፥፲፬-፲፭ ማቴ. ፲፩፥፳፭-፳፮። ፮፥፲፮ ኢሳ. ፶፰፥፭።

ውር የሚያያችሁ አባታችሁም ዋጋችሁን በግ
ልጥ ይሰጣችኋል።

## ስለ ሰማያት መዝገብ
(ሉቃ. ፲፪፥፴፫-፴፬)

፲፱“ብልና ነቀዝ በሚያበላሹት፥ ሌቦችም ቈፍ
ረው በሚሰርቁበት በምድር ለእናንተ መዝገብ
አትሰብስቡ። ፳ነገር ግን ብልና ነቀዝ በማያበ
ላሹት፥ ሌቦችም ቈፍረው በማይሰርቁት በሰ
ማይ ለእናንተ መዝገብን ሰብስቡ። ፳፩መዝገባ
ችሁ ባለበት ልባችሁ በዚያ ይኖራልና።
፳፪“የሰውነትህ መብራቱ ዐይንህ ነው፤ ዐይ
ንህ ብሩህ ቢሆን ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆ
ናል። ፳፫ዐይንህ ግን ታማሚ ቢሆን ሰውነትህ
ሁሉ ጨለማ ይሆናል፤ በአንተ ላይ ያለው ብር
ሃን ጨለማ ከሆነ ጨለማህ እንዴት ይበዛ!
፳፬ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው አገልጋይ
የለም፤ ያለዚያ አንዱን ይወዳል፤ ሁለተኛው
ንም ይጠላል፤ ወይም ለአንዱ ይታዘዛል፤ ለሁ
ለተኛውም አይታዘዝም፤ እንግዲህ ለእግዚአብ
ሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።

## ለምግብና ለልብስ መጨነቅ እንደማይገባ

፳፭“ስለዚህም እላችኋለሁ፤ ለነፍሳችሁ በም
ትበሉትና በምትጠጡት፥ ለሥጋችሁም በም
ትለብሱት አትጨነቁ፤ ነፍስ ከምግብ አት
በልጥምን? ሥጋስ ከልብስ አይበልጥምን?
፳፮የማይዘሩና የማያጭዱ፥ በጎተራም የማይ
ሰበስቡ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፤ ሰማ
ያዊ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ
ከእነርሱ እጅግ ትበልጡ የለምን? ፳፯ከእ
ናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ
መጨመር የሚችል ማን ነው? ፳፰ስለ ልብ
ስስ ለምን ትጨነቃላችሁ? የምድረ በዳ አበ
ቦች እንዴት እንደሚያድጉ እዩ፤ አይደክ
ሙም፤ አይፈትሉምም። ፳፱ነገር ግን እላች
ኋለሁ፦ ሰሎሞንስ እንኳ በዚያ ሁሉ ክብሩ
ከእነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም። ፴እግዚአ
ብሔር ግን ዛሬ ያለውን፥ ነገም ወደ እሳት
ምድጃ የሚጣለውን የምድረ በዳ ሣር እነሆ፥
እንደዚህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ ሃይ
ማኖት የጐደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እን
ዴት? ፴፩እንግዲህ ምን እንበላለን? ምን እን
ጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አት
ጨነቁ። ፴፪ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይሹታልና፤
ለእናንተ ግን ሰማያዊ አባታችሁ ይህን ሁሉ
እንድትሹ ያውቃል። ፴፫እናንተስ አስቀድማ
ችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት፥ ጽድቁ
ንም ፈልጉ፤ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።
፴፬ለነገ አትጨነቁ፤ ነገ ለራስዋ ታስባለችና፤
ለቀኒቱ ክፋቷ ይበቃታል።

## ምዕራፍ ፯

## በሌሎች ላይ መፍረድ እንደማይገባ
(ሉቃ. ፮፥፴፯-፵፪)

፩“እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ። ፪በምት
ፈርዱት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፥ በምትሰፍ
ሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋልና። ፫በወን
ድምህ ዐይን ያለውን ጉድፍ ለምን ታያለህ?
በአንተ ዐይን ያለውን ምሰሶ ግን ለምን
አታስተውልም? ፬ወንድምህን በዐይንህ ያለ
ውን ጉድፍ ላውጣልህ ተወኝ እንዴት ትለ
ዋለህ? እነሆም፥ በአንተ ዐይን ምሰሶ አለ።
፭አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ በአንተ ያለ
ውን ምሰሶ አውጣ፤ ከዚህ በኋላ በወንድ
ምህ ዐይን ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አጥ
ርተህ ታያለህ።
፮“በእግራቸው እንዳይረግጡት፥ ተመልሰ
ውም እንዳይነክሱአችሁ የተቀደሰውን ለው
ሾች አትስጡ፤ ዕንቍአችሁንም በዕሪያዎች
ፊት አታኑሩ። ፯ለምኑ፥ ይሰጣችኋልም፤
ፈልጉ፥ ታገኛላችሁም፤ ደጅ ምቱ፥ ይከ
ፈትላችኋልም። ፰የሚለምን ሁሉ ይቀበላ
ልና፥ የሚፈልግም ያገኛልና፥ ደጅ ለሚመ
ታም ይከፈትለታልና። ፱ከእናንተ ልጁ ዳቦ
ቢለምነው ድንጋይ የሚሰጠው ሰው ማነው?
፲ወይስ ዓሣ ቢለምነው እባብ ይሰጠዋልን?
፲፩እንግዲህ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆ
ቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃ
ችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁማ ለሚ
ለምኑት መልካሙን ነገር እንዴት አብልጦ
ይሰጣቸው ይሆን? ፲፪ሰዎች ሊያደርጉላችሁ
የምትወዱትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድ
ርጉላቸው፤ ኦሪትም፥ ነቢያትም የሚያዝ
ዙት ይህ ነውና።

---

፮፥፲፱ ያዕ. ፭፥፪-፫። ፮፥፳፪ ሉቃ. ፲፩፥፴፬-፴፮። ፮፥፳፬ ሉቃ. ፲፮፥፲፫፤ ፲፪፥፳፪-፴፩።
፮፥፳፯ መዝ. ፴፰፥፭-፯። ፮፥፳፱ ፩ነገ. ፲፥፩-፯፤ ፪ዜ.መ. ፱፥፫-፮። ፯፥፪ ማር. ፬፥፳፬።
፯፥፯ ሉቃ. ፲፩፥፱-፲፫። ፯፥፲፪ ሉቃ. ፮፥፴፩።

### ጠባቢቱ በር

፲፫“በጠባቢቱ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት የምትወ
ስድ ሰፊ በር፥ ሰፊ መንገድም አለችና፤ ወደ
እርስዋም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው። ፲፬ወደ ሕይ
ወት የምትወስደው በር እጅግ ጠባብ፥ መንገ
ድዋም ቀጭን ናትና፤ የሚገቡባትም ጥቂቶች
ናቸው።

፲፭“የበግ ለምድ ለብሰው ወደ እናንተ ከሚ
መጡ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ፤ በውስጣ
ቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ናቸው። ፲፮ከፍ
ሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፤ ከእሾህ ወይን፥ ከአ
ሜከላም በለስ ይለቀማልን? ፲፯እንዲሁ መል
ካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬን ያፈራል፤ ክፉ
ዛፍም ክፉ ፍሬን ያፈራል። ፲፰መልካምም ዛፍ
ክፉ ፍሬን ማፍራት፥ ክፉ ዛፍም መልካም
ፍሬን ማፍራት አይችልም። ፲፱መልካም ፍሬ
የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል፤ ወደ እሳትም
ይጣላል። ፳እንግዲህ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋ
ላችሁ።

### የአብን ፈቃድ ስለ ማድረግ

፳፩“በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ ከሚ
ያደርግ በቀር አቤቱ! አቤቱ! የሚለኝ ሁሉ
ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።
፳፪በዚያች ቀን ብዙዎች አቤቱ! አቤቱ! በስ
ምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ አጋ
ንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራ
ትን አላደረግንምን? ይሉኛል። ፳፫ያንጊዜ ከቶ
አላውቃችሁም፤ ዐመፅን የምታደርጉ ሁላችሁ
ከእኔ ራቁ እላቸዋለሁ። ፳፬ይህን ቃሌን ሰምቶ
የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዐለት ላይ የሠራ
ብልህ ሰውን ይመስላል። ፳፭ዝናም ዘነመ፤
ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት
ገፋት፤ ነገር ግን አልወደቀም፤ በዐለት ላይ
ተመሥርቶአልና። ፳፮ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማ
ያደርገው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ
ሰውን ይመስላል። ፳፯ዝናም ዘነመ፤ ጐርፍም
ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንም ቤት ገፋት፤
ወደቀም፤ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።” ፳፰ጌታ
ችን ኢየሱስም ይህን ነገር በፈጸመ ጊዜ
ሕዝቡ በትምህርቱ ተደነቁ። ፳፱እንደ ጸፎቻ
ቸው ሳይሆን እንደ ባለሥልጣን ያስተምራ
ቸው ነበርና።

## ምዕራፍ ፰

### ጌታችን ለምጻሙን ሰው እንደ አዳነ

(ማር. ፩፥፵-፵፭፤ ሉቃ. ፭፥፲፪)

፩ከተራራም ሲወርድ ብዙ ሰዎች ተከተሉት።
፪እነሆ፥ አንድ ለምጻም ሰው መጥቶ፥ “አቤቱ!
ከወደድህስ እኔን ማንጻት ይቻልሃል” እያለ ሰገ
ደለት። ፫እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና “እፈቅዳ
ለሁ ንጻ” አለው፤ ያንጊዜም ከለምጹ ነጻ።
፬ጌታችን ኢየሱስም፥ “ለማንም እንዳትናገር
ተጠንቀቅ፤ ነገር ግን ሂድና ራስህን ለካህን አስ
መርምር፤ ምስክርም ሊሆንባቸው ሙሴ እንደ
አዘዘ መባህን አቅርብ” አለው።

### የመስፍኑን ልጅ ጌታችን ኢየሱስ እንደ ፈወሰው

(ሉቃ. ፯፥፩-፲)

፭ወደ ቅፍርናሆም በገባ ጊዜ የመቶ አለቃ
ወደ እርሱ መጥቶ፡- ፮“አቤቱ! ልጄ ሽባ ሆኖ
እጅግ እየተጨነቀ በቤት ተኝቶአል” ብሎ ለመ
ነው። ፯ጌታችን ኢየሱስም “እኔ መጥቼ እፈው
ሰዋለሁ” አለው። ፰የመቶ አለቃውም መልሶ፥
“አቤቱ! አንተ ከቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይ
ገባኝም፤ ነገር ግን በቃልህ እዘዝ፤ ልጄም ይድ
ናል፤ ፱እኔም እኮ የምገዛ ሰው ነኝ፤ የማዝዛ
ቸውም ጭፍሮች አሉኝ፤ ይህን ሂድ ብለው
ይሄዳል፤ ሌላውንም ና ብለው ይመጣል፤ አገ
ልጋዬንም ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል”
አለው። ፲ጌታችን ኢየሱስም ሰምቶ አደነቀ፤
ለሚከተሉትም እንዲህ አለ፥ “እውነት እላች
ኋለሁ፤ በእስራኤል ሁሉ እንዲህ ያለ እምነት
አላገኘሁም፤ ፲፩ነገር ግን እላችኋለሁ፡- ብዙ
ዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፤ በመን
ግሥተ ሰማያትም ከአብርሃምና ከይስሐቅ፥ ከያ
ዕቆብም አጠገብ ይቀመጣሉ። ፲፪የመንግሥትን
ልጆች ግን በውጭ ወደ አለ ጨለማ ይጥሏቸ
ዋል፤ በዚያም ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆ
ናል።” ፲፫ጌታችን ኢየሱስም የመቶ አለቃውን
እንዲህ አለው፥ “እንግዲህ ሂድ እንደ እምነ

---

፯፥፲፫ ሉቃ. ፲፫፥፳፬። ፯፥፲፬ ኤር. ፳፩፥፰፤ ዘዳ. ፴፥፲፱። ፯፥፲፭ ሕዝ. ፳፪፥፳፯።
፯፥፲፱ ማቴ. ፫፥፲፤ ሉቃ. ፫፥፱። ፯፥፳ ማቴ. ፲፪፥፴፫። ፯፥፳፫ መዝ. ፮፥፰።
፯፥፳፰-፳፱ ማር. ፩፥፳፪ ሉቃ. ፬፥፴፪፤ ማር. ፩፥፳፪፤ ሉቃ. ፬፥፴፪። ፰፥፬ ዘሌ. ፲፬፥፩-፴፪። ፰፥፲፩ ፲፫፥፳፱።
፰፥፲፪ ኢሳ. ፵፱፥፲፪፤ ፶፱፥፲፱ ሚል. ፩፥፲፩፤ መዝ. ፻፯፥፫፤ ማቴ. ፳፪፥፲፫፤ ፳፭፥፴፤ ሉቃ. ፲፫፥፳፰።

ትህ ይሁንልህ።” ልጁም በዚያ ሰዓት ዳነ፤
መስፍኑም ወደ ቤቱ በተመለሰ ጊዜ ልጁ ድኖ
አገኘው።[፩]

### ስለ ጴጥሮስ አማት መፈወስ

(ማር. ፩፥፳፱-፴፬፤ ሉቃ. ፬፥፴፰-፵፩)

[፲፬]ጌታችን ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ቤት በገባ
ጊዜ የጴጥሮስን አማት በንዳድ ታማ ተኝታ
አገኛት። [፲፭]እጅዋንም ይዞ ዳሰሳት፤ ንዳዱም
ተዋት፤ ተነሥታም አገለገለቻቸው።

### ከብዙ ደዌ ስለ ዳኑ ሰዎች

[፲፮]በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደሩባቸውን
ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ፤ አጋንንት
ንም በቃሉ አወጣቸው። የታመሙትንም ሁሉ
ፈወሰ። [፲፯]ይህም ነቢዩ ኢሳይያስ፥ “ደዌያችንን
ተቀበለ፤ ሕማማችንንም ተሸከመ” ብሎ የተ
ናገረው ይፈጸም ዘንድ ነው። [፲፰]ጌታችን ኢየሱ
ስም በዙሪያው የተሰበሰቡትን ብዙ ሰዎች በአየ
ጊዜ ባሕሩን ተሻግረው እንዲሄዱ አዘዘ።

### ሊከተሉት ስለ ጠየቁት ሰዎች

(ሉቃ. ፱፥፶፯-፷፪)

[፲፱]አንድ ጸሓፊ ወደ እርሱ መጥቶ፥ “መም
ህር፥ ወደምትሄድበት ሁሉ ልከተልህን?”
አለው። [፳]ጌታችን ኢየሱስም፥ “ለቀበሮዎች
ጕድጓድ አላቸው፤ ለሰማይ ወፎችም ጎጆ አላ
ቸው፤ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋ
በት የለውም” አለው። [፳፩]ከደቀ መዛሙርቱም
አንዱ፥ “ጌታ ሆይ አስቀድሜ ልሂድና አባቴን
ልቅበር ፍቀድልኝ” አለው። [፳፪]ጌታችን ኢየ
ሱስም፥ “አንተስ ተከተለኝ፤ ሙታኖቻቸውን
ይቀብሩ ዘንድ ሙታንን ተዋቸው” አለው።

### ማዕበሉን ፀጥ እንደ አደረገ

(ማር. ፬፥፴፭-፵፩)

[፳፫]ወደ ታንኳ በወጣ ጊዜም ደቀ መዛሙርቱ
ተከተሉት። [፳፬]እነሆም፥ የባሕሩ ማዕበል ታንኳ
ውን እስኪደፍነው ድረስ በባሕሩ ውስጥ ታላቅ
መናወጥ ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር። [፳፭]ደቀ
መዛሙርቱም ቀርበው ቀሰቀሱትና፥ “አቤቱ!
እንዳንሞት አድነን” አሉት። [፳፮]እርሱም፥ “እና
ንተ እምነት የጐደላችሁ ምን ያስፈራችኋል?”
አላቸው፤ ተነሥቶም ነፋሳትንና የባሕሩን ማዕ
በል ገሠጻቸው፤ ታላቅ ፀጥታም ሆነ። [፳፯]ሰዎ
ችም፥ “ባሕርና ነፋሳትስ እንኳ የሚታዘዙለት
ይህ ማነው?” እያሉ ተደነቁ።

### አጋንንት ስለ አደሩባቸው ሰዎች

(ማር. ፭፥፩-፳፤ ሉቃ. ፰፥፳፮)

[፳፰]ወደ ማዶም ወደ ጌርጌሴኖን ሀገር በደረሰ
ጊዜ አጋንንት ያደሩባቸው ሁለት ሰዎች ከመ
ቃብር ወጥተው ተቀበሉት፤ እነርሱም ማንም
በዚያች መንገድ ማለፍ እስከማይችል ድረስ
እጅግ ክፉዎች ነበሩ። [፳፱]ባዩት ጊዜም፥ “የእ
ግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር
ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን ወደ
ዚህ መጣህን?” እያሉ ጮኹ። [፴]ከዚያም ብዙ
የእሪያ መንጋዎች ከእነርሱ ርቀው ተሰማር
ተው ነበሩ። [፴፩]እነዚያ አጋንንትም፥ “ካወጣኸ
ንስ በእሪያዎቹ መንጋ ላይ እንድናድር ወደዚያ
ስደደን” ብለው ለመኑት፤ እርሱም “ሂዱ”
አላቸው። [፴፪]ወጥተውም ሄዱ፤ በእሪያዎቹም
ላይ አደሩ፤ የእሪያዎችም መንጋዎች ሁሉ ከአ
ፋፉ እየሮጡ ወደ ባሕር ውስጥ ወደቁ፤ በው
ኃው ውስጥም ሞቱ። [፴፫]እረኞችም ሸሹ፤ ወደ
ከተማይቱም ገብተው ነገሩን ሁሉ፥ አጋንን
ትም ባደሩባቸው የሆነውን አወሩ። [፴፬]እነሆ፥
በከተማዋ ያሉት ሁሉ ጌታችን ኢየሱስን ሊቀ
በሉት ወጡ፤ ባዩት ጊዜም ከሀገራቸው እንዲ
ሄድ ለመኑት።

## ምዕራፍ ፱

### ስለ መፃጉዕ መፈወስ

(ማር. ፪፥፩-፲፪፤ ሉቃ. ፭፥፲፯-፳፮)

[፩]ወደ ታንኳም ወጥቶ ተሻገረና ወደ ከተ
ማው ደረሰ። [፪]እነሆም፥ አንድ መፃጉዕ በአ
ልጋ ተሸክመው ወደ እርሱ አመጡ፤ ጌታ
ችን ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ መፃጉ
ዑን፥ “ልጄ ሆይ፥ ጽና፤ ኀጢአትህ ተሰርዮ
ልሀል” አለው። [፫]እነሆም፥ ከጻፎች ወገን ሰም
ተው በልባቸው፥ “ይህስ ይሳደባል” ተባባሉ።
[፬]ጌታችን ኢየሱስም አሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ
አላቸው፥ “በልባችሁ ለምን ክፉ ነገር ታስባላ
ችሁ? [፭]ኀጢአትህ ተሰረየልህ ከማለትና ተነሥ
ተህ ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል? [፮]ለሰው
ልጅ በምድር ላይ ኀጢአትን ሊያስተሰርይ

---

[፩] “መስፍኑም ወደ ቤቱ በተመለሰ ጊዜ ልጁ ድኖ አገኘው” የሚለው በግሪኩ የለም።

፰፥፲፯ ኢሳ. ፶፫፥፬። ፰፥፳፱ መሳ. ፲፩፥፲፪፤ ፪ሳሙ. ፲፮፥፲።

ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፥” ከዚህ በኋላ
ያን መፃጉዕ፥ “ተነሥ፤ አልጋህን ተሸከምና
ወደ ቤትህ ሂድ” አለው። ፯ተነሥቶም አልጋ
ውን ተሸክሞ ወደ ቤቱ ሄደ። ፰ሕዝቡም አይ
ተው አደነቁ፤ እንዲህ ያለውን ሥልጣን ለሰው
የሰጠ እግዚአብሔርንም አመሰገኑት።

## ማቴዎስ እንደ ተጠራ

(ማር. ፪፥፲፫-፲፯፤ ሉቃ. ፭፥፳፯-፴፪)

፱ጌታችን ኢየሱስም ከዚያ አልፎ ስሙ
ማቴዎስ የተባለ ሰው በቀረጥ መቀበያው ተቀ
ምጦ አገኘና፥ “ተከተለኝ” አለው፤ ተነሥ
ቶም ተከተለው። ፲በቤቱም ለምሳ ተቀምጦ
ሳለ፥ ብዙ ቀራጮችና ኀጢአተኞች መጥ
ተው ከጌታችን ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙ
ርቱ ጋር ተቀመጡ። ፲፩ፈሪሳውያንም አይ
ተው ደቀ መዛሙርቱን፥ “መምህራችሁ
ከቀራጮችና ከኀጢአተኞች ጋር ለምን ይበ
ላል?” አሉአቸው። ፲፪ጌታችን ኢየሱስም
ሰምቶ እንዲህ አላቸው፥ “በሽተኞች ባለ
መድኀኒትን ይሹታል፤ ጤነኞች ግን አይሹ
ትም። ፲፫ሂዱ፤ ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን
እመርጣለሁ ያለው ምን እንደ ሆነ ዕወቁ፤
ኃጥአንን እንጂ፥ ጻድቃንን ወደ ንስሓ ልጠራ
አልመጣሁምና።”

## ስለ ጾም

(ማር. ፪፥፲፰-፳፪፤ ሉቃ. ፭፥፴፫-፴፱)

፲፬ከዚህ በኋላ፥ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት
ወደ እርሱ መጥተው፥ “እኛና ፈሪሳውያን
ብዙ እንጾማለን፤ ደቀ መዛሙርትህስ ለምን
አይጾሙም?” አሉት። ፲፭ጌታችን ኢየሱስም
እንዲህ አላቸው፥ “የሙሽራው ሚዜዎች
ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ አይች
ሉም፤ ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወ
ሰድበት ወራት ይመጣል። ያንጊዜ ይጾማሉ።
፲፮የአዲስ ልብስ ዕራፊም በአሮጌ ልብስ ቀዳዳ
ላይ የሚጥፍ የለም፤ ደጎነኛውን ልብስ ይዞት
ይሄዳልና፤ ቀዳዳውንም ያሰፋዋልና። ፲፯በአ
ሮጌ ረዋት አዲስ የወይን ጠጅ አይጨምሩም፤
ቢጨመር ግን ረዋቱ ይቀደዳል፤ ወይኑም ይፈ
ስሳል፤ ረዋቱም ይበላሻል፤ ነገር ግን፤ አዲ
ሱን ወይን በአዲስ ረዋት ይሾሙታል፤ ሁለ
ቱም እርስ በርሳቸው ይጠባበቃሉ።”

## ስለ ምኵራቡ ሹም ልጅና ደም ስለሚፈስሳት ሴት

(ማር. ፭፥፳፩-፵፫፤ ሉቃ. ፰፥፵)

፲፰ይህንም ሲነግራቸው እነሆ፥ አንድ መኰንን
መጥቶ፥ “ልጄ አሁን ሞተች፤ ነገር ግን መጥ
ተህ እጅህን ጫንባት፤ ትድናለችም” እያለ ሰገደ
ለት። ፲፱ጌታችን ኢየሱስም ተነሥቶ ተከተለው፤
ደቀ መዛሙርቱም አብረውት ነበሩ። ፳እነሆ፥
ከዐሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም ይፈስሳት የነ
በረች ሴት በኋላው መጥታ የልብሱን ጫፍ ዳሰ
ሰች። ፳፩በልቧ፥ “የልብሱን ጫፍ ብቻ የዳሰስሁ
እንደ ሆነ እድናለሁ” ብላ ነበርና። ፳፪ጌታችን ኢየ
ሱስም መለስ ብሎ አያትና፥ “ልጄ ጽኚ፤ እም
ነትሽ አዳነችሽ” አላት፤ ከዚያም ሰዓት ጀምሮ
ያቺ ሴት ዳነች። ፳፫ጌታችን ኢየሱስም ወደዚያ
መኰንን ቤት በደረሰ ጊዜ፥ እስለቃሾችንና የሚ
ንጫጩትን ሰዎች አየ። ፳፬“በላቴናይቱ ተኝታ
ለች እንጂ የሞተች አይደለምና ፈቀቅ በሉ” አላ
ቸው፤ እነርሱም ሳቁበት። ፳፭ሰዎቹ ከወጡ በኋላ
ገብቶ እጅዋን ያዛት፤ ብላቴናዪቱም ተነሣች።
፳፮የተአምራቱም ዝና በሀገሩ ሁሉ ተሰማ።

## ስለ ሁለቱ ዕውራን

፳፯ጌታችን ኢየሱስም ከዚያ በአለፈ ጊዜ
ሁለት ዕውራን፥ “የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ራራ
ልን” ብለው እየጮኹ ተከተሉት። ፳፰ወደ
ቤትም በገባ ጊዜ እነዚያ ዕውራን ወደ እርሱ
መጡ፤ ጌታችን ኢየሱስም “ይህን ማድረግ
እንዲቻለኝ ታምናላችሁን?” አላቸው፤ እነር
ሱም፥ “አዎን ጌታ ሆይ!” አሉት። ፳፱“እንደ
እምነታችሁ ይሁንላችሁ” ብሎ ዐይኖቻቸውን
ዳሰሳቸው። ፴ያንጊዜም ዐይኖቻቸው ተገለጡ፤
ጌታችን ኢየሱስም፥ “ማንም እንዳያውቅ ተጠ
ንቀቁ” ብሎ አዘዛቸው። ፴፩እነርሱ ግን፥ ወጥ
ተው በዚያ ሀገር ሁሉ ስለእርሱ ተናገሩ።

## ጋኔን የያዘው ዲዳ እንደ ተፈወሰ

፴፪እነዚያም ከወጡ በኋላ ጋኔን ያደረበትን
ዲዳ ወደ እርሱ አመጡ። ፴፫ያደረበትም ጋኔን
በወጣ ጊዜ ዲዳ የነበረው ተናገረ፤ ሰዎችም
“በእስራኤል ውስጥ እንዲህ ያለ ከቶ አልታ
የም” እያሉ አደነቁ። ፴፬ፈሪሳውያን ግን “በአ
ጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል” አሉ።

---

፱፥፲-፲፩ ሉቃ. ፲፭፥ ፩-፪። ፱፥፲፫ ሆሴዕ ፮፥፮ ማቴ. ፲፪፥፯። ፱፥፳ ዘኁ. ፲፭፥፴፰፤ ዘዳ. ፳፪፥፲፪።
፱፥፴፬ ማቴ. ፲፥፳፭፤ ፲፪፥፳፬፤ ማር. ፫፥፳፪፤ ሉቃ. ፲፩፥፲፭።

### በገሊላ እንደ ተመላለሰ

[፴፭]ጌታችን ኢየሱስም በምኵራቦቻቸው እያስ
ተማረ፥ የመንግሥት ወንጌልንም እየሰበከ፥ በሕ
ዝቡም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በየ
ከተማውና በየመንደሩ ሁሉ ተመላለሰ። [፴፮]ብዙ
ሰዎችንም አይቶ አዘነላቸው፤ ደክመው ነበርና፥
እረኛ እንደሌላቸው በጎችም ተበትነው ነበርና።
[፴፯]ያንጊዜ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤
“መከሩስ ብዙ ነው፤ ሠራተኛው ግን ጥቂት
ነው። [፴፰]እንግዲህ ለመከሩ ሠራተኛን ይጨምር
ዘንድ የመከሩን ባለቤት ለምኑት።”

## ምዕራፍ ፲

### ስለ ሐዋርያት መጠራት

(ማር. ፫፡፲፫-፲፱፤ ሉቃ. ፮፡፲፪-፲፮)

[፩]ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ
ያወጡአቸው ዘንድ፥ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ
ይፈውሱ ዘንድ በርኩሳን መናፍስት ላይ ሥል
ጣንን ሰጣቸው። [፪]የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያትም
ስማቸው እንዲህ ነው፤ መጀመሪያው ጴጥሮስ
የተባለው ስምዖን፥ ወንድሙ እንድርያስም፥
የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብም፥ ወንድሙም ዮሐ
ንስ፤ [፫]ፊልጶስም፥ በርተሎሜዎስም፥ ቶማ
ስም፥ ቀራጩ ማቴዎስም፥ የዕልፍዮስ ልጅ ያዕ
ቆብም፥ ታዴዎስ የተባለ ልብድዮስም፤ [፬]ቀነ
ናዊው ስምዖን፥ አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ
ሰው ይሁዳም።

[፭]ጌታችን ኢየሱስ እነዚህን ዐሥራ ሁለቱን
ሐዋርያት ላካቸው፤ እንዲህም ብሎ አዘዛቸው፤
“በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፤ ወደ ሳምራው
ያን ከተማም አትግቡ። [፮]ነገር ግን ከእስራኤል
ወገን ወደ ጠፉ በጎች ሂዱ። [፯]ሄዳችሁም መን
ግሥተ ሰማያት ቀርባለች እያላችሁ አስተምሩ።
[፰]ድውያንን ፈውሱ፤ ሙታንንም አንሡ፤ ለም
ጻሞችንም አንጹ፤ አጋንንትንም አውጡ፤ ያለ
ዋጋ የተቀበላችሁትን ያለ ዋጋ ስጡ። [፱]በመቀነ
ታችሁም ወርቅ፥ ወይም ብር፥ ወይም መሐለቅ
አትያዙ። [፲]ለመንገድም ስልቻ፤ ወይም ሁለት
ልብስ፥ ወይም ጫማ፥ ወይም በትር አትያዙ፤
ለሠራተኛ ዋጋው ይገባዋልና። [፲፩]በምትገቡባ
ትም በማንኛዪቱም ከተማ፥ ወይም መንደር
በዚያ የሚገባው ማን እንደ ሆነ በጥንቃቄ መር
ምሩ፤ እስክትወጡም ድረስ በዚያ ተቀመጡ።
[፲፪]ወደ ቤትም በገባችሁ ጊዜ፥ ሰላምታ ስጡአ
ቸው። [፲፫]ለዚያ ቤት የሚገባው ቢሆን ሰላማ
ችሁ ይደርበት፤ የማይገባው ቢሆን ግን ሰላማ
ችሁ ወደ እናንተ ይመለስ። [፲፬]ከማይቀበላችሁ፥
ቃላችሁንም ከማይሰማችሁ ግን ከዚያች ቤት፥
ወይም ከዚያች ከተማ ወጥታችሁ፥ የእግራች
ሁን ትቢያ አራግፉ። [፲፭]ከዚያች ሀገር ይልቅ
በፍርድ ቀን ሰዶምና ገሞራ ዕረፍት እንደሚያ
ገኙ በእውነት እነግራችኋለሁ።

[፲፮]“እነሆ እኔ እንደ በጎች በተኵላዎች መካ
ከል እልካችኋለሁ፤ እንግዲህ እንደ እባብ ብል
ሆች፥ እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ። [፲፯]ከክፉዎች
ሰዎች ተጠበቁ፤ ወደ አደባባዮች አሳልፈው ይሰ
ጡአችኋልና፤ በምኵራቦቻቸውም ይገርፉአች
ኋልና። [፲፰]ለእነርሱና ለአሕዛብ ምስክር ትሆኑ
ዘንድ ስለ እኔ ወደ መሳፍንትና ወደ ነገሥታት
ይወስዱአችኋል። [፲፱]አሳልፈው በሰጧችሁ ጊዜ፥
እንዴት ወይም ምን እንደምትናገሩ አትጨነቁ፤
በዚያች ሰዓት የምትናገሩት ይሰጣችኋልና። [፳]የሰ
ማያዊው አባታችሁ መንፈስ እርሱ በእናንተ
ላይ አድሮ ይናገራል እንጂ የምትናገሩ እናንተ
አይደላችሁምና። [፳፩]ወንድምም ወንድሙን፥
አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፤ ልጆ
ችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ፤ ይገድሉአቸ
ዋልም። [፳፪]ስለ ስሜም በሰው ሁሉ ዘንድ የተ
ጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ ፍጻሜ የሚታገሥ
ግን እርሱ ይድናል። [፳፫]ከዚያች ከተማ ቢአሳ
ድዱአችሁ ወደ ሌላዪቱ ሽሹ፤ እውነት እላች
ኋለሁ፤ የሰው ልጅ እስኪመጣ ድረስ፥ የእስራ
ኤል ከተሞች አይፈጸሙም። [፳፬]ከመምህሩ የሚ
በልጥ ደቀ መዝሙር፥ ከጌታውም የሚበልጥ
አገልጋይ የለም። [፳፭]ደቀ መዝሙር እንደ መም
ህሩ፥ አገልጋይም እንደ ጌታው ከሆነ ይበቃ

፱፡፴፭ ማቴ. ፬፡፳፫፤ ማር. ፩፡፴፱፤ ሉቃ. ፬፡፵፬።
፱፡፴፮ ዘኍ. ፳፯፡፲፯፤ ፩ነገ. ፳፪፡፲፯፤ ፪ዜ.መ. ፲፰፡፲፮፤ ሕዝ. ፴፬፡፭፤ ዘካ. ፲፡፪፤ ማር. ፮፡፴፬።
፱፡፴፯-፴፰ ሉቃ. ፲፡፪። ፲፡፮-፲፭ ሉቃ. ፲፡ ፬-፲፪። ፲፡፲ ፩ቆሮ. ፱፡፲፬፤ ፩ጢሞ. ፭፡፲፰።
፲፡፲፬ ሐ.ሥ. ፲፫፡፶፩። ፲፡፲፭ ማቴ. ፲፩፡፳፬፤ ዘፍ. ፲፱፡፳፬-፳፰። ፲፡፲፮ ሉቃ. ፲፡፫።
፲፡፲፯-፳ ማር. ፲፫፡ ፱-፲፩፤ ሉቃ. ፲፪፡፲፩-፲፪፤ ፳፩፡፲፪-፲፭። ፲፡፳፩ ማር. ፲፫፡፲፪፤ ሉቃ. ፳፩፡፲፮።
፲፡፳፪ ማቴ. ፳፬፡፱፤ ፲፫፤ ማር. ፲፫፡፲፫፤ ሉቃ. ፳፩፡፲፯። ፲፡፳፬ ሉቃ. ፮፡፵፤ ዮሐ. ፲፫፡፲፮፤ ፲፭፡፳።
፲፡፳፭ ማቴ. ፱፡፴፬፤ ፲፪፡፳፬፤ ማር. ፫፡፳፪፤ ሉቃ. ፲፩፡፲፭።

ዋል። ባለቤቱን በሰይጣናት አለቃ ሰይጣናትን
ያወጣል ካሉት፥ ቤተ ሰቡንማ እንደ ምን ከዚህ
አብልጠው አይናገሩአቸው?
፳፮“እንግዲህ አትፍሩአቸው፤ የማይገለጥ የተ
ከደነ የለምና፤ የማይታወቅም የተሰወረ የለ
ምና። ፳፯በጨለማ የነገርሁአችሁን በብርሃን
ተናገሩት፤ በጆሮአችሁ በሹክሹክታ የነገርሁ
አችሁንም በሰገነት ላይ ስበኩት። ፳፰ሥጋችሁ
ንም የሚገድሉትን አትፍሩአቸው፤ ነፍሳችሁን
ግን ሊገድሉአት አይችሉም፤ ነገር ግን ነፍስ
ንም ሥጋንም አንድ አድርጎ በገሃነም ማጥ
ፋት የሚቻለውን እርሱን ፍሩት። ፳፱ሁለት
ወፎች በሁለት መሐለቅ ይሸጡ የለም? ከእነ
ርሱ አንዲቱ እንኳ ሰማያዊው አባታችሁ ሳያ
ውቅ በምድር ላይ አትወድቅም። ፴የእናንተስ
የራስ ጠጕራችሁ ሁሉ እንኳን የተቈጠረ ነው።
፴፩እንኪያስ አትፍሩ፤ ከብዙ ወፎች እናንት
ትበልጣላችሁና። ፴፪በሰው ፊት ለሚመሰክር
ልኝ ሁሉ፤ እኔም በሰማያት በአለው አባቴ
ፊት እመሰክርለታለሁ። ፴፫በሰው ፊት የሚ
ክደኝን ግን፥ እኔም በሰማያት ባለው አባቴ
ፊት እክደዋለሁ።
፴፬“በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመ
ጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን
ለማምጣት አልመጣሁም። ፴፭ወንድ ልጅን ከአ
ባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናቷ፥ ምራትንም ከአ
ማቷ ልለይ መጥቻለሁ። ፴፮ለሰውም ጠላቶቹ
ቤተ ሰቦቹ ይሆኑበታል። ፴፯ከእኔ ይልቅ አባ
ቱንና እናቱን የሚወድድ ለእኔ ሊሆን አይገ
ባውም፤ ከእኔም ይልቅ ወንድ ልጁንና ሴት
ልጁን የሚወድድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም።
፴፰መስቀሉንም ተሸክሞ እኔን በኋላዬ የማይከተ
ለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም። ፴፱ነፍሱን የሚ
ያገኛት ያጠፋታል፤ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያ
ጠፋት ያገኛታል።
፵“እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔ
ንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። ፵፩በነቢ
ይም ስም ነቢይን የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይቀ
በላል፤ በጻድቅም ስም ጻድቅን የሚቀበል የጻ
ድቅን ዋጋ ይቀበላል። ፵፪ከእነዚህ ከታናናሾቹ
ለአንዱ በደቀ መዝሙሬ ስም ቀዝቃዛ ጽዋ
ውኃ ብቻ የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ፤
ዋጋውን አያጣም።”

## ምዕራፍ ፲፩

### ከመጥምቁ ዮሐንስ ስለ ተላኩት መልእክተኞች

(ሉቃ. ፯፥፲፰-፴፭)

፩ጌታችን ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛ
ሙርቱን ማዘዙን ከፈጸመ በኋላ፥ ሊሰብክና
ሊያስተምር ወደ ከተሞቻቸው ሄደ። ፪ዮሐንስም
በእስር ቤት ሳለ፥ ክርስቶስ ያደረገውን ሰምቶ፥
ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ወደ እርሱ ልኮ፥
፫“የሚመጣው አንተ ነህ? ወይስ ተስፋ የምናደ
ርገው ሌላ አለ?” አለው። ፬ጌታችን ኢየሱስም
መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “ሂዳችሁ ያያችሁት
ንና የሰማችሁትን ለዮሐንስ ንገሩት። ፭ዕውሮች
ያያሉ፤ አንካሶችም ይሄዳሉ፤ ለምጻሞችም ይነ
ጻሉ፤ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፤ ሙታንም ይነ
ሣሉ፤ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል። ፮በእኔም
የማይሰናከል ሁሉ ብፁዕ ነው።”

### ጌታችን ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስን እንደ አመሰገነው

፯እነዚያም ከሄዱ በኋላ፥ ጌታችን ኢየሱስ
ስለ ዮሐንስ ለሕዝቡ እንዲህ ይላቸው ጀመረ፥
“ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጥታችኋል?
ከነፋስ የተነሣ የሚወዛወዘውን ሸንበቆ ነውን?
፰ወይስ ምን ልታዩ ወጥታችኋል? ቀጭን ልብስ
የለበሰ ሰውን ነውን? እነሆ፥ ቀጭን ልብስ የሚ
ለብሱስ በነገሥታት ቤቶች አሉ። ፱ምን ልታዩ
ወጥታችኋል? ነቢይን ነውን? አዎን፤ እሱ ከነ
ቢይ እጅግ ይበልጣል እላችኋለሁ። ፲እነሆ፥
እኔ በፊትህ መንገድህን የሚጠርግ መልእክተ
ኛዬን በአንተ ፊት እልካለሁ ተብሎ ስለ እርሱ
የተጻፈለት ይህ ነውና። ፲፩እውነት እላችኋለሁ፤
ሴቶች ከወለዱአቸው ወገን ከመጥምቁ ዮሐንስ
የሚበልጥ አልተነሣም፤ በመንግሥተ ሰማያት
ግን የሚያንሰው ይበልጠዋል። ፲፪ከመጥምቁ
ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግ
ሥተ ሰማያት ትገፋለች፤ የተገፉትም[፩] ይናጠቁ

---

፩ ግሪኩ “ግፈኞች” ይላል።

፲፥፳፮ ማር. ፬፥፳፪፤ ሉቃ. ፰፥፲፯። ፲፥፴፫ ፪ጢሞ. ፪፥፲፪። ፲፥፴፭-፴፮ ሚክ. ፯፥፮።

፲፥፴፰ ማቴ. ፲፮፥፳፬፤ ማር. ፰፥፴፬፤ ሉቃ. ፱፥፳፫።

፲፥፴፱ ማቴ. ፲፮፥፳፭፤ ማር. ፰፥፴፭፤ ሉቃ. ፱፥፳፬፤ ፲፯፥፴፫፤ ዮሐ. ፲፪፥፳፭።

፲፥፵ ማር. ፱፥፴፯፤ ሉቃ. ፱፥፵፰፤ ፲፥፲፮፤ ዮሐ. ፲፫፥፳። ፲፩፥፭ ኢሳ. ፴፭፥፭-፮፤ ፷፩፥፩። ፲፩፥፲ ሚል. ፫፥፩።

አታል። ፲፫ነቢያትም ሁሉ፥ ኦሪትም እስከ ዮሐ
ንስ ትንቢትን ተናግረዋልና። ፲፬ልትቀበሉትስ
ብትወድዱ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ
ነው። ፲፭ዦሮ ያለው መስማትን ይስማ።

፲፮"ይህቺን ትውልድ በምን እመስላታ
ለሁ? በገበያ ተቀምጠው ጓደኞቻቸውን የሚ
ጠሩ ልጆችን ትመስላለች። ፲፯እንዲህም ይሏቸ
ዋል፡- እንቢልታ እየነፋን አቀነቀንላችሁ አልዘ
ፈናችሁም፤ ሙሾም አወጣንላችሁ አላለቀሳች
ሁም። ፲፰ዮሐንስ ሳይበላና ሳይጠጣ መጣ፤ እነ
ርሱ ግን ጋኔን አለበት አሉት። ፲፱የሰው ልጅ
እየበላና እየጠጣ መጣ፤ እነርሱም እነሆ፥ የሚ
በላና የወይን ጠጅ የሚጠጣ፥ የቀራጮችና የኃ
ጥአን ወዳጅ ነው አሉት፤ ጥበብም ከልጆችዋ
የተነሣ ጸደቀች።"

## ያላመኑትን ከተሞች እንደ ነቀፋቸው

፳ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ብዙ ተአ
ምራት ያደረገባቸውን ከተሞች ንስሓ ስላል
ገቡ ይነቅፋቸው ጀመር፤ እንዲህም አላቸው።
፳፩"ኮራዚ ወዮልሽ፤ ቤተ ሳይዳ ወዮልሽ፤ በእ
ናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና
ተደርጎ ቢሆን ማቅ ለብሰው፥ አመድም ነስን
ሰው አስቀድመው ንስሓ በገቡ ነበር። ፳፪ነገር
ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ
ጢሮስና ሲዶና ዕረፍትን ያገኛሉ። ፳፫ቅፍርናሆም!
አንቺም እስከ ሰማይ ከፍ ከፍ ብትዪ
እስከ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺም የተደረ
ገው ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን እስከ
ዛሬ በኖረች ነበር። ፳፬ነገር ግን እልሻለሁ፥ በፍ
ርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ የሰዶም ምድር ዕረፍ
ትን ታገኛለች።"

፳፭ያንጊዜም ጌታችን ኢየሱስ መልሶ እንዲህ
አለ፤ "የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፥
ይህን ምሥጢር ከጥበበኞችና ከዐዋቆች ሰውረህ
ለሕፃናት ገልጸኸዋልና አመሰግንሃለሁ። ፳፮አዎን
አባት ሆይ፥ ፈቃድህ በፊትህ እንዲሁ ሆኖአ
ልና። ፳፯ሁሉም ከአባቴ ዘንድ ተሰጠኝ፤ ከአብ
በቀር ወልድን የሚያውቀው የለም፤ አብንም
ከወልድ በቀር፥ ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈ
ቅደው በቀር የሚያውቀው የለም። ፳፰እናንተ
ደካሞች፥ ሸክማችሁም የከበደ ሁሉ ወደ እኔ
ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ፳፱ቀንበሬን በላያ
ችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ
ነኝና፤ ልቤም ትሑት ነውና፥ ለነፍሳችሁም
ዕረፍትን ታገኛላችሁ። ፴ቀንበሬ ልዝብ፥ ሸክ
ሜም ቀላል ነውና።"

# ምዕራፍ ፲፪

## ስለ ሰንበትና ስለ አከባበርዋ

(ማር. ፪፥፳፫-፳፰፤ ሉቃ. ፮፥፩-፭)

፩በዚያም ወራት ጌታችን ኢየሱስ በሰንበት
በእርሻ መካከል ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም ተር
በው ነበርና እሸት እየቈረጡ ይበሉ ጀመር።
፪ፈሪሳውያንም አይተው፥ "እነሆ፥ ደቀ መዛ
ሙርትህ በሰንበት ሊደረግ የማይገባውን ሲያደ
ርጉ እይ" አሉት። ፫እርሱም አላቸው፥ "እርሱ
በተራበ ጊዜ፥ ከእርሱም ጋር የነበሩት በተራቡ
ጊዜ ዳዊት ያደረገውን፥ ፬ወደ እግዚአብሔር
ቤት እንደ ገባ፥ ከካህናትም ብቻ በቀር እርሱ
ሊበላው የማይገባውን፥ ከእርሱም ጋር የነበ
ሩት ሊበሉት የማይገባቸውን የመሥዋዕቱን ኅብ
ስት እንደ በላ አላነበባችሁምን? ፭በቤተ መቅ
ደስ የሚያገለግሉ ካህናት ሰንበትን እንደሚሽሩ
አት፥ በደልም እንደማይሆንባቸው በኦሪት ያለ
ውን አላነበባችሁምን? ፮እኔም ከቤተ መቅደስ
የሚበልጥ እዚህ እንዳለ እላችኋለሁ። ፯ከመሥዋ
ዕት ይልቅ ምሕረትን እመርጣለሁ ያለው ምን
እንደ ሆነ ብታውቁስ ኖሮ ያልበደሉትን ባልፈ
ረዳችሁባቸው ነበር። ፰የሰንበት ጌታዋ የሰው
ልጅ ነውና።"

## እጁ ደርቃ ስለ ነበረችው ሰው

(ማር. ፫፥፩-፮፤ ሉቃ. ፮፥፮-፲፩)

፱ጌታችን ኢየሱስም ከዚያ ዐልፎ ወደ ምኵ
ራባቸው ገባ። ፲እነሆ፥ እጁ የሰለለች ሰው
ነበር፤ ይከሱት ዘንድ፥ "በሰንበት መፈወስ
ይገባልን?" ብለው ጠየቁት። ፲፩እርሱም አላ
ቸው፥ "ከእናንተ መካከል አንድ በግ ያለው

---

፲፩፥፲፪-፲፫ ሉቃ. ፲፮፥፲፮። ፲፩፥፲፬ ሚል. ፬፥፭፤ ማቴ. ፲፯፥፲-፲፫፤ ማር. ፱፥፲፩-፲፫። ፲፩፥፳ ሉቃ. ፲፥፲፫-፲፭።
፲፩፥፳፩ ኢሳ. ፳፫፥፩-፲፰፤ ሕዝ. ፳፮፥፩-፳፰፤ ፳፯፤ ኢዩ. ፫፥፬-፰፤ አሞጽ ፩፥፱-፲፤ ዘካ. ፱፥፪-፬።
፲፩፥፳፫ ኢሳ. ፲፬፥፲፫-፲፭፤ ዘፍ. ፲፱፥፳፬-፳፰። ፲፩፥፳፬ ማቴ. ፲፥፲፭፤ ሉቃ. ፲፥፲፪። ፲፩፥፳፭ ሉቃ. ፲፥፳፩-፳፪።
፲፩፥፳፯ ዮሐ. ፫፥፴፭፤ ፩፥፲፰፤ ፲፥፭። ፲፩፥፳፱ ኤር. ፮፥፲፮። ፲፪፥፩ ዘዳ. ፳፫፥፳፭።
፲፪፥፫-፬ ፩ሳሙ. ፳፩፥፩-፯። ፲፪፥፬ ዘሌ. ፳፬፥፱። ፲፪፥፭ ዘኁ. ፳፰፥፱-፲። ፲፪፥፯ ማቴ. ፱፥፲፫፤ ሆሴዕ ፮፥፮።
፲፪፥፲፩ ሉቃ. ፲፬፥፭።

በሰንበትም ወደ ጕድጓድ ውስጥ ቢወድቅበት
ይዞ የማያወጣው ማነው? ፲፪እንግዲያማ ከበግ
ይልቅ ሰው እንደ ምን አይበልጥም! እንኪያስ
በሰንበት መልካም ማድረግ ይገባል።” ፲፫ከዚ
ያም በኋላ ያን ሰው “እጅህን ዘርጋ” አለው፤
እጁንም ዘረጋት፤ ያንጊዜም ድና እንደ ሁለ
ተኛዋ ሆነች። ፲፬ፈሪሳውያንም ወጥተው ሊገድ
ሉት ስለ እርሱ ተማከሩ።

### ብዙ ሰዎችን ስለ ማዳኑ

፲፭ጌታችን ኢየሱስም ባወቀ ጊዜ ከዚያ ሄደ፤
ብዙ ሰዎችም ተከተሉት፤ ሁሉንም አዳና
ቸው። ፲፮እንዳይገልጡትም አዘዛቸው። ፲፯በነቢዩ
በኢሳይያስ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ፥ እንዲህ
ሲል። ፲፰“እነሆ፥ የመረጥሁት ልጄ፥ ነፍሴ የወ
ደደችው፥ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፤
እርሱ ለአሕዛብ ፍርድን ይናገራል፤ ፲፱አይከራ
ከርም፤ አይጮኽም፤ በአደባባይም ቃሉን የሚ
ሰማ የለም። ፳ያሸናፊነቱን ፍርድ እስኪያመጣ
ድረስ የተቀጠቀጠ መቃን አይሰብርም፤ የሚ
ጤስ የጧፍ ኩስታሪንም አያጠፋም። ፳፩አሕዛ
ብም በስሙ ተስፋ ያደርጋሉ።”

### ጋኔን ስለ አደረበት ዕውር፥ ዲዳ፥ ደንቆሮ
(ማር. ፫፥፳-፴፤ ሉቃ. ፲፩፥፲፬-፳፫)

፳፪ከዚህ በኋላ ጋኔን ያደረበትን ዕውርና ደን
ቆሮ አመጡለት፤ ያም ዕውር፥ ደንቆሮ እስኪና
ገር፥ እስኪያይም ድረስ ፈወሰው። ፳፫ሕዝቡም
ሁሉ እየተደነቁ፥ “ይህ የዳዊት ልጅ አይደለ
ምንን?”፩ አሉ። ፳፬ፈሪሳውያን ግን በሰሙ ጊዜ
“በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል ነው እንጂ
ይህስ አጋንንትን አያወጣም” አሉ። ፳፭ጌታ
ችን ኢየሱስም ዐሳባቸውን ዐውቆ እንዲህ አላ
ቸው፥ “እርስ በርስዋ የምትለያይ መንግሥት
ሁላ ትጠፋለች፤ ከተማም ሁላ፥ ቤትም እርስ
በርስዋ የምትለያይ ከሆነች አትጸናም። ፳፮ሰይጣ
ንም ሰይጣንን የሚያወጣው ከሆነ እርስ በርሱ
ተለያየ፤ እንግዲህ መንግሥቱ እንዴት ትጸና
ለች? ፳፯እኔስ፥ በብዔል ዜቡል አጋንንትን የማ
ወጣ ከሆንሁ ልጆቻችሁ በምን ያወጡአቸዋል?
ስለዚህ እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባችኋል። ፳፰እኔ
በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ
ከሆንሁ ግን፥ እንግዲያስ የእግዚአብሔር መን
ግሥት አሁን ወደ እናንተ ደርሳለች። ፳፱ኀይለ
ኛን አስቀድሞ ካላሰረ በስተቀር ወደ ኀይለኛ
ቤት ለመግባት፥ ገንዘቡንም ለመበርበር የሚ
ችል ማንም የለም፤ ከዚህም በኋላ ቤቱን ይበ
ረብራል። ፴ከእኔ ጋር ያልሆነ ባለጋራዬ ነው፤
ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ይበትናል። ፴፩ስለዚህ
እላችኋለሁ፡- ለሰው ኀጢአትና ስድብ ሁሉ
ይሰረያል፤ መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ ግን አይ
ሰረይለትም። ፴፪በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚና
ገር ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚና
ገር ግን በዚህ ዓለምም ቢሆን፥ በሚመጣውም
ዓለም ቢሆን አይሰረይለትም።

፴፫“ወይም ዛፉን መልካም፥ ፍሬውንም
መልካም አድርጉ፤ ወይም ዛፉን ክፉ፥ ፍሬ
ውንም ክፉ አድርጉ፤ ዛፍ በፍሬው ይታወ
ቃልና። ፴፬የእባብ ልጆች ሆይ፥ እናንተ ክፉ
ዎች ስትሆኑ መልካም መናገርን እንዴት ትች
ላላችሁ? ከልብ የተረፈውን አፍ ይናገራልና።
፴፭ደግ ሰው ከመልካም ልቡ መዝገብ መልካም
ነገርን ያወጣል፤ ክፉ ሰው ግን ከክፉ ልቡ
መዝገብ ክፉ ነገርን ያወጣል። ፴፮እኔ ግን እላ
ችኋለሁ፡- ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር
ሁሉ በፍርድ ቀን ስለ እርሱ መልስ ይሰጡበ
ታል። ፴፯ከአነጋገርህ የተነሣ ትጸድቃለህ፤ ከአነ
ጋገርህም የተነሣ ይፈረድብሃልና።”

### ምልክት ስለ ጠየቁ ሰዎች
(ማር. ፰፥፲፩-፲፪፤ ሉቃ. ፲፩፥፳፱)

፴፰ያንጊዜም ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ወገን
ሰዎች መጥተው፤ “መምህር ሆይ፥ ከአንተ
ምልክት ልናይ እንወዳለን” አሉት። ፴፱ጌታ
ችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “ዐመ
ፀኞዪቱና፤ አመንዝራዪቱ ትውልድ ምልክትን
ትሻለች፤ ምልክት ግን ከነቢዩ ከዮናስ ምል
ክት በቀር አይሰጣትም። ፵ዮናስ ሦስት መዓ
ልትና ሦስት ሌሊት በዓሣ አንበሪ ሆድ እንደ
ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ ሦስት መዓልትና
ሦስት ሌሊት በምድር ልብ ውስጥ ይኖራልና።
፵፩የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ተነሥተው ይህ

---

፩ ግሪኩ “እንጃ ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆን?” ይላል።

፲፪፥፲፰-፳፩ ኢሳ. ፵፪፥፩-፬። ፲፪፥፳፬ ማቴ. ፱፥፴፬፤ ፲፥፳፭። ፲፪፥፴ ማር. ፱፥፵። ፲፪፥፴፪ ሉቃ. ፲፪፥፲። ፲፪፥፴፫ ማቴ. ፯፥፳፤ ሉቃ. ፮፥፵፬። ፲፪፥፴፬ ማቴ. ፫፥፯፤ ፳፫፥፴፫፤ ፲፭፥፲፰፤ ሉቃ. ፫፥፯፤ ፮፥፵፭። ፲፪፥፴፰ ማቴ. ፲፮፥፩፤ ማር. ፰፥፲፩፤ ሉቃ. ፲፩፥፲፮። ፲፪፥፴፱ ማቴ. ፲፮፥፬፤ ማር. ፰፥፲፪። ፲፪፥፵ ዮናስ ፩፥፲፯። ፲፪፥፵፩ ዮናስ ፫፥፭።

ችን ትውልድ ይፋረዱአታል፤ በዮናስ ስብ
ከት ንስሓ ገብተዋልና፤ እነሆ፥ ከዮናስ የሚ
በልጥ በዚህ አለ። ፵፪ንግሥተ አዜብ በፍርድ
ቀን ተነሥታ ከዚች ትውልድ ጋር ትፋረዳ
ለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ ከምድር
ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ፥ ከሰሎሞን የሚበ
ልጥ በዚህ አለ።

፵፫“ርኩስ መንፈስም ከሰው ከወጣ በኋላ፥
ዕረፍት ሲሻ ውኃ ወደሌለበት ምድረ በዳ ይዞ
ራል፤ አያገኝምም። ፵፬ከዚህም በኋላ፥ እንግዲ
ህስ ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤
በመጣም ጊዜ ባዶ ሆኖ፥ ተጠርጎና ተለስኖ ያገ
ኘዋል። ፵፭ከዚህም በኋላ ይሄዳል፤ ከእርሱም
የሚከፉ ሌሎች ሰባት አጋንንትን ያመጣል፤
ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው የኋላ
ኑሮው ከፊተኛው የከፋ ይሆናል፤ ለዚችም ክፉ
ትውልድ እንዲሁ ይሆንባታል።”

፵፮ለሕዝቡም ይህን ሲነግራቸው፥ እነሆ፥ እና
ቱና ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው በውጭ
ቆመው ነበር። ፵፯ከደቀ መዛሙርቱም አንዱ
መጥቶ፥ “እነሆ፥ እናትህና ወንድሞችህ ከውጭ
ቆመዋል፤ ሊያነጋግሩህም ይሻሉ” አለው።
፵፰እርሱ ግን ለነገረው መልሶ፥ “እናቴ ማን
ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?” አለው።
፵፱እጁንም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ፥
“እነሆ፥ እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው።
፶በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ
ሁሉ እርሱ ወንድሜ፥ እኅቴ፥ እናቴም ነውና”
አለ።

## ምዕራፍ ፲፫

### ስለ ዘርና ስለ ዘሪው ምሳሌ

(ማር. ፬፥፩-፱፤ ሉቃ. ፰፥፬-፰)

፩በዚያችም ቀን ጌታችን ኢየሱስ ከቤት
ወጥቶ በባሕሩ አጠገብ ተቀመጠ። ፪ወደ ታን
ኳም ወጥቶ እስኪቀመጥ ድረስ ብዙ ሰዎች
ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፤ ሕዝቡም ሁሉ በወደቡ
ቆመው ነበሩ። ፫እንዲህ እያለም በምሳሌ ብዙ
ነገርን ነገራቸው፤ “እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ።
፬ሲዘራም በመንገድ የወደቀ ዘር ነበረ፤ የሰማይ
ወፎችም መጥተው በሉት። ፭ብዙ አፈር በሌለ
በት ጭንጫ ላይ የወደቀ ዘርም ነበረ፤ ለመሬ
ቱም ጥልቀት አልነበረውምና ወዲያውኑ በቀለ።
፮ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፤ ሥርም አልነ
በረውምና ደረቀ። ፯በእሾኽ መካከልም የወደቀ
ዘር ነበረ፤ በበቀለም ጊዜ እሾኽ አነቀው፤ አጣ
በቀውም። ፰በመልካም ምድር ላይም የወደቀ
ዘር ነበረ፤ ፍሬም ሰጠ፤ መቶ ያፈራ ነበረ፤
ስድሳም ያፈራ ነበረ፤ ሠላሳም ያፈራ ነበረ።
፱ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ።”

፲ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው “ስለምን በም
ሳሌ ትነግራቸዋለህ?” አሉት። ፲፩ጌታችን ኢየ
ሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ “ለእናንተ
የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰ
ጥቶአችኋል፤ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም።
፲፪ላለው ይሰጡታል፤ ይጨምሩለታልም፤ የሌ
ለውን ግን ያንኑ ያለውን ቅሉ ይወስዱበታል።
፲፫ስለዚህም እያዩ ስለማያዩ፥ እየሰሙም ስለማ
ይሰሙ፥ ስለማያስተውሉም በምሳሌ እነግራቸ
ዋለሁ። ፲፬መስማትን ትሰማላችሁ፤ ልብ አታደ
ርጉም፤ ማየትንም ታያላችሁ፤ አትመለከቱም።
፲፭በዐይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳ
ይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ ተመ
ልሰውም እንዳልፈውሳቸው የዚህ ሕዝብ ልቡ
ደንድኖአልና፥ ጆሮአቸውም ደንቍሮአል፤ ዐይ
ናቸውንም ጨፍነዋል የሚል የኢሳይያስ ትን
ቢት በእነርሱ ይፈጸም ዘንድ። ፲፮የእናንተ ግን
ዐይኖቻችሁ ያያሉና፥ ጆሮዎቻችሁም ይሰማ
ሉና ብፁዓት ናቸው። ፲፯እውነት እላችኋለሁ
ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን እናንተ የምታዩትን
ሊያዩ ተመኝተው አላዩም፤ እናንተ የምትሰሙ
ትንም ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም።

፲፰“እንግዲህ እናንተ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ።
፲፱የመንግሥተ ሰማያትን ቃል ሰምቶ የማያስተ
ውል ሁሉ፥ ክፉው መጥቶ በልቡ የተዘራውን
ቃል ይነጥቀዋል፤ በመንገድ የተዘራው ዘር
ይህ ነው። ፳በጭንጫ ላይ የተዘራውም ቃሉን
የሚሰማና ፈጥኖ በደስታ የሚቀበለው ነው።
፳፩ነገር ግን፥ ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ላይ
ሥር የለውም፤ በቃሉም ምክንያት መከራ፥
ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይክዳል።
፳፪በእሾኽ መካከል የተዘራውም ቃሉን ሰምቶ
የዚህ ዓለም አሳብና የሀብት ማታለል ቃሉን

---

፲፪፥፵፪ ፩ነገ. ፲፥ ፩-፲፤ ፪ዜመ. ፱፥፩-፲፪። ፲፪፥፵፫ ሉቃ. ፲፩፥፳፬-፳፮።
፲፪፥፵፮ ማር. ፫፥፴፩-፴፭፤ ሉቃ. ፰፥፲፱-፳፩። ፲፫፥፪ ሉቃ. ፭፥፩-፫።
፲፫፥፲፪ ማቴ. ፳፭፥፳፱፤ ማር. ፬፥፳፭፤ ሉቃ. ፰፥፲፰፤ ፲፱፥፳፮። ፲፫፥፲፬-፲፭ ኢሳ. ፮፥፱-፲።
፲፫፥፲፮-፲፯ ሉቃ. ፲፥፳፫-፳፬።

አንቆት ያለ ፍሬ የሚቀረው ነው። ፳፫ነገር ግን
በመልካም ምድር ላይ የተዘራው ይህ ቃሉን
የሚሰማና የሚያስተውል ነው፤ እርሱም አንዱ
መቶ፥ ሌላውም ስድሳ፥ ሌላውም ሠላሳ ፍሬ
ይሰጣል።”

### ስለ ስንዴና እንክርዳድ ምሳሌ

፳፬ሌላ ምሳሌም እንዲህ ሲል መሰለላቸው፤
“መንግሥተ ሰማያት በእርሻው ላይ መልካም
ዘርን የዘራ ሰውን ትመስላለች። ፳፭ቤተሰቦቹም
ተኝተው ሳለ፥ ጠላት መጥቶ በስንዴው መካ
ከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ። ፳፮ስንዴውም በበቀ
ለና በአፈራ ጊዜ፥ ወዲያውኑ እንክርዳዱ ታየ።
፳፯የባለ እርሻው አገልጋዮችም መጥተው አቤቱ
በእርሻህ መልካም ዘር ዘርተህ አልነበረምን?
እንግዲህ እንክርዳዱ ከየት መጣ? አሉት።
፳፰እርሱም ጠላት ሰው ይህን አደረገ አላቸው፤
አገልጋዮቹ ግን፦ እንግዲህ ሂደን ልናርመው
ትወዳለህን? አሉት። ፳፱እንክርዳዱን ስታርሙ
ስንዴውንም ጨምራችሁ እንዳትነቅሉ አይሆ
ንም፤ ፴ተውአቸው እስከ መከር ድረስ አብረው
ይደጉ፤ በመከርም ጊዜ አጫጆችን አስቀድማ
ችሁ እንክርዳዱን ልቀሙ፤ በየነዶውም አስራ
ችሁ በእሳት አቃጥሉት፤ ስንዴውን ግን በጎተ
ራዬ ሰብስቡት እላቸዋለሁ” አለ።

### ስለ ሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ
(ማር. ፬፥፴-፴፪፤ ሉቃ. ፲፫፥፲፰-፲፱)

፴፩ሌላም ምሳሌ እንዲህ ብሎ መሰለላቸው፤
“መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው
ላይ የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች።
፴፪እርስዋም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፤ በአደገች
ጊዜ ግን ከአታክልት ሁሉ ትበልጣለች፤ የሰ
ማይ ወፎችም መጥተው ከቅርንጫፎችዋ በታች
እስኪያርፉ ድረስ ታላቅ ዛፍ ትሆናለች።”

### ስለ እርሾ ምሳሌ
(ሉቃ. ፲፫፥፳-፳፩)

፴፫ሌላ ምሳሌንም ነገራቸው፤ እንዲህም አለ፥
“መንግሥተ ሰማያት ሴት ወስዳ በሦስት መስ
ፈሪያ ዱቄት የለወሰችውን፥ ሁሉንም እንዲ
ቦካ ያደረገውን እርሾ ትመስላለች።” ፴፬ጌታ
ችን ኢየሱስም ይህን ሁሉ ለሕዝቡ በምሳሌ
ነገራቸው፤ ያለ ምሳሌ ግን አልነገራቸውም።
፴፭በነቢይ “አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤ ከጥ
ንት የተነገረውንም ምሳሌ እናገራለሁ” የተባ
ለው ይፈጸም ዘንድ።

### ስለ እንክርዳዱና ስለ ስንዴው፥ ስለ እርሻውም ትርጓሜ

፴፮ከዚህም በኋላ ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት
ገባ፤ ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው
“የእርሻውን እንክርዳድ ምሳሌ ተርጕምልን”
አሉት። ፴፯እርሱም መልሶ አላቸው፤ “መል
ካም ዘርን የዘራ የሰው ልጅ ነው። ፴፰እርሻ
ውም ዓለም ነው፤ መልካሙም ዘር የመንግ
ሥት ልጆች ናቸው፤ እንክርዳዱም የክፉው
ልጆች ናቸው። ፴፱የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ
ነው፤ መከሩም የዓለም ፍጻሜ ነው፤ አጫጆ
ቹም መላእክት ናቸው። ፵እንግዲህ አስቀድሞ
እንክርዳዱን እንደሚለቅሙት፥ በእሳትም እን
ደሚያቃጥሉት በዚህ ዓለም ፍጻሜም እንዲሁ
ይሆናል። ፵፩የሰው ልጅም መላእክቱን ይልካል፤
ከመንግሥቱም ዐላውያንንና በደልን የሚያደር
ጉትን ሁሉ ይሰበስባሉ። ፵፪ወደ እሳት ጕድጓ
ድም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያም ልቅሶና ጥርስ
ማፋጨት ይሆናል። ፵፫ያንጊዜም ጻድቃን በአባ
ታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ፤ ጆሮ
ያለው መስማትን ይስማ።

### ስለ ተቀበረው ወርቅ፥ ስለ ዕንቍና ስለ መረብ ምሳሌ

፵፬“ዳግመኛም መንግሥተ ሰማያት በእርሻ
ውስጥ የተቀበረች ወርቅን ትመስላለች፤ ሰውም
አግኝቶ ሰወራት፤ ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለ
ውን ሁሉ ሸጠና ያችን እርሻ ገዛት።
፵፭“ዳግመኛም መንግሥተ ሰማያት ክቡር
ዕንቍን የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች። ፵፮ዋጋ
ዋም ብዙ የሆነ አንዲት ዕንቍን በአገኘ ጊዜ
ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ገዛት። ፵፯ዳግመኛም
መንግሥተ ሰማያት በባሕር ውስጥ የተጣለች
ውን፥ የዓሣ ወገንን ሁሉ የሰበሰበችውን መረብ
ትመስላለች። ፵፰በሞላችም ጊዜ ወደ ዳር አወ
ጡአት፤ ተቀምጠውም መልካም መልካሙን
መርጠው ወደ ሣጥናቸው ጨመሩ፤ መጥፎ
ውን ግን ወደ ውጭ ጣሉት። ፵፱በዓለም ፍጻ
ሜም እንዲሁ ይሆናል፤ መላእክት ይመጣሉ፤
ኃጥአንንም ከጻድቃን መካከል ይለያሉ። ፶ልቅ
ሶና ጥርስ ማፋጨት ወደ አለበት ወደ እሳት
ጕድጓድም ይጥሉአቸዋል።”

---

፲፫፥፴፭ መዝ. ፸፰፥፪።

፶፩ጌታችን ኢየሱስም፥ “እንግዲህ ይህን ሁሉ
አስተዋላችሁን?” አላቸው፤ እነርሱም፥ “አዎ፥
ጌታ ሆይ፥” አሉት። ፶፪እርሱም፥ “ስለዚህ
ለመንግሥተ ሰማያት የሚያገለግል ጸሓፊ ሁሉ
ከሣጥኑ አሮጌውንና ሐዲሱን የሚያወጣ ባለጸጋ
ሰውን ይመስላል” አላቸው።
፶፫ጌታችን ኢየሱስም እነዚህን ምሳሌዎች በፈ
ጸመ ጊዜ ከዚያ ሄደ። ፶፬ወደ ሀገሩም መጣ፤
እስኪደነቁ ድረስም በምኵራባቸው አስተማራ
ቸው፤ እንዲህም ይሉ ነበር፤ “እንግዲህ ይህ
ሁሉ ጥበብና ተአምር ከየት ተሰጠው? ፶፭ይህ
የጠራቢው የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? የእናቱ
ስምስ ማርያም አይደለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆ
ብና ዮሳ፥ ስምዖንም፥ ይሁዳም አይደሉምን?
፶፮እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደለምን?
እንግዲህ ይህ ሁሉ ጥበብና ተአምር ከየት ተሰ
ጠው?” እያሉ ስለ እርሱ ያንጐራጕሩ ጀመር።
፶፯ጌታችን ኢየሱስ ግን “ነቢይ በሀገሩና በወገኑ
እንጂ፥ በሌላ የማይከብርበት የለም” አላቸው።
፶፰ባለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአ
ምራትን አላደረገም።

## ምዕራፍ ፲፬

### ስለ ሄሮድስና ስለ መጥምቁ ዮሐንስ

(ማር. ፮፥፲፬-፳፱፤ ሉቃ. ፱፥፯-፱)

፩በዚያ ወራትም የገሊላው ንጉሥ ሄሮድስ
የጌታችን የኢየሱስን ዝና ሰማ። ፪ሎሌዎቹንም፥
“ይህ መጥምቁ ዮሐንስ ነው፤ እርሱ ከሙታን
ተለይቶ ተነሥቶአል፤ ስለዚህ በእርሱ ተአም
ራት ይደረጋል” አላቸው። ፫እርሱ ሄሮድስ
በወንድሙ በፊልጶስ ሚስት በሄሮድያዳ ምክን
ያት፥ ዮሐንስን አሲዞ በእስር ቤት አግዞት ነበ
ርና። ፬ዮሐንስም “እርስዋ ለአንተ ትሆን ዘንድ
አይገባህም” ይለው ነበር። ፭ሊገድለውም ወዶ
ሳለ ሕዝቡን ይፈራቸው ነበር፤ ዮሐንስን እንደ
ነቢይ ያዩት ነበርና። ፮የሄሮድስም የልደቱ ቀን
በሆነ ጊዜ የሄሮድያዳ ልጅ በመካከላቸው ዘፈ
ነችለት፤ ሄሮድስንም ደስ አሰኘችው። ፯ስለዚ
ህም የምትለምነውን ሁሉ ሊሰጣት ማለላት።
፰እርስዋ ግን አስቀድማ በእናቷ ዘንድ ዐውቃ
ነበርና “የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ አሁን በወ
ጭት ስጠኝ” አለችው። ፱ንጉሡም አዘነ፥ ነገር
ግን ስለ መሐላው፥ አብረውት በማዕዱ ተቀ
ምጠው ስላሉት ሰዎች ይሰጧት ዘንድ አዘዘ።
፲ልኮም በግዞት በእስር ቤት ሳለ የዮሐንስን ራስ
አስቈረጠው። ፲፩ራሱንም በወጭት አምጥተው
ለዚያች ብላቴና ሰጡአት፤ እርስዋም ወስዳ ለእ
ናቷ ሰጠች። ፲፪ደቀ መዛሙርቱም መጡ፤ በድ
ኑንም ወስደው ቀበሩት፤ መጥተውም ለጌታ
ለኢየሱስ ነገሩት።

### ስለ አምስቱ እንጀራና ስለ ሁለቱ ዓሣዎች

፲፫ጌታችን ኢየሱስም ይህን በሰማ ጊዜ በታ
ንኳ ሆኖ ከዚያ ብቻውን ወደ ምድረ በዳ ሄደ፤
ሕዝቡም ሰምተው ከየመንደሩ በእግር ተከተ
ሉት። ፲፬በወጣም ጊዜ ብዙ ሰዎችን አይቶ
አዘነላቸው፤ ድውዮቻቸውንም አዳነላቸው።
፲፭በመሸ ጊዜም ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ
ቀርበው፥ “ቦታው ምድረ በዳ ነው፤ ሰዓቱም
አልፎአል፤ ወደ መንደር ገብተው ምግባቸውን
ይገዙ ዘንድ ሕዝቡን አሰናብታቸው” አሉት።
፲፮ጌታችን ኢየሱስም፥ “እንደ ራባቸው ሊሄዱ
አይገባም፤ እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው
እንጂ” አላቸው። ፲፯እነርሱም “ከሁለት ዓሣና
ከአምስት እንጀራ በቀር፥ በዚህ ምንም የለ
ንም” አሉት። ፲፰እርሱም “እነዚያን ወደዚህ
አምጡልኝ” አላቸው። ፲፱በመስኩም ላይ እን
ዲቀመጡ ሰዎችን አዘዘ፤ አምስቱን እንጀራና
ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ ተመለከተና ባርኮ
ቈርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው፤ ደቀ መዛ
ሙርቱም ለሕዝቡ አቀረቡ። ፳ሁሉም በልተው
ጠገቡ፤ የተረፈውንም ቍርስራሽ ዐሥራ ሁለት
መሶብ ሙሉ አነሡ። ፳፩የበሉትም፥ ከሴቶችና
ከልጆች በቀር ወንዶቹ አምስት ሺህ ያህሉ
ነበር።

### ጌታችን ኢየሱስ በባሕር ላይ እንደ ሄደ

፳፪ያንጊዜም ሕዝቡን እስኪያሰናብት ድረስ
ደቀ መዛሙርቱ በታንኳው ገብተው ወደ ባሕር
ማዶ ቀድመውት ይሄዱ ዘንድ ግድ አላቸው።
፳፫ከዚያም በኋላ ሕዝቡን አሰናብቶ ሊጸልይ
ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ፤ በመሸም ጊዜ ብቻ
ውን በዚያው ነበር። ፳፬ታንኳው ግን እነሆ፥
በባሕር መካከል ነበር፤ ከማዕበሉም የተነሣ
ይታወክ ነበር፤ ነፋስ ከፊቱ ነበርና። ፳፭ከሌሊ

፲፫፥፶፫ ማር. ፮፥፩-፮፤ ሉቃ. ፬፥፲፮-፴። ፲፫፥፶፯ ዮሐ. ፬፥፵፬። ፲፬፥፫-፬ ሉቃ. ፫፥፲፱-፳።
፲፬፥፬ ዘሌ. ፲፰፥፲፮፤ ፳፥፳፩። ፲፬፥፲፫ ማር. ፮፥፴-፵፬፤ ዮሐ. ፮፥፩-፲፬።
፲፬፥፳፪ ማር. ፮፥፵፭-፶፪፤ ዮሐ. ፮፥፲፭-፳፩።

ቱም በአራተኛዪቱ ክፍለ ሰዓት ጌታችን ኢየ
ሱስ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ።
፳፮ደቀ መዛሙርቱም በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት
ጊዜ፥ "ምትሐት ነው" ብለው ደነገጡ፤ ከፍ
ርሀትም የተነሣ ጮኹ። ፳፯ወዲያውም ጌታችን
ኢየሱስ፥ "አይዞአችሁ፥እኔ ነኝ አትፍሩ" አላ
ቸው። ፳፰ጴጥሮስም መልሶ፥ "አቤቱ፥ አንተስ
ከሆንህ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘ
ዘኝ" አለው፤ ፳፱እርሱም፥ "ና" አለው። ጴጥ
ሮስም ከታንኳው ወርዶ ወደ ጌታችን ኢየሱስ
ሊደርስ በውኃው ላይ ሄደ። ፴ነገር ግን ነፋሱ
በርትቶ ባየ ጊዜ ፈራ፤ ሊሰጥምም ጀመረ፥ ያን
ጊዜም "አቤቱ፥ አድነኝ" ብሎ ጮኸ ፴፩ወዲ
ያው ጌታችን ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና፥
"አንተ እምነት የጐደለህ ለምን ተጠራጠርህ?"
አለው። ፴፪ወደ ታንኳውም በወጣ ጊዜ ወዲያ
ውኑ ነፋሱ ፀጥ አለ። ፴፫በታንኳውም ውስጥ
የነበሩት ሁሉ "በእውነት አንተ የእግዚአብሔር
ልጅ ነህ" እያሉ ሰገዱለት። ፴፬ባሕሩንም ተሻ
ግረው ወደ ጌንሴሬጥ ምድር ደረሱ። ፴፭የዚያ
ሀገር ሰዎችም ዐወቁት፤ ወደ አውራጃዎቻቸ
ውም ሁሉ ላኩ፤ በሽተኞችንም ሁሉ አመጡ
ለት። ፴፮የልብሱንም ዘርፍ ይዳስሱ ዘንድ ለመ
ኑት፤ የዳሰሱትም ሁሉ ይድኑ ነበር።

## ምዕራፍ ፲፭

### የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለሚተዉ
(ማር. ፯፥፩-፲፫)

፩ከዚህ በኋላ ከኢየሩሳሌም የመጡ ጻፎችና
ፈሪሳውያን ወደ ጌታችን ኢየሱስ ቀርበው እን
ዲህ አሉ፦ ፪"ደቀ መዛሙርትህ የሽማግሌዎ
ችን ሥርዐት ለምን ይተላለፋሉ? እንጀራ በሚ
በሉበት ጊዜ እጃቸውን አይታጠቡምና።" ፫እር
ሱም መልሶ እንዲህ አላቸው "እናንተስ ስለ
ወጋችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለምን ትተላ
ለፋላችሁ? ፬እግዚአብሔርስ 'አባትህንና እናት
ህን አክብር፤ በአባቱና በእናቱ ላይ ክፉ ቃልን
የተናገረ ፈጽሞ ይሙት' ብሏል። ፭እናንተ ግን
አባቱን ወይም እናቱን ከእኔ የምትጠቀምበት
መባ ነው የሚል ሁሉ አባቱን ወይም እናቱን
አያከብርም ትላላችሁ። ፮ስለ ወጋችሁም የእግ
ዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ። ፯እናንተ ግብዞች፥
ኢሳይያስ በእናንተ ላይ እንዲህ ሲል መልካም
ተናገረ፦ ፰'ይህ ሕዝብ በከንፈራቸው ያከብሩ
ኛል፤ በልባቸው ግን ከእኔ እጅግ ይርቃሉ።'
፱የሰው ወግ የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከ
ንቱ ያመልኩኛል።" ፲ሕዝቡንም ጠርቶ እን
ዲህ አላቸው፤ "ስሙ፥ አስተውሉም። ፲፩ሰውን
የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባው አይደለም፤
ከአፍ የሚወጣው ሰውን ያረክሰዋል እንጂ።"
፲፪ከዚህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው "ፈሪ
ሳውያን ንግግርህን ሰምተው እንደ አንጐራጐሩ
ታውቃለህን?" አሉት። ፲፫እርሱም መልሶ እን
ዲህ አለ፥ "የሰማዩ አባቴ ያልተከላት ተክል
ሁላ ትነቀላለች። ፲፬እነርሱን ተዉአቸው፤ ዕው
ሮችን የሚመሩ ዕውሮች ናቸውና፤ ዕውርም
ዕውርን ቢመራ ሁለቱም ወደ ጕድጓድ ይወድ
ቃሉ።" ፲፭ጴጥሮስም መልሶ፥ "ምሳሌውን ተር
ጕምልን" አለው። ፲፮ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ
አላቸው፥ "እናንተም ገና ይህን አላስተዋላች
ሁምን? ፲፯ወደ አፍ የሚገባው ሁሉ ወደ ሆድ
እንደሚወርድ፥ ወደ ውጭም እንደሚወድቅ
አታውቁምን? ፲፰ከአፍ የሚወጣው ግን ከልብ
ይወጣል፤ ሰውንም የሚያረክሰው ይህ ነው።
፲፱ከልብ ክፉ ዐሳብ ይወጣልና፤ ይኸውም መግ
ደል፥ ምንዝርነት፥ ዝሙት፥ ስርቆት፥ በሐሰት
መመስከር፥ ስድብም ነው። ፳ሰውን የሚያረክ
ሱት እነዚህ ናቸው፤ እጅን ሳይታጠቡ መብላ
ትስ ሰውን አያረክሰውም።"

### ስለ ከነዓናዊት ሴት

፳፩ጌታችን ኢየሱስም ከዚያ ወጥቶ ወደ
ጢሮስና ወደ ሲዶና አገር ሄደ። ፳፪እነሆ፥
አንዲት ከነዓናዊት ሴት ከዚያ አገር
ወጥታ፥ "አቤቱ፥ የዳዊት ልጅ እዘንልኝ፤
ልጄን ክፉ ጋኔን ይዞ ያሠቃያታልና" እያ
ለች ጮኸች። ፳፫ጌታችን ኢየሱስ ግን አን
ድም ቃል አልመለሰላትም፤ ደቀ መዛሙር
ቱም ቀርበው፥ "ይህችን ሴት አሰናብታት፤
እኛን እየተከተለች ትጮሃለችና" ብለው
ማለዱት። ፳፬እርሱም መልሶ፤ "ከእስራኤል
ቤት ወደ ጠፉ በጎች ብቻ እንጂ አልተላ
ክሁም" አላቸው። ፳፭እርስዋ ግን ቀርባ፥
"አቤቱ፥ ርዳኝ" ብላ ሰገደችለት። ፳፮እር
ሱም መልሶ፥ "የልጆችን እንጀራ ወስዶ
ለውሾች መስጠት መልካም አይደለም"
አላት። ፳፯እርስዋም፤ "አዎን ጌታዬ ውሾ

፲፭፥፬ ዘፀ. ፳፥፲፪፤ ፳፩፥፲፯፤ ዘዳ. ፭፥፲፮፤ ዘሌ. ፳፥፱። ፲፭፥፰-፱ ኢሳ. ፳፱፥፲፫። ፲፭፥፲፬ ሉቃ. ፮፥፴፱።
፲፭፥፲፩ ማቴ. ፲፪፥፴፬። ፲፭፥፳፩ ማር. ፯፥፳፬-፴።

ችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ የሚወድቀውን
ፍርፋሪ ይበላሉ” አለች። ፳፰ከዚህም በኋላ
ጌታችን ኢየሱስ መልሶ፥ “አንቺ ሴት፥
እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደ ወደድሽ ይሁ
ንልሽ” አላት፤ ከዚያችም ሰዓት ጀምሮ
ልጅዋ ዳነች።

### ከብዙ ደዌ ስለ ተፈወሱ አሕዛብ

፳፱ጌታችን ኢየሱስም ከዚያ አልፎ ወደ
ገሊላ ባሕር አጠገብ ደረሰ፤ ወደ ተራራም
ወጥቶ በዚያ ተቀመጠ። ፴ብዙ ሕዝብም
ወደ እርሱ ቀረቡ፤ ከእነርሱ ጋርም አንካ
ሶችን፥ ዕውሮችን፥ ደንቆሮዎችን፥ ልምሾ
ዎችንና ሌሎችንም ብዙዎች በሽተኞችን
አምጥተው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ
እግር በታች አኖሩአቸው፤ እርሱም አዳና
ቸው። ፴፩ሕዝቡም ዲዳዎች ሲናገሩ፥ ሽባ
ዎች ሲድኑ፥ አንካሶች ሲሄዱ፥ ዕውሮችም
ሲያዩ አይተው፥ እስኪደነቁ ድረስ፥ የእስ
ራኤልን አምላክ አመሰገኑት።

### ስለ ሰባት እንጀራና ስለ ጥቂት ዓሣ

፴፪ጌታችን ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን
ጠርቶ፥ “እነዚህ ሰዎች ያሳዝኑኛል፤ በዚህ
ከእኔ ጋር ከዋሉ ሦስት ቀን ነውና፤ የሚበ
ሉትም የላቸውም፤ በመንገድ እንዳይደክሙ
ጦማቸውን ላሰናብታቸው አልወድም” አላ
ቸው። ፴፫ደቀ መዛሙርቱም፥ “ይህን ያህል
ሕዝብ የሚያጠግብ እንጀራ በምድረ በዳ ከወ
ዴት እናገኛለን?” አሉት። ፴፬ጌታችን ኢየሱ
ስም፥ “ስንት እንጀራ አላችሁ?” አላቸው፤
እነርሱም፥ “ሰባት እንጀራ፥ ጥቂትም ዓሣ”
አሉት። ፴፭ሕዝቡንም በምድር ላይ እንዲ
ቀመጡ አዘዘ፤ ፴፮ሰባቱን እንጀራና ዓሣውን
ይዞ አመሰገነ፤ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣ
ቸው፤ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ አቀረቡ።
፴፯ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ የተረፈውንም ቍር
ስራሽ ሰባት ቅርጫት ሙሉ አነሡ። ፴፰የበሉት
ሰዎችም ከሴቶችና ከልጆች በቀር አራት ሺህ
ወንዶች ነበሩ። ፴፱ሕዝቡንም አሰናብቶ ወደ
ታንኳው ገባ፤ ወደ መጌዶል አገርም ሄደ።

## ምዕራፍ ፲፮

### ከሰማይ ምልክት ስለሚሹ ሰዎች

(ማር. ፰፥፲፩-፲፫፤ ሉቃ. ፲፪፥፶፬-፶፮)

፩ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንም ከሰማይ
ምልክትን ያሳያቸው ዘንድ ሊፈትኑት
መጡ። ፪ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ
አላቸው፥ “በመሸ ጊዜ ሰማዩ ቀልትዋልና
ጊዜው ብራ ነው ትላላችሁ። ፫በነጋም ጊዜ
ሰማዩ ደምኖ ቀልቶአልና ዛሬስ ይዘንማል
ትላላችሁ፤ እናንተ ግብዞች፥ የሰማዩን ፊት
መተርጐም ታውቃላችሁ፤ የዘመኑንስ ምል
ክት እንዴት አታውቁም? ፬ክፉና[፩] አመን
ዝራ ትውልድ ምልክትን ትሻለች፤ ምልክት
ግን ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር አይሰጣ
ትም” ከዚህም በኋላ ትቶአቸው ሄደ።

### ከፈሪሳውያን ትምህርት ስለ መጠበቅ

(ማር. ፰፥፲፬-፳፩)

፭ደቀ መዛሙርቱም ወደ ማዶ በደረሱ ጊዜ
እንጀራ መያዝን ረስተው ነበር። ፮ጌታችን
ኢየሱስም፥ “ዕወቁ፤ ከፈሪሳውያንና ከሰዱ
ቃውያን እርሾ ተጠበቁ” አላቸው። ፯እነር
ሱም፥ “እንጀራ አልያዝንምና እንዲህ ይለ
ናል?” ብለው እርስ በርሳቸው ዐሰቡ። ፰ጌታ
ችን ኢየሱስም ዐውቆባቸው እንዲህ አላ
ቸው፥ “እናንት እምነት የጐደላችሁ፥ እርስ
በርሳችሁ ምን ታስባላችሁ? እንጀራ ስለሌ
ላችሁ ነውን? ፱ገና አታስተውሉምን? በአ
ምስቱ እንጀራ ጊዜስ ለአምስት ሺህ ሰዎች
የሆነውን፥ ስንት መሶብም እንደ አነሣችሁ
አታስቡምን? ፲ወይስ ሰባት እንጀራ ለአራቱ
ሺህ ሰው፥ ስንት ቅርጫትም እንዳነሣችሁ
ትዝ አይላችሁምን? ፲፩ከፈሪሳውያንና ከሰዱ
ቃውያን እርሾ ተጠበቁ ያልኋችሁ ስለ እን
ጀራ እንዳይደለ እንዴት አታስተውሉም?”
፲፪ከዚህም በኋላ፥ ደቀ መዛሙርቱ ከፈሪሳው
ያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት እንጂ፥ ከእን
ጀራ እርሾ ይጠበቁ ዘንድ እንዳልነገራቸው
ያንጊዜ አስተዋሉ።

---

፩ ግእዙ “ዕሉት” ይላል።

፲፭፥፴፪ ማር. ፰፥፩-፲። ፲፮፥፩ ማቴ. ፲፪፥፴፰፤ ሉቃ. ፲፩፥፲፮። ፲፮፥፬ ማቴ. ፲፪፥፴፱፤ ሉቃ. ፲፩፥፳፱።
፲፮፥፮ ሉቃ. ፲፪፥፩። ፲፮፥፱ ማቴ. ፲፬፥፲፯-፳፩። ፲፮፥፲ ማቴ. ፲፭፥፴፬-፴፰።

### በቂሳርያ ስለ ራሱ እንደ ጠየቃቸው
(ማር. ፰፥፳፯-፴፤ ሉቃ. ፱፥፲፰)

፲፫ጌታችን ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፥ "የሰው ልጅ ሰዎች ማን ይሉታል?" ብሎ ጠየቃቸው። ፲፬እነርሱም፦ "መጥምቁ ዮሐንስ ነው የሚሉ አሉ፤ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ኤርምያስ፥ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ" አሉት። ፲፭እርሱም፦ "እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?" አላቸው። ፲፮ስምዖን ጴጥሮስ መልሶ፥ "አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ" አለው። ፲፯ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ አንተ ብፁዕ ነህ፤ በሰማይ ያለው አባቴ ነው እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና። ፲፰እኔም እልሃለሁ፤ አንተ ዐለት ነህ፤ በዚያች ዐለት ላይም ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ፤ የሲኦል በሮችም አይበረታቱባትም። ፲፱የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈታው በሰማይ የተፈታ ይሆናል።" ፳ከዚህም በኋላ እርሱ ክርስቶስ፪ እንደ ሆነ ለማንም እንዳይናገሩ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው።

### ሕማሙንና ሞቱን ስለ መግለጡ
(ማር. ፰፥፴፩--፱፥፩፤ ሉቃ. ፱፥፳፪-፳፯)

፳፩ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች፥ ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዳለው ለደቀ መዛሙርቱ ይነግራቸው ጀመረ። ፳፪ጴጥሮስም መልሶ:-፫ "አቤቱ፥ ይህ አይሁንብህ፤ ከቶም አይድረስብህ" እያለ ይከለክለው ጀመረ። ፳፫ጌታችን ኢየሱስ ግን መለስ ብሎ ጴጥሮስን እንዲህ አለው፦ "አንተ ሰይጣን! ከኋላዬ ሂድ፤ ዕንቅፋት ሆነህብኛል፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና።"

### መስቀልን ስለ መሸከም

፳፬ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፦ "እኔን ሊከተል የሚወድ ራሱን ይካድ፤ ጨክኖም የሞቱን መስቀል ተሸክሞ ይከተለኝ። ፳፭ነፍሱን ሊያድናት የሚወድ ይጥላታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚጥላት ያገኛታል። ፳፮ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ፥ ነፍሱንም ቢያጣ፥ ለሰው ምን ይረባዋል? ሰውስ ለነፍሱ ቤዛ ምን በሰጠ ነበር? ፳፯የሰው ልጅ መላእክቱን አስከትሎ በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፥ ያንጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ዋጋውን ይሰጠዋል። ፳፰እውነት እላችኋለሁ፤ የሰው ልጅ በመንግሥቱ፬ ሲመጣ እስኪያዩት ድረስ፥ እዚህ ቆመው ካሉት ሞትን የማይቀምሱ አሉ።"

## ምዕራፍ ፲፯

### ክብሩን በደብረ ታቦር ስለ መግለጡ
(ማር. ፱፥፪-፲፫፤ ሉቃ. ፱፥፳፰-፴፮)

፩ከስድስት ቀንም በኋላ፥ ጌታችን ኢየሱስ ጴጥሮስን፥ ያዕቆብንና ወንድሙ ዮሐንስን ይዞ ለብቻቸው ወደ ረዥም ተራራ አወጣቸው። ፪መልኩም በፊታቸው ተለወጠ፤ ፊቱም እንደ ፀሐይ አበራ፤ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። ፫እነሆ፥ ሙሴና ኤልያስም ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። ፬ጴጥሮስም መልሶ ጌታችን ኢየሱስን፥ "አቤቱ፥ በዚህ መኖር ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ ሦስት ቤቶችን በዚህ እንሥራ፤ አንዱን ለአንተ፥ አንዱንም ለሙሴ፥ አንዱንም ለኤልያስ" አለው። ፭እርሱም ገና ይህን ሲናገር ብሩህ ደመና መጥቶ ጋረዳቸው፤ እነሆ፥ ከደመናው ውስጥም "የምወደው፥ በእርሱም ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት" የሚል ቃል መጣ። ፮ደቀ መዛሙር

---

፪ አንዳንድ የግሪክና የግእዝ ዘርዕ "ኢየሱስ ክርስቶስ" ይላል።
፫ ግሪኩ "ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ ..." ይላል።
፬ አንዳንድ የግእዝ ዘርዕ "በስብሐተ አቡሁ ..." ይላል።

፲፮፥፲፬ ማቴ. ፲፬፥ ፩-፪፤ ማር. ፮፥፲፬-፲፭፤ ሉቃ. ፱፥፯-፰። ፲፮፥፲፮ ዮሐ. ፮፥፷፰-፷፱።
፲፮፥፲፱ ማቴ. ፲፰፥፲፰፤ ዮሐ. ፳፥፳፫። ፲፮፥፳፬ ማቴ. ፲፥፴፰፤ ሉቃ. ፲፬፥፳፯።
፲፮፥፳፭ ማቴ. ፲፥፴፱፤ ሉቃ. ፲፯፥፴፫፤ ዮሐ. ፲፪፥፳፭። ፲፮፥፳፯ ማቴ. ፳፭፥፴፩፤ መዝ. ፷፪፥፲፪፤ ሮም ፪፥፮።
፲፯፥፩-፭ ፪ጴጥ. ፩፥፲፯-፲፰።
፲፯፥፭ ዘፍ. ፳፪፥፪፤ ዘዳ. ፲፰፥፲፭፤ መዝ. ፪፥፯፤ ኢሳ. ፵፪፥፩፤ ማቴ. ፫፥፲፯፤ ፲፪፥፲፰፤ ማር. ፩፥፲፩፤ ሉቃ. ፫፥፳፪።

ቱም ሰምተው በግንባራቸው ወደቁ፤ እጅግም
ፈርተው ነበር። ፯ጌታችን ኢየሱስም ቀርቦ ዳሰ
ሳቸው፤ "ተነሡ፥ አትፍሩም" አላቸው። ፰ዐይ
ናቸውንም አቅንተው አዩ፤ ነገር ግን ከጌታ
ችን ከኢየሱስ ብቻ በቀር ያዩት ማንም አል
ነበረም።
፱ከተራራውም ሲወርዱ ጌታችን ኢየሱስ
"የሰው ልጅ ከሙታን ተለይቶ እስኪነሣ ድረስ
ያያችሁትን ለማንም አትናገሩ" ብሎ አዘዛ
ቸው። ፲ደቀ መዛሙርቱም፥ "ጻፎች ኤልያስ
አስቀድሞ ይመጣ ዘንድ አለው ለምን ይላሉ?"
ብለው ጠየቁት። ፲፩ጌታችን ኢየሱስም መልሶ
እንዲህ አላቸው:- አዎን፥ ኤልያስ አስቀድሞ
ይመጣል፥ ሁሉንም ያቀናል። ፲፪ነገር ግን እላ
ችኋለሁ፥ ኤልያስ ፈጽሞ መጥቶአል፤ የወደዱ
ትንም ሁሉ በእርሱ ላይ አደረጉበት እንጂ አላ
ወቁትም፤ እንዲሁ የሰው ልጅም ከእነርሱ መከ
ራን ይቀበል ዘንድ አለው።" ፲፫ከዚህም በኋላ
ደቀ መዛሙርቱ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እንደ ነገ
ራቸው ዐወቁ።

## ጋኔን የሚጥለው ሰው እንደ ተፈወሰ

(ማር. ፱፡፲፬-፳፱፤ ሉቃ. ፱፡፴፯)

፲፬ወደ ሕዝቡም በደረሱ ጊዜ አንድ ሰው ወደ
እርሱ ቀርቦ እየለመነ ሰገደለት። ፲፭እንዲህም
አለ፥ "አቤቱ፥ ልጄን ማርልኝ፤ ክፉ ጋኔን በየ
ወሩ መጀመሪያ[፩] ያሠቃየዋልና፥ ይዞ ይጥለዋ
ልና፤ ብዙ ጊዜም ወደ እሳት ይጥለዋል፤ ወደ
ውኃም የሚጥልበት ጊዜ አለ። ፲፮ወደ ደቀ መዛ
ሙርትህም አመጣሁት፤ እርሱንም ማዳን ተሳ
ናቸው።" ፲፯ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ
መልሶ፥ "የማታምን ጠማማ ትውልድ፥ እስከ
መቼ ድረስ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ
መቼስ እታገሣችኋለሁ? ወደዚህ አምጡልኝ"
አለ። ፲፰ጌታችን ኢየሱስም ገሠጸውና ጋኔኑ ከእ
ርሱ ወጣ፤ በዚያች ሰዓትም ልጁ ዳነ። ፲፱ከዚ
ህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ቀር
በው ጌታችን ኢየሱስን፥ "ስለምን እኛ ማው
ጣት ተሳነን?" አሉት። ፳ጌታችን ኢየሱስም፥
"ስለ እምነታችሁ መጕደል ነው፤ እውነት እላ
ችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት
ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ወደዚያ ተነቅለህ
ሂድ ብትሉት ይፈልሳል፤ የሚሳናችሁ ነገርም
የለም። ፳፩ይህ ዓይነት ግን ያለ ጾምና ጸሎት
አይወጣም" አላቸው።
፳፪በገሊላም ሲመላለሱ፥ ጌታችን ኢየሱስ፥
"የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጥ ዘንድ
አለው፤ ፳፫ይገድሉታል፤ በሦስተኛውም ቀን
ይነሣል" አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም ይህን
ሰምተው እጅግ አዘኑ።

## ለቤተ መቅደስ ግብር ስለ መክፈል

፳፬ወደ ቅፍርናሆምም በደረሱ ጊዜ ግብር
የሚቀበሉ ሰዎች ወደ ጴጥሮስ መጥተው፥
"መምህራችሁ ሁለቱን ዲናር አይገብርምን?"
አሉት። ፳፭እርሱም፥ "አዎን" አለ፤ ወደ
ቤትም በገባ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ አስቀድሞ፥
"ስምዖን ሆይ፥ ምን ትላለህ? የምድር ነገሥ
ታት ቀረጥንና ግብርን ከማን ይቀበላሉ? ከል
ጆቻቸው ወይስ ከሌሎች?" አለው። ፳፮ጴጥ
ሮስም "ከሌሎች ነው" አለ፤ ጌታችን ኢየ
ሱስም አለው፤ "እንኪያስ ልጆቻቸው ነጻ
ናቸው። ፳፯ነገር ግን፤ እንዳያጕረመርሙ ወደ
ባሕር ሂድና መረብ ጣል፤ በመጀመሪያ የያዝ
ኸውን ዓሣ ወስደህ አፉን ክፈት፤ በውስጡም
ሰጣጢራ ታገኛለህ፤ ይኸውም አራት ድሪም
ነው፤ እርሱንም ወስደህ ስለ እኔና ስለ አንተ
ስጣቸው" አለው።

## ምዕራፍ ፲፰

## ትሕትናን ስለ ማስተማሩ

(ማር. ፱፡፴፫-፴፯፤ ሉቃ. ፱፡፵፮-፵፰)

፩በዚያችም ሰዓት የጌታችን ኢየሱስ ደቀ መዛ
ሙርት፥ "በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበ
ልጥ ማነው?" እያሉ ወደ እርሱ ቀረቡ። ፪ሕፃ
ንንም ጠርቶ በመካከላቸው አቆመው። ፫እን
ዲህም አለ፥ "እውነት እላችኋለሁ፤ ካልተመ
ለሳችሁ፥ እንደዚህም ሕፃን ካልሆናችሁ ወደ
መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም። ፬እንደዚ
ህም ሕፃን ራሱን ዝቅ ያደረገ በመንግሥተ ሰማ
ያት የሚበልጥ ይህ ነው። ፭እንደዚህም ያለውን
አንድ ሕፃን በስሜ የሚቀበል እኔን ይቀበላል።
፮በእኔ ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን

---

፩ ግሪኩ "ጨረቃ ስትወጣ" የሚል አለው።

፲፯፡፲ ሚል. ፬፡፭።  ፲፯፡፲፪ ማቴ. ፲፩፡፲፬።  ፲፯፡፳ ማቴ. ፳፩፡፳፩፤ ማር. ፲፩፡፳፫፤ ፩ቆሮ. ፲፫፡፪።
፲፯፡፳፪ ማር. ፱፡፴-፴፪፤ ሉቃ. ፱፡፵፫።  ፲፯፡፳፬ ዘፀ. ፴፡፲፫፤ ፴፰፡፳፮።  ፲፰፡፩ ሉቃ. ፳፪፡፳፬።
፲፰፡፫ ማር. ፲፡፲፭፤ ሉቃ. ፲፰፡፲፯።

የሚያስናክል አህያ የሚፈጭበት ወፍጮ በአ
ንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ቢሰጥም ይሻ
ለዋል።
፯"ከሚመጣው ማሰናከያ የተነሣ ለዓለም ወዮ
ለት፤ ማሰናከያ ግድ ይመጣልና፤ ነገር ግን
ማሰናከያን ለሚያመጣት ለዚያ ሰው ወዮለት።
፰እጅህ ወይም እግርህ ብታስትህ ከአንተ ቈር
ጠህ ጣላት፤ ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር
ኖሮህ ወደ ዘለዓለም እሳት ከምትጣል፥ አንካሳ
ወይም ጕንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት ብትገባ
ይሻልሃልና። ፱ዐይንህ ብታስትህ ከአንተ አውጥ
ተህ ጣላት፤ ሁለት ዐይን ኖሮህ ወደ ዘለዓለም
ገሃነመ እሳት ከምትጣል፥ አንድ ዐይን ኖሮህ
ወደ ሕይወት ብትገባ ይሻልሃልና።

## ስለ ጠፋው በግ
(ሉቃ. ፲፭፥፫-፯)

፲"ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ስንኳ እንዳ
ትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት
ሁልጊዜ በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ
እላችኋለሁ። ፲፩የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈል
ግና ሊያድን መጥቶአልና። ፲፪ምን ትላላችሁ?
መቶ በጎች ያሉት ሰው ቢኖር፥ ከመካከላቸ
ውም አንዱ ቢጠፋው፥ ዘጠና ዘጠኙን በተ
ራራ ላይ ትቶ የጠፋውን ሊፈልግ ይሄድ የለ
ምን? ፲፫እውነት እላችኋለሁ፤ ባገኘው ጊዜ ካል
ጠፉት ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ ጠፍቶ ስለ ተገ
ኘው ፈጽሞ ደስ ይለዋል። ፲፬እንዲሁም ከእነ
ዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንኳ ይጠፉ ዘንድ በሰ
ማያት ባለው አባቴ ፊት አይፈቀድም።

## ወንድምን ስለ መምከር

፲፭"ወንድምህ አንተን ቢበድልህ፥ ሄደህ
ብቻህን ሆነህ፥ ብቻውን አድርገህ ምከረው፤
ቢሰማህ ወንድምህን ጠቀምኸው። ፲፮ባይሰ
ማህ ግን በሁለተኛው ጊዜ ከአንተ ጋር አንድ
ወይም ሁለት ምስክር ያዝ፤ ነገር ሁሉ በሁ
ለት ወይም በሦስት ምስክር ቃል ይጸናልና።
፲፯እነርሱን ባይሰማቸው ግን ለቤተ ክርስቲያን
ንገራት፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማት እንደ
አረማዊና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ። ፲፰እውነት
እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት በሰማይ የታ
ሰረ ይሆናል፤ በምድርም የምትፈቱት በሰማይ
የተፈታ ይሆናል። ፲፱ዳግመኛም እላችኋለሁ፤
ከእናንተ ሁለቱ በምድር ላይ ስለሚለምኑት
ነገር ሁሉ ቢተባበሩ፥ በሰማያት ባለው አባቴ
ዘንድ ይደረግላቸዋል። ፳ሁለት ወይም ሦስት
በስሜ በሚሰበሰቡበት እኔ በዚያ በመካከላቸው
እኖራለሁና።"
፳፩ከዚህም በኋላ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ፥
"አቤቱ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተ
ውለት? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?" አለው።
፳፪ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አለው፥ " እስከ
ሰባ ጊዜ ሰባት ነው እንጂ እስከ ሰባት አልል
ህም።

## ስለ ንጉሥና ስለ አገልጋዮቹ ምሳሌ

፳፫"ስለዚህም መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን
ሊቈጣጠራቸው የወደደ ንጉሥን ትመስላለች።
፳፬ሊቈጣጠራቸውም በጀመረ ጊዜ እልፍ መክ
ሊት የሚከፍለውን አንድ ባለ ዕዳ ወደ እርሱ
አመጡ። ፳፭የሚከፍለውም ባጣ ጊዜ ጌታው
እርሱና ሚስቱ፥ ልጆቹም፥ ያለውም ሁሉ እን
ዲሸጡና ዕዳውን እንዲከፍል አዘዘ። ፳፮ወዲያ
ውም ያ አገልጋይ ወድቆ ሰገደለት፡- አቤቱ፥
ታገሠኝ፤ ሁሉን እከፍልሃለሁ እያለ ለመነው።
፳፯ጌታውም ያን አገልጋይ አዘነለትና ፈታው፤
ዕዳውንም ተወለት። ፳፰ነገር ግን ያ አገልጋይ
በወጣ ጊዜ፥ ከአገልጋዮች ባልንጀሮቹ መቶ
ዲናር የሚከፍለውን አንድ ባለ ዕዳ አገኘና የም
ትከፍለኝን ስጠኝ ብሎ አንቆ ያዘው። ፳፱ያም
የጌታው አገልጋይ እግሩ ላይ ወድቆ፡- ታገሠኝ
ሁሉንም እከፍልሃለሁ እያለ ለመነው። ፴እር
ሱም እንቢ አለው፤ ዕዳውንም እስኪከፍለው
ድረስ ወስዶ አሰረው። ፴፩ባልንጀሮቹ አገልጋዮ
ችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፤ ሄደ
ውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ነገሩት። ፴፪ከዚ
ህም በኋላ ጌታው ጠራውና እንዲህ አለው፡-
አንተ ክፉ አገልጋይ ስለ ለመንኸኝ ዕዳህን
ሁሉ ተውሁልህ። ፴፫አንተስ እኔ እንደ ማርሁህ
ባልንጀራህን ልትምረው አይገባህምን? ፴፬ጌታ
ውም ተቈጥቶ ዕዳውን ሁሉ ጨርሶ እስኪከ
ፍለው ድረስ ለሚያሠቃዩት አሳልፎ ሰጠው።
፴፭እናንተም የወንድሞቻችሁን በደል ከልባችሁ
ይቅር ባትሉ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንዲሁ
ያደርግባችኋል።"

---

፲፰፥፯ ማቴ. ፳፮፥፳፬።  ፲፰፥፱ ማቴ. ፭፥፳፱።  ፲፰፥፲፩ ሉቃ. ፲፱፥፲።  ፲፰፥፲፪ ሉቃ. ፲፭፥፫።
፲፰፥፲፮ ዘዳ. ፲፱፥፲፭።  ፲፰፥፲፰ ማቴ. ፲፮፥፲፱፤ ዮሐ. ፳፥፳፫።  ፲፰፥፳፩-፳፪ ሉቃ. ፲፯፥፫-፬።
፲፰፥፳፪ ዘፍ. ፬፥፳፬።

## ምዕራፍ ፲፱

### ስለ ፈሪሳውያን ጥያቄ

(ማር. ፲፥፩-፲፪)

፩ጌታችን ኢየሱስም ይህን ነገር ከፈጸመ በኋላ
ከገሊላ ተነሥቶ ወደ ይሁዳ አውራጃ ወደ ዮር
ዳኖስ ማዶ ደረሰ። ፪ብዙዎች በሽተኞችም ተከ
ተሉት፤ በዚያም ፈወሳቸው። ፫ፈሪሳውያንም
ሊፈትኑት ወደ እርሱ መጥተው፥ "በማናቸ
ውም በበደለችው ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ለሰው
ይገባልን?" አሉት። ፬እርሱም መልሶ እንዲህ
አላቸው፥ "አላነበባችሁምን? በመጀመሪያ የፈ
ጠራቸው እርሱ ወንድና ሴት አደረጋቸው።"
፭እንዲህም አለ፥ "ስለዚህ ሰው አባቱንና እና
ቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል፤ ሁለቱም አንድ
አካል ይሆናሉ። ፮እንኪያስ ሁለት አይደሉም፤
አንድ አካል ናቸው እንጂ፤ እግዚአብሔርም
አንድ ያደረገውን ሰው አይለይ።" ፯እነርሱም፥
"እንኪያ የፍቺዋን ደብዳቤ ሰጥተው እንዲፈቷ
አት ሙሴ ለምን አዘዘ?" አሉት። ፰እርሱም
አላቸው፥ "ሙሴስ ስለ ልባችሁ ክፋት ሚስቶ
ቻችሁን እንድትፈቱ ፈቀደላችሁ፤ ቀድሞ ግን
እንዲህ አልነበረም። ፱እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ያለ
ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመ
ንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም ያገባ ያመ
ነዝራል።"

፲ደቀ መዛሙርቱም፥ "የባልና የሚስት ሥር
ዐት እንዲህ ከሆነስ መጋባት መልካም አይደ
ለም" አሉት። ፲፩እርሱም አላቸው፥ "ይህ ለተ
ሰጠው ነው እንጂ ለሁሉ የሚቻል አይደለም።
፲፪ከእናታቸው ማኅፀን እንዲሁ የተወለዱ ጃን
ደረቦች አሉና፤ ሰዎች የሰለቡአቸውም ጃንደ
ረቦች አሉ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸ
ውን ጃንደረባ ያደረጉ አሉ፤ መታገሥ የሚችል
ግን ይታገሥ።"

### ጌታ ስለ ባረካቸው ሕፃናት

(ማር. ፲፥፲፫-፲፮)

፲፫ከዚህም በኋላ እጁን በላያቸው ጭኖ ይጸ
ልይ ዘንድ ሕፃናትን አመጡለት፤ ደቀ መዛሙ
ርቱ ግን ተቈጡአቸው። ፲፬ጌታችን ኢየሱስም፥
"ሕፃናትን ተዉአቸው፤ ወደ እኔም ይመጡ
ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት
እንደ እነዚህ ላሉት ናትና" አላቸው። ፲፭እጁ
ንም በላያቸው ጫነባቸውና ከዚያ ሄደ።

### ስለ ባለጸጋው ጥያቄ

(ማር. ፲፥፲፯-፴፩፤ ሉቃ. ፲፰፥፲፰-፴)

፲፮እነሆም አንድ ጐልማሳ መጥቶ፥ "ቸር
መምህር ሆይ የዘለዓለም ሕይወትን እወ
ርስ ዘንድ ከበጎ ሥራ ወገን ምን ላድርግ?"
አለው። ፲፯እርሱም፥ "ለምን ቸር ትለኛለህ?
ከአንዱ እግዚአብሔር በቀር ማንም ቸር የለም፤
ወደ ሕይወት ልትገባ ብትወድድስ ትእዛዛትን
ጠብቅ" አለው። ፲፰እርሱም፥ "የትኞቹን?"
አለው፤ ጌታችን ኢየሱሱም አለው፥ "አትግ
ደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በሐሰትም አት
መስክር፥ ፲፱አባትህንና እናትህን አክብር፤ ባል
ንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ።" ፳ያም ጐል
ማሳ፥ "ይህን ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአ
ለሁ፤ እንግዲህ የቀረኝ ምንድን ነው?" አለው።
፳፩ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አለው፥ "ፍጹም
ልትሆን ብትወድስ፥ ሂድና ያለህን ሁሉ ሸጠህ
ለድኆች ስጥ፤ ሰማያዊ ሀብትንም ታገኛለህ፤
መጥተህም ተከተለኝ።" ፳፪ጐልማሳውም ይህን
ነገር ሰምቶ ሀብቱ ብዙ ነበርና እያዘነ ሄደ።
፳፫ጌታችን ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ
አላቸው፥ "እውነት እላችኋለሁ፤ ባለጸጋ ወደ
መንግሥተ ሰማያት ይገባ ዘንድ ጭንቅ ነው።
፳፬ዳግመኛም እላችኋለሁ፡- ባለጸጋ ወደ እግ
ዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል
በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል።" ፳፭ደቀ
መዛሙርቱም ይህን በሰሙ ጊዜ፥ "እንግዲያ
ማን ሊድን ይችላል?" እያሉ እጅግ ተደነቁ።
፳፮ጌታችን ኢየሱስም አያቸውና፥ "በሰው
ዘንድ ይህ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ
ግን ሁሉ ይቻላል" አላቸው።

### ዕጥፍ ዋጋ ስለ ማግኘት

፳፯ከዚህም በኋላ ጴጥሮስ መልሶ፥ "እኛ
ሁሉን ትተን ተከተልንህ፤ እንግዲህ ምን እናገ
ኛለን?" አለው። ፳፰ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ
አላቸው፥ "እውነት እላችኋለሁ፤ የተከተላች
ሁኝ እናንተ በዳግም ልደት የሰው ልጅ በክ
ብሩ ዙፋን በተቀመጠ ጊዜ እናንተም በዐሥራ

---

፲፱፥፬ ዘፍ፥ ፩፥፳፯፤ ፭፥፪። ፲፱፥፭ ዘፍ. ፪፥፳፬። ፲፱፥፯ ዘዳ. ፳፬፥ ፩-፬፤ ማቴ. ፭፥፴፩።
፲፱፥፱ ማቴ. ፭፥፴፪፤ ፩ቆሮ. ፯፥፲-፲፩። ፲፱፥፲፰ ዘፀ. ፳፥፲፫-፲፮፤ ዘዳ. ፭፥፲፯-፳።
፲፱፥፲፱ ዘፀ. ፳፥፲፪፤ ዘዳ. ፭፥፲፮፤ ዘሌ. ፲፱፥፲፰። ፲፱፥፳፰ ማቴ. ፳፭፥፴፩፤ ሉቃ. ፳፪፥፴።

ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ፤ በዐሥራ ሁለ
ቱም ነገደ እሥራኤል ትፈርዳላችሁ። ፳፱ስለ
ስሜም ቤትን፥ ወይም ወንድሞችን፥ ወይም
እኅቶችን፥ ወይም አባትን፥ ወይም እናትን፥
ወይም ሚስትን፥ ወይም ልጆችን፥ ወይም ርስ
ትን የተወ ሁሉ መቶ ዕጥፍ ዋጋ ያገኛል፤ የዘ
ለዓለም ሕይወትንም ይወርሳል። ፴ነገር ግን
ብዙዎች ፊተኞች ኋለኞች ይሆናሉ፤ ኋለኞችም
ፊተኞች ይሆናሉ።

## ምዕራፍ ፳

### ስለ ወይኑ ባለቤት ምሳሌ

፩"መንግሥተ ሰማያት ለወይኑ ቦታ ሠራተኞ
ችን ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤት ሰውን ትመስ
ላለች። ፪ከሠራተኞችም ጋር በቀን አንድ ድሪም
ሊሰጣቸው ተስማምቶ፥ ወደ ወይኑ ቦታ ላካ
ቸው። ፫በሦስት ሰዓትም በወጣ ጊዜ ሌሎችን
በአደባባይ ቆመው ሥራ ፈትተው አየ። ፬እነዚያ
ንም፦ እናንተም ወደ ወይኔ ቦታ ሂዱና ሥሩ፤
የሚገባውንም እሰጣችኋለሁ አላቸው፤ እነርሱም
ሄዱ። ፭ዳግመኛም በስድስትና በዘጠኝ ሰዓት
ወጥቶ እንዲሁ አደረገ። ፮በዐሥራ አንድ ሰዓትም
ወጥቶ ሌሎችን ቆመው አገኘ፤ ቀኑን ሁሉ ሥራ
ፈትታችሁ ለምን በዚህ ቆማችኋል? አላቸው።
፯እነርሱም፦ የሚቀጥረን ስለ አጣን ነው አሉት፤
እርሱም፦ እናንተ ወደ ወይኔ ቦታ ሂዱ፤ የሚገባ
ውንም እሰጣችኋለሁ አላቸው። ፰በመሸም ጊዜ
የወይኑ ቦታ ባለቤት ሹሙን እንዲህ አለው፤
ሠራተኞቹን ጠርተህ አስቀድመህ ከኋለኞች ጀም
ረህ እስከ ፊተኞች ድረስ ደመወዛቸውን ስጣ
ቸው። ፱በዐሥራ አንድኛው ሰዓት የተቀጠሩትም
መጡና እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ።
፲የቀደሙትም መጥተው ከእነዚያ ይበልጥ የሚ
ያገኙ መስሎአቸው ነበር፤ እነርሱም እያንዳን
ዳቸው አንድ አንድ ዲናር ተቀበሉ። ፲፩ተቀብ
ለውም በባለቤቱ ላይ አንጐራጐሩ። ፲፪እንዲህ
እያሉ፦ እነዚህ ኋለኞች አንዲት ሰዓት ብቻ
ሠሩ፤ የቀኑን ድካምና ሐሩር ከተሸከምነው ከእ
ኛም ጋር አስተካከልሃቸው። ፲፫እርሱ ግን ከእነ
ርሱ አንዱን እንዲህ አለው፦ ወዳጄ ሆይ፥ አልበ
ደልሁህም፤ በአንድ ዲናር ተስማምቼህ የለምን?
፲፬የሚደርስህን ይዘህ ሂድ፤ እኔም ለዚህ ለኋለ
ኛው እንዳንተ ልሰጠው እወዳለሁ። ፲፭ወይስ በገ
ንዘቤ የወደድሁትን ላደርግ መብት የለኝምን?
ወይስ እኔ ቸር ስለሆንሁ ዐይንህ ምቀኛ ናትን?
፲፮እንዲሁም ኋለኞች ፊተኞች ይሆናሉ፤ ፊተኞ
ችም ኋለኞች ይሆናሉ፤ የተጠሩ ብዙዎች፥ የተ
መረጡም ጥቂቶች ናቸውና።"

### ስለ መከራውና ስለ ሞቱ

(ማር. ፲፥፴፪-፴፬፤ ሉቃ. ፲፰፥፴፩-፴፬)

፲፯ጌታችን ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ
ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ለብቻቸው
ወሰዳቸው፤ በመንገድም እንዲህ አላቸው፦
፲፰"እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፤ የሰው
ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች ተላልፎ ይሰ
ጣል፤ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል። ፲፱ለሕዝ
ቡም አሳልፈው ይሰጡታል፤ እነርሱም ይዘብ
ቱበታል፤ ይገርፉታል፤ ይሰቅሉታል፤ በሦስተ
ኛውም ቀን ይነሣል።"

### ስለ ዘብዴዎስ ልጆች

(ማር. ፲፥፴፭-፵፭)

፳ከዚህም በኋላ፥ የዘብዴዎስ ልጆች እናት
ከልጆችዋ ጋር መጣች፤ ከእርሱም አንዳች
ነገር እየለመነች ሰገደችለት። ፳፩እርሱም፥ "ምን
ትፈልጊያለሽ?" አላት፤ እርስዋም፥ "እነዚህ
ሁለቱ ልጆቼ በመንግሥትህ አንዱ በቀኝህ አን
ዱም በግራህ እንዲቀመጡ አድርግልኝ" አለ
ችው። ፳፪ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ "የምት
ለምኑትን አታውቁም፤ እኔ የምጠጣውን ጽዋ
መጠጣት ትችላላችሁን? እኔስ የምጠመቀውን
ጥምቀት ትጠመቃላችሁን?" አላቸው። እነር
ሱም፥ "አዎን፥ እንችላለን" አሉት። ፳፫እር
ሱም፥ "ጽዋዬንስ ትጠጣላችሁ፤ ጥምቀቴንም
ትጠመቃላችሁ፤ በቀኜና በግራዬ መቀመጥን
ግን ከአባቴ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ የም
ሰጥ እኔ አይደለሁም" አላቸው። ፳፬ዐሥሩም
ሰምተው በሁለቱ ወንድማማቾች ላይ አዘኑ።
፳፭ጌታችን ኢየሱስም ጠርቶ እንዲህ አላቸው፥
"አሕዛብን መኳንንቶቻቸው እንዲገዙአቸው፥
ታላላቆቻቸውም እንዲሠለጥኑባቸው፤ አታው
ቁምን? ፳፮በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር
ግን ከእናንተ የበላይ ሊሆን የሚወድ አገልጋይ
ይሁናችሁ። ፳፯ከእናንተም አለቃ ሊሆን የሚ

---

፲፱፥፴ ማቴ. ፳፥፲፮፤ ሉቃ. ፲፫፥፴። ፳፥፰ ዘሌ. ፲፱፥፲፫፤ ዘዳ. ፳፬፥፲፭።
፳፥፲፮ ማቴ. ፲፱፥፴፤ ማር. ፲፥፴፩፤ ሉቃ. ፲፫፥፴። ፳፥፳፭-፳፯ ሉቃ. ፳፪፥፳፭-፳፯።
፳፥፳፯ ማቴ. ፳፫፥፲፩፤ ማር. ፱፥፴፭፤ ሉቃ. ፳፪፥፳፯።

ወድ፥ ሎሌ ይሁናችሁ። ፳፰የሰው ልጅ ሊያ
ገለግል፥ ሰውነቱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ
ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣምና።”

## ስለ ሁለቱ ዕውራን መፈወስ

(ማር. ፲፡፵፮-፶፪፤ ሉቃ. ፲፰፡፴፭-፵፫)

፳፱ከኢያሪኮም በወጣ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተከ
ተሉት። ፴እነሆ፥ ሁለት ዕውራን በመንገድ
አጠገብ ተቀምጠው ነበር፤ ጌታችን ኢየሱስም
ሲያልፍ ሰምተው፥ “አቤቱ፥ የዳዊት ልጅ፥
ይቅር በለን” እያሉ ጮኹ። ፴፩ሕዝቡ ግን ዝም
እንዲሉ ይቈጡአቸው ነበር፤ እነርሱ ግን፥
“አቤቱ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረን” እያሉ አብዝ
ተው ጮኹ። ፴፪ጌታችን ኢየሱስም ቆሞ ጠራቸ
ውና፥ “ምን ላደርግላችሁ ትወዳላችሁ?” አላ
ቸው። ፴፫እነርሱም፥ “አቤቱ፥ ዐይኖቻችን እን
ዲከፈቱ ነው” አሉት። ፴፬ጌታችን ኢየሱስም
አዘነላቸው፤ ዐይኖቻቸውንም ዳሰሳቸው፤ ወዲ
ያውም አዩና ተከተሉት።

## ምዕራፍ ፳፩

## ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መግባቱ

(ማር. ፲፩፡፩-፲፩፤ ሉቃ. ፲፱፡፳፰-፵)

፩ጌታችን ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ቀርቦ፥
ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተ ፋጌ በደረሰ ጊዜ
ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ላከ። ፪እንዲህም
አላቸው፤ “በፊታችሁ ወደ አለችው መንደር
ሂዱ፤ ያንጊዜም የታሰረች አህያ ከውርንጫዋ
ጋር ታገኛላችሁ፤ ፍቱና አምጡልኝ። ፫ምን
ታደርጋላችሁ? የሚላችሁ ቢኖርም ጌታቸው
ይሻቸዋል በሉ፥ ያንጊዜ ይሰዱአችኋል።”
፬ይህም ሁሉ የሆነው በነቢይ እንዲህ ተብሎ
የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው። ፭“ለጽዮን
ልጅ፦ እነሆ፥ የዋህ ንጉሥሽ በአህያይቱና በአህ
ያይቱ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመ
ጣል በሉአት”። ፮ደቀ መዛሙርቱም ሄደው
ጌታችን ኢየሱስ እንደ አዘዛቸው አደረጉ። ፯አህ
ያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፤ ልብሳ
ቸውንም በላያቸው ጫኑ፤ ጌታችን ኢየሱስም
በእነርሱ ላይ ተቀመጠ። ፰ብዙ ሕዝብም ልብ
ሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፤ ሌሎችም ከዛ
ፎች ጫፍ ጫፉን እየቈረጡ በመንገድ ላይ ያነ
ጥፉ ነበር። ፱በፊቱ የሚሄዱትና የሚከተሉት
ሕዝብም፥ “ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ፤ በእግዚአ
ብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው፤ ሆሣዕና በአ
ርያም” እያሉ ይጮሁ ነበር። ፲ጌታችን ኢየሱ
ስም ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ፥ “ከተማዪቱ
ይህ ማነው?” እያለች ታወከች። ፲፩ሕዝቡም፥
“ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣው ነቢዩ ኢየሱስ
ነው” አሉ።

## በቤተ መቅደስ ስለ አደረገው ተአምር

(ማር. ፲፩፡፲፭-፲፱፤ ሉቃ. ፲፱፡፵፭-፵፰)

፲፪ጌታችን ኢየሱስም ወደ ቤተ መቅደስ
ገብቶ በቤተ መቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙ
ትን ሁሉ አባረረ፤ የገንዘብ ለዋጮችንም መደ
ርደሪያ፥ የርግብ ሻጮችንም ወንበር ገለበጠ።
፲፫“ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል ተብሎ ተጽፎ
አል፤ እናንተ ግን የሌባና የቀማኛ ዋሻ አደረጋ
ችሁት” አላቸው። ፲፬በቤተ መቅደስም ዕውሮ
ችና አንካሶች ወደ እርሱ መጡ፤ አዳናቸውም።
፲፭ያንጊዜም የካህናት አለቆችና ጻፎች ያደረገ
ውን ተአምራት፥ ልጆችንም በቤተ መቅደስ፥
“ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ” እያሉ ሲጮሁ ባዩ
ጊዜ ደስ አላላቸውም።[፩] ፲፮እነርሱም፥ “እነዚህ
የሚሉትን አትሰማምን?” አሉት፤ ጌታችን ኢየ
ሱስም፥ “አዎን፥ እሰማለሁ፥ ‘ከልጆችና ከሕ
ፃናት አንደበት ምስጋናን አዘጋጀህ’ የሚለውን
ቃል ከቶ ያነበባችሁበት ጊዜ የለምን?” አላ
ቸው። ፲፯ትቶአቸውም ከከተማው ወደ ቢታ
ንያ ሄደ፤ በዚያም አደረ።

## ፍሬ ስለ ታጣባት በለስ

፲፰በነጋም ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ወደ ከተማ
ሲመለስ ተራበ። ፲፱በመንገድም አጠገብ የበለስ
ዛፍ አይቶ ወደ እርስዋ ሄደ፤ ነገር ግን ከቅ
ጠል ብቻ በቀር ምንም ፍሬ አላገኘባትም፤
“እንግዲህ ወዲህ ለዘለዓለም ፍሬ አይኑርብሽ”
አላት፤ ያንጊዜውንም በለሲቱ ደረቀች። ፳ደቀ
መዛሙርቱም አይተው “ይህቺ በለስ እንዴት
ወዲያውኑ ደረቀች?” ብለው አደነቁ። ፳፩ጌታ
ችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “እው
ነት እላችኋለሁ እምነት ቢኖራችሁ፥ ባትጠራ
ጠሩም በበለሲቱ እንደ ተደረገው ብቻ የምታደ
ርጉ አይደለም፤ ነገር ግን ይህን ተራራ ተነሥ

---

፩ ግሪኩ “ተቈጡ” ይላል።

፳፩፡፭ ዘካ. ፱፡፱። ፳፩፡፱ መዝ. ፻፲፯፡፳፭-፳፮። ፳፩፡፲፫ ኢሳ. ፶፮፡፯፤ ኤር. ፯፡፲፩። ፳፩፡፲፮ መዝ. ፰፡፪።
፳፩፡፳፩ ማቴ. ፲፯፡፳፤ ፩ቆሮ. ፲፫፡፪።

ተህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት ይደረግላ
ችኋል። ፳፪አምናችሁ በጸሎት የምትለምኑትን
ሁሉ ታገኛላችሁ።”

## ስለ ካህናት አለቆችና ስለ መምህራን ጥያቄ

(ማር. ፲፩፥፳፯-፴፫፤ ሉቃ. ፳፥፩-፰)

፳፫ወደ ቤተ መቅደስም ገብቶ ሲያስተምር፥
የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሌዎች፥ ወደ
እርሱ መጥተው፥ “በማን ሥልጣን ይህን ታደር
ጋለህ? ይህንስ ሥልጣን ማን ሰጠህ?” አሉት።
፳፬ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፥ “እኔም አንዲት
ቃል እጠይቃችኋለሁ፤ የነገራችሁኝ እንደ ሆነ
እኔም በምን ሥልጣን ይህን እንደማደርግ እነ
ግራችኋለሁ” አላቸው። ፳፭“የዮሐንስ ጥምቀቱ
ከየት ነው? ከሰማይ ነውን? ወይስ ከሰው?”
አላቸው፤ እርስ በርሳቸውም ተነጋግረው እን
ዲህ አሉ፥ “ከሰማይ ነው ብንለው እንኪያ
ለምን አላመናችሁበትም? ይለናል። ፳፮ከሰው
ነው ብንለውም ዮሐንስን ሁሉም እንደ ነቢይ
ያዩታልና ሕዝቡን እንፈራቸዋለን፤” ፳፯እነር
ሱም፥ “አናውቅም” ብለው መለሱለት፤ እር
ሱም፥ “እንኪያስ እኔም በምን ሥልጣን ይህን
እንደማደርግ አልነግራችሁም” አላቸው።

## ስለ ሁለት ወንድማማቾች

፳፰“ምን ትላላችሁ? አንድ ሰው ሁለት ወን
ድማማች ልጆች ነበሩት፤ ታላቁንም፦ ልጄ
ሆይ! ዛሬ ወደ ወይኔ ቦታ ሂድና ሥራ አለው።
፳፱ልጁም መልሶ እንቢ አለ፤ ኋላ ግን ተጸጽቶ
ሄደ። ፴ሁለተኛውንም እንዲሁ አለው፤ እርሱም
እሺ ጌታዬ አለ፤ ነገር ግን አልሄደም። ፴፩እንግ
ዲህ ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ የፈጸመ ማንኛው
ነው?” አላቸው፤ “ፊተኛው ነዋ” አሉት፤ ጌታ
ችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ “እውነት እላ
ችኋለሁ፤ ቀራጮችና አመንዝሮች ወደ እግዚአ
ብሔር መንግሥት በመግባት ይቀድሙአችኋል።
፴፪ዮሐንስ በጽድቅ ጎዳና ወደ እናንተ መጣ፤ አላ
መናችሁበትም፤ ቀራጮችና አመንዝሮች ግን
አመኑበት፤ እናንተም በኋላ በእርሱ ለማመን
አይታችሁ እንኳ ንስሓ አልገባችሁም።

## ስለ ወይን ምሳሌ

(ማር. ፲፪፥፩-፲፪፤ ሉቃ. ፳፥፱-፲፱)

፴፫“ሌላ ምሳሌ ስሙ፤ ባለቤት ሰው ወይንን
ተከለ፤ ቅጥርም ቀጠረለት፤ መጭመቂያም አስ
ቈፈረለት፤ ግንብም ሠራለት፤ ለገባሮችም ሰጥ
ቶአቸው ሄደ። ፴፬የሚያፈራበት ወራት በደረሰ
ጊዜም፥ ከወይኑ ፍሬ ያመጡለት ዘንድ አገል
ጋዮችን ወደ ገባሮቹ ላከ። ፴፭ገባሮቹም አገልጋዮ
ቹን ይዘው፥ አንዱን በበትር ደበደቡት፤ አንዱ
ንም ገደሉት፤ ሌላውንም በድንጋይ መቱት።
፴፮ከዚያም በኋላ ከቀደሙት የሚበዙ ሌሎች
አገልጋዮችን ላከ፤ እነርሱንም እንዲሁ አደረ
ጉባቸው። ፴፯በኋላም ልጄንስ ይፈሩት ይሆናል
ብሎ ልጁን ላከ። ፴፰ገባሮቹም ልጁን ባዩት
ጊዜ እርስ በርሳቸው፦ እነሆ፥ ወራሹ ይህ
ነው፤ ኑ እንግደለውና ርስቱን እንውረስ ተባ
ባሉ። ፴፱ይዘውም ከወይኑ ቦታ ወደ ውጭ አው
ጥተው ገደሉት። ፵እንግዲህ የወይኑ ቦታ ባለ
ቤት በመጣ ጊዜ እነዚህን ገባሮች ምን ያደርጋ
ቸዋል?” ፵፩እነርሱም፥ “ክፉዎችን በክፉ ያጠ
ፉቸዋል፤ ወይኑንም በየጊዜው ፍሬውን ለሚሰ
ጡት ለሌሎች ገባሮች ይሰጣል” አሉት።
፵፪ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥
“በመጻሕፍት ያለውን ያነበባችሁበት ጊዜ የለ
ምን? ግንበኞች የናቁአት ድንጋይ የማዕዘን ራስ
ሆነች፤ ይህቺም ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፤
ለዐይኖቻችንም ድንቅ ናት። ፵፫ስለዚህም እላ
ችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ
ትወሰዳለች፤ ፍሬዋንም ለሚያደርጉ ለአሕዛብ
ትሰጣለች። ፵፬በዚያችም ድንጋይ ላይ የሚወ
ድቅ ይቀጠቀጣል፤ በላዩ የምትወድቅበትንም
ትፈጨዋለች።”
፵፭የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም ምሳሌ
ዎቹን በሰሙ ጊዜ፥ ስለ እነርሱ እንደተናገረ
ዐወቁ። ፵፮ሊይዙትም ሲፈልጉ ሕዝቡን ፈሩአ
ቸው፤ በእነርሱ ዘንድ እንደ ነቢይ ነበርና።

## ምዕራፍ ፳፪

## ለልጁ ሰርግ ስለ አደረገው ንጉሥ ምሳሌ

(ሉቃ. ፲፬፥፲፭-፳፬)

፩ጌታችን ኢየሱስ ዳግመኛ መልሶ በምሳሌ
ነገራቸው፤ እንዲህም አለ፦ ፪“መንግሥተ ሰማ
ያት ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች።
፫ለሰርጉም የታደሙትን ይጠሩአቸው ዘንድ አገ
ልጋዮቹን ላከ፤ ሊመጡም አልወደዱም። ፬ዳግ
መኛም ሌሎችን አገልጋዮች እንዲህ ብሎ ላከ፤
የታደሙትን እንዲህ በሉአቸው፦ እነሆ ድግሴን
አዘጋጅቻለሁ፤ ኮርማዎቼና የሰቡ ከብቶቼ ታር

---

፳፩፥፴፪ ሉቃ. ፫፥፲፪፤ ፯፥፳፱-፴።  ፳፩፥፴፫ ኢሳ. ፭፥፩-፪።  ፳፩፥፵፪ መዝ. ፻፲፰፥፳፪-፳፫።

ደዋል፥ ሁሉም ተዘጋጅቶአል። ወደ ሰርጉ ኑ።
፭እነርሱ ግን ቸል ብለው ሄዱ፤ ወደ እርሻው
የሄደ አለ፤ ወደ ንግዱም የሄደ አለ። ፮የቀሩ
ትም አገልጋዮቹን ይዘው ሰደቡአቸው፤ ገደሉ
አቸውም፤፩ ፯ንጉሡም ተቈጣ፤ ጭፍሮቹንም
ልኮ እነዚያን ገዳዮች አጠፋ፤ ከተማቸውንም
አቃጠለ። ፰ከዚህም በኋላ አገልጋዮቹን እንዲህ
አላቸው፤ ሰርጌስ ተዘጋጅቶአል፤ ነገር ግን ለአ
ደምናቸው አልተገባቸውም። ፱እንግዲህ ወደ
ሜዳዎችና ወደ አደባባይም ሂዱና ያገኛችሁ
ትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ጥሩ። ፲እነዚያ አገልጋዮ
ችም ወደ መንገዶች ወጥተው ያገኙትን ሁሉ
ክፉዎችንም፥ በጎዎችንም ሰበሰቡ፤ የሰርጉም
ቤት በተጋባዦች ሞላ። ፲፩ንጉሡም ተጋባዦቹን
ሊያይ በገባ ጊዜ በዚያ የሰርግ ልብስ ያልለበሰ
አንድ ሰው አገኘ። ፲፪ወዳጄ ሆይ የሰርግ ልብስ
ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው፤ ያም
ሰው ምላሽ አጣ። ፲፫ከዚህም በኋላ ንጉሡ አገ
ልጋዮቹን፥ እጁንና እግሩን አስረው በውጭ
ወደ አለ ጨለማ ይጥሉት ዘንድ አዘዘ፤ በዚ
ያም ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። ፲፬የተ
ጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸ
ውና።”

## ለቄሣር ግብር ስለ መክፈል የቀረበ ጥያቄ

(ማር. ፲፪፥፲፫-፲፯፤ ሉቃ. ፳፥፳-፳፮)

፲፭ከዚህም በኋላ ፈሪሳውያን ሄዱ፤ በአነጋገ
ሩም ያጠምዱት ዘንድ ተማከሩ። ፲፮ደቀ መዛ
ሙርቶቻቸውንም ከሄሮድስ ቤተ ሰቦች ጋር
ወደ እርሱ ላኩ፤ እነርሱም እንዲህ አሉት፥
“መምህር ሆይ፥ አንተ እውነተኛ እንደ ሆንህ፥
የእግዚአብሔርንም መንገድ በእውነት እንደም
ታስተምር እናውቃለን፤ ማንንም አትፈራም፤
የሰውንም ፊት አይተህ አታደላም። ፲፯እንግ
ዲህ የሚገባውን ንገረን፤ ምን ትላለህ? ለቄ
ሣር ግብር መስጠት ይገባልን? ወይስ አይገ
ባም?” አሉት። ፲፰ጌታችን ኢየሱስም ክፋታቸ
ውን ዐወቀባቸውና፥ “እናንት ግብዞች ለምን
ትፈትኑኛላችሁ? የግብሩን ገንዘብ አሳዩኝ”
አላቸው። ፲፱ገንዘቡንም አመጡለት። ፳ጌታችን
ኢየሱስም፥ “ይህ መልኩ፥ ጽሕፈቱስ የማን
ነው?” አላቸው። ፳፩እነርሱም “የቄሣር ነው”
አሉት፤ እርሱም “እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር፤
የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ” አላ
ቸው። ፳፪ይህንም ሰምተው አደነቁ፤ ትተው
ትም ሄዱ።

## ትንሣኤ ሙታን የለም ስለሚሉ ስለ ሰዱቃውያን

(ማር. ፲፪፥፲፰-፳፯፤ ሉቃ. ፳፥፳፯)

፳፫በዚያችም ቀን ትንሣኤ ሙታን የለም
የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ መጡ። ፳፬እንዲ
ህም ብለው ጠየቁት፥ “መምህር ሆይ፥ ሙሴ
ልጅ ሳይወልድ የሞተ ሰው ቢኖር ወንድሙ
ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካለት
ብሎአል። ፳፭እንግዲህ ሰባት ወንድማማቾች
በእኛ ዘንድ ነበሩ፤ ታላቁም ሚስት አገባና ልጅ
ሳይወልድ ሞተ፤ ለወንድሙም ሚስቱን ተወ።
፳፮እንዲሁ ደግሞ ሁለተኛው፥ ሦስተኛውም፥
እስከ ሰባተኛው ድረስ። ፳፯ከሁሉም በኋላ ያቺ
ሴት ሞተች። ፳፰እንግዲህ ሙታን በሚነሡ
በት ጊዜ ከሰባቱ ለማንኛው ሚስት ትሆናለች?
ሁሉም አግብተዋት ነበርና።” ፳፱ጌታችን ኢየ
ሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “መጻሕፍት
ንና የእግዚአብሔርን ኀይል ባለ ማወቅ ትስታ
ላችሁ። ፴ሙታንስ በሚነሡበት ጊዜ በሰማያት
እንደ እግዚአብሔር መላእክት ሆነው ይኖራሉ
እንጂ አያገቡም፤ አይጋቡምም። ፴፩ስለ ሙታን
መነሣት ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ
እንዲህ ተብሎ የተነገረውን አላነበባችሁምን?
፴፪እኔ እግዚአብሔር የአብርሃም አምላክ የይ
ስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ እን
ግዲህ የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አም
ላክ አይደለም።” ፴፫ሕዝቡም ሰምተው ትምህ
ርቱን አደነቁ።

## ስለ ታላቂቱ ትእዛዝ

(ማር. ፲፪፥፳፰-፴፬፤ ሉቃ. ፲፥፳፭-፳፰)

፴፬ፈሪሳውያንም ሰዱቃውያንን ምላሽ እንዳሳ
ጣቸው በሰሙ ጊዜ በአንድነት ወደ እሱ ተሰ
በሰቡ። ፴፭ከመካከላቸውም አንድ ሕግ ዐዋቂ
ሊፈትነው ጠየቀው። ፴፮“መምህር ሆይ፥ ከኦ
ሪት ማንኛይቱ ትእዛዝ ትበልጣለች?” አለው።
፴፯ጌታችን ኢየሱስም እንዲህ አለው፥ “አምላ
ክህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም
ነፍስህ፥ በፍጹም ኀይልህ ውደደው። ፴፰ታላ

---

፩ ግእዙ “እርሱንም ሰደቡት” ይላል።

፳፪፥፲፫ ማቴ. ፰፥፲፪፤ ፳፭፥፴፤ ሉቃ. ፲፫፥፳፰። ፳፪፥፳፫ ሐ.ሥ. ፳፫፥፰። ፳፪፥፳፬ ዘዳ. ፳፭፥፭።
፳፪፥፴፪ ዘፀ. ፫፥፮። ፳፪፥፴፭-፵ ሉቃ. ፲፥፳፭-፳፰። ፳፪፥፴፯ ዘዳ. ፮፥፭።

ቂቱና የመጀመሪያይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።
፴፱የምትመስላት ሁለተኛይቱም ባልንጀራህን
እንደ ራስህ ውደድ የምትለው ናት። ፵አሪትና
ነቢያት ሁሉ በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸን
ተዋል።”

### ፈሪሳውያንን ስለ መጠየቁ

(ማር. ፲፪፥፴፭-፴፯፤ ሉቃ. ፳፥፵፩-፵፬)

፵፩ፈሪሳውያንም ተሰብስበው ሳሉ ጌታችን
ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው፡- ፵፪“ስለ ክር
ስቶስ ምን ትላላችሁ? የማን ልጅ ነው?” እነር
ሱም፥ “የዳዊት ልጅ ነው” አሉት። ፵፫ጌታችን
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፥ “እንግዲያ እርሱ
ራሱ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ እንዴት እንዲህ
አለ? ፵፬‘ጌታ ጌታዬን፡- ጠላቶችህን ከእግርህ
በታች እስከ አደርጋቸው ድረስ በቀኜ ተቀመጥ
አለው።’ ፵፭እርሱ ራሱ ዳዊት ‘ጌታዬ’ ያለው፥
እንግዲህ እንዴት ልጁ ይሆነዋል?” ፵፮አንድም
ቃል እንኳ ሊመልስለት የቻለ የለም፤ ከዚ
ያች ቀንም ጀምሮ ማንም ሊጠይቀው አል
ደፈረም።

## ምዕራፍ ፳፫

### ስለ ግብዞች ጻፎችና ስለ ፈሪሳውያን

(ማር. ፲፪፥፴፰-፴፱፤ ሉቃ. ፲፩፥፵፫)

፩ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ለሕዝቡና
ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው።
፪“ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ላይ
ተቀምጠዋል። ፫ስለዚህ ያስተማሩአችሁን ሁሉ
አድርጉ፤ ጠብቁትም፤ ነገር ግን እንደሚሠ
ሩት አታድርጉ፤ የሚያስተምሩትን አይሠሩት
ምና። ፬ትልቅና ከባድ ሸክም አስረው ሰውን
በጫንቃው ላይ ያሸክሙታል፤ እነርሱ ግን በጣ
ታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም። ፭የሚሠሩ
ትን ሥራቸውን ሁሉ ለሰው ሊታዩ ይሠሩታ
ልና፤ አሸንክታባቸውን ይዘረጋሉ፤ የልብሳቸው
ንም ዘርፍ ያስረዝማሉ። ፮በማዕድ ጊዜ በክብር
ስፍራ፥ በምኵራብም በፊተኛው ወንበር መቀ
መጥን ይወድዳሉ። ፯በገበያም ሰዎች እጅ እንዲ
ነሱአቸውና መምህር ሆይ፥ እንዲሉአቸው ይወ
ድዳሉ። ፰እናንተስ መምህራን ተብላችሁ አት
ጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ነውና፤ እናንተስ
ሁላችሁ ወንድማማቾች ናችሁ። ፱የሰማዩ አባታ
ችሁ አንድ ነውና በምድር ላይ ማንንም አባት
ብላችሁ አትጥሩ። ፲ሊቃችሁ አንድ፤ እርሱም
ክርስቶስ ነውና በምድር ላይ ሊቃውንት ተብ
ላችሁ አትጠሩ፤ ፲፩ነገር ግን ከእናንተ የሚበል
ጠው አገልጋይ ይሁናችሁ። ፲፪ራሱን ከፍ ከፍ
የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፤ ራሱንም ዝቅ
የሚያደርግ ሁሉ ይከብራልና።
፲፫“እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥
ጸሎታችሁን በማብዛት ምክንያት የመበለቶችን
ገንዘብ ስለምትበሉ ወዮላችሁ! ስለዚህ ጽኑ
ፍርድን ትቀበላላችሁ። ፲፬እናንተ ግብዞች ጻፎ
ችና ፈሪሳውያን፥ መንግሥተ ሰማያትን በሰው
ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ! እናንተም አትገ
ቡም፤ የሚገቡትንም ከመግባት ትከለክሉአቸ
ዋላችሁ። ፲፭እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳው
ያን፥ አንድን ሰው ለማሳመን ባሕሩንና የብ
ሱን ስለምትዞሩ ወዮላችሁ! ካመነም በኋላ ከእ
ናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የገሃነም ልጅ ታደ
ርጉታላችሁ። ፲፮በቤተ መቅደስ የሚምል ኀጢ
አት የለበትም፤ በቤተ መቅደስ ወርቅ የሚምል
ግን ይበድላል የምትሉ ዕውራን መሪዎች እና
ንተ ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ወዮላችሁ! ፲፯እና
ንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች፥ የትኛው ይበል
ጣል? ወርቁ ነውን? ወይስ ወርቁን የሚቀድ
ሰው ቤተ መቅደስ? ፲፰ደግማችሁም በመሠዊ
ያው የሚምል አይበድልም፤ በላዩ በአለው በመ
ሥዋዕቱ የሚምል ግን ይበድላል ትላላችሁ።
፲፱እናንተ ሰነፎችና ዕውራን፥ የትኛው ይበል
ጣል? መሥዋዕቱ ነውን? ወይንስ መሥዋዕቱን
የሚቀድሰው መሠዊያው? ፳በመሠዊያው የሚ
ምል በእርሱ ይምላል፤ በእርሱ ላይም ባለው
ሁሉ ይምላል። ፳፩በቤተ መቅደስም የሚምል
በእርሱና በውስጡ በሚኖረው ሁሉ ይምላል።
፳፪በሰማይ የሚምልም በእግዚአብሔር ዙፋንና
በእርሱ ላይ በተቀመጠው ይምላል።
፳፫“እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ከአ
ዝሙድና ከእንስላል፥ ከከሙንም ዐሥራትን ስለ
ምታወጡ፥ በኦሪት ያለውንም ታላቁን ትእዛዝ፥
ፍርድንና ምጽዋትን፥ ታማኝነትንም ስለምት
ተዉ ወዮላችሁ! ይህን ልታደርጉ፥ ያንንም ላት
ተዉ ይገባ ነበር። ፳፬እናንተ ዕውራን መሪዎች፥
ትንኙን የምታጠሩ፥ ግመልንም የምትውጡ፤

---

፳፪፥፴፱ ዘሌ. ፲፱፥፲፰። ፳፪፥፵፬ መዝ. ፻፲፥፩። ፳፫፥፭ ማቴ. ፮፥፩፤ ዘኁ. ፲፭፥፴፰፤ ዘዳ. ፮፥፰።
፳፫፥፲፩ ማቴ. ፳፥፳፮-፳፯፤ ማር. ፱፥፴፭፤ ፲፥፵፫-፵፬፤ ሉቃ. ፳፪፥፳፮። ፳፫፥፲፪ ሉቃ. ፲፬፥፲፩፤ ፲፰፥፲፬።
፳፫፥፳፪ ኢሳ. ፷፮፥፩፤ ማቴ. ፭፥፴፬። ፳፫፥፳፫ ዘሌ. ፳፯፥፴።

፳፭“እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥
በውስጡ ቅሚያንና ስስትን ተሞልቶ ሳለ የጽ
ዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለምታጥቡ ወዮላ
ችሁ! ፳፮አንተ ዕውር ፈሪሳዊ፥ ውጭው ንጹሕ
ይሆን ዘንድ አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን
ውስጡን እጠበው። ፳፯በውጫቸው አምረው
የሚታዩ፥ በውስጣቸው ግን የሙታን አጥንት
ንና ርኵሰትን ሁሉ የተመሉ፥ የተለሰኑ መቃ
ብሮችን የምትመስሉ እናንተ ግብዞች ጻፎችና
ፈሪሳውያን፥ ወዮላችሁ! ፳፰እንዲሁ እናንተም
በውጭ ለሰው ጻድቃን ትመስላላችሁ፤ በውስ
ጣችሁ ግን ዐመጽንና ግብዝነትን፥ ቅሚያንም
የተሞላችሁ ናችሁ።

፳፱“የነቢያትን መቃብር የምትሠሩ፥ የጻድቃ
ንንም መቃብር የምታስጌጡ እናንተ ግብዞች
ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ወዮላችሁ! ፴በአባቶቻ
ችን ዘመን ኖረን ቢሆን በነቢያት ደም ከእነርሱ
ጋር ባልተባበርንም ነበር ትላላችሁ። ፴፩እነሆ፥
የነቢያት ገዳዮች ልጆች እንደ ሆናችሁ እናንተ
ራሳችሁ ትመሰክራላችሁ። ፴፪እናንተም የአባቶ
ቻችሁን መስፈሪያ ሙሉ። ፴፫እናንተ እባቦች፥
የእፉኝት ልጆች፥ ከገሃነም ፍርድ ልታመልጡ
እንዴት ትችላላችሁ? ፴፬ስለዚህ እነሆ፥ እኔ
ነቢያትንና ጠቢባንን፥ ጻፎችንም ወደ እናንተ
እልካለሁ፤ ከእነርሱም ትገድላላችሁ፤ ትሰቅላ
ላችሁም፤ ከእነርሱም በምኵራባችሁ ትገርፋላ
ችሁ፤ ከከተማም ወደ ከተማ ታሳድዱአቸዋላ
ችሁ። ፴፭ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ
መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላች
ሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም
ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቃን ሁሉ
ደም በእናንተ ላይ ይደርስ ዘንድ። ፴፮እውነት
እላችኋለሁ፤ ይህ ሁሉ በዚች ትውልድ ይደ
ርስባታል።

፴፯“ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ነቢያ
ትን የምትገድል፥ ወደ እርስዋ የተላኩትንም
የምትደበድብ፥ ዶሮ ጫጭቶችዋን በክንፎችዋ
ውስጥ እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ
ዘንድ ምን ያህል ወደድሁ! እናንተ ግን እንቢ
አላችሁ። ፴፰እነሆ ቤታችሁ ምድረ በዳ ሆኖ
ይቀርላችኋል። ፴፱እውነት እላችኋለሁ፤ ‘በእ
ግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው’ እስ
ከምትሉበት ጊዜ ድረስ ከዛሬ ጀምሮ አታዩ
ኝም።”

## ምዕራፍ ፳፬

### ስለ ዳግመኛ ምጽአቱና ስለ ዓለም ፍጻሜ ምልክቶች

(ማር. ፲፫፥፩-፪፤ ሉቃ. ፳፩፥፭-፯)

፩ጌታችን ኢየሱስም ከቤተ መቅደስ ወጥቶ
ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀር
በው የቤተ መቅደሱን የሕንጻ አሠራር አሳ
ዩት። ፪ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላ
ቸው፥ “ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት
እላችኋለሁ፤ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ
በዚህ አይቀርም።” ፫በደብረ ዘይትም ተቀ
ምጦ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ
እርሱ ቀረቡና እንዲህ አሉት፥ “ንገረን፤ ይህ
መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለሙ ፍጻ
ሜስ ምልክቱ ምንድን ነው?” ፬ጌታችን ኢየ
ሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ “የሚያስታ
ችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ፤ ፭ብዙዎች እኔ
ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙ
ዎችንም ያስታሉ። ፮ጦርነትን፥ የጦርነትንም
ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ
ነውና ተጠንቀቁ፤ አትደንግጡ፤ ነገር ግን ፍጻ
ሜው ገና ነው። ፯ሕዝብ በሕዝብ ላይ፥ መንግ
ሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣሉ፤ በየሀገሩም
ረኀብ፥ ቸነፈርም፥ የምድር መናወጥም ይሆ
ናል። ፰እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ
ናቸው። ፱ያንጊዜም ለመከራ አሳልፈው ይሰ
ጡአችኋል፤ [፩] ይገድሉአችኋልም፤ ስለ ስሜም
በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።
፲ያንጊዜም ብዙዎች ሃይማኖታቸውን ይለው
ጣሉ፤ እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣ
ጣሉ፤ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ። ፲፩ብዙዎች
ሐሰተኞች ነቢያትም ይመጣሉ፤ ብዙዎችንም
ያስታሉ። ፲፪ከዐመፅም ብዛት የተነሣ ፍቅር
ከብዙዎች ዘንድ ትጠፋለች። ፲፫እስከ መጨረ
ሻው የሚታገሥ ግን እርሱ ይድናል። ፲፬በአ
ሕዛብ ሁሉ ላይ ምስክር ሊሆን ይህ የመንግ
ሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ያንጊ
ዜም ፍጻሜ ይደርሳል።

---

፩ ግእዙ “ይቀሥፉክሙ” የሚል ይጨምራል።

፳፫፥፳፯ ሐ.ሥ. ፳፫፥፫። ፳፫፥፴፫ ማቴ. ፫፥፯፤ ፲፪፥፴፬፤ ሉቃ. ፫፥፯።

፳፫፥፴፭ ዘፍ. ፬፥፰፤ ፪ዜ.መ. ፳፬፥ ፳-፳፩። ፳፫፥፴፰ ኤር. ፳፪፥፭። ፳፫፥፴፱ መዝ. ፻፲፰፥፳፮።

፳፬፥፱ ማቴ. ፲፥፳፪። ፳፬፥፲፫ ማቴ. ፲፥፳፪።

፲፭“እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን
የመፍረሱን የርኵሰት ምልክት በተቀደሰ ቦታ
ቆሞ ባያችሁት ጊዜ አንባቢው ያስተውል።
፲፮ያንጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች ይሽሹ።
፲፯በሰገነት ያለም በቤት ውስጥ ያለውን ያነሣ
ዘንድ አይውረድ። ፲፰በእርሻም ያለ ልብሱን
ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ። ፲፱ነገር
ግን በዚያ ወራት ለፀነሱና ለሚያጠቡ ወዮላ
ቸው! ፳ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም
በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ። ፳፩ያንጊዜ ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ያልተደረገ፥ ከእን
ግዲህም ወዲያ የማይደረግ ታላቅ መከራ ይሆ
ናል። ፳፪እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ኖሮ ሥጋ የለ
በሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን ስለ ተመረ
ጡት እነዚያ ቀኖች ያጥራሉ። ፳፫ያንጊዜ እነሆ፥
ክርስቶስ በዚህ አለ፤ ወይም በዚያ አለ የሚላ
ችሁ ሰው ቢኖር አትመኑ። ፳፬ሐሰተኞች መሢ
ሖችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻላቸ
ውስ የተመረጡትን እንኳ ለማሳት ታላላቅ ተአ
ምራትንና ድንቅ ሥራን ይሠራሉ። ፳፭እነሆ፥
አስቀድሜ ነገርኋችሁ። ፳፮እነሆ፥ በምድረ በዳ
አለ ቢሉአችሁ አትውጡ፤ እነሆም፥ በቤት
ውስጥ ነው ቢሉአችሁ አትመኑ። ፳፯መብረቅ
ከምሥራቅ እንደሚወጣ፥ እስከ ምዕራብም እን
ደሚታይ የሰው ልጅም መምጣት እንዲሁ ይሆ
ናል። ፳፰ገደላ ባለበት አሞሮች በዚያ ይሰበሰ
ባሉ።

፳፱“ከእነዚያም ቀኖች መከራ በኋላ፥ ወዲያ
ውኑ ፀሐይ ይጨልማል፤ ጨረቃም ብርሃኑን
አይሰጥም፤ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፤
የሰማያት ኀይልም ይናወጣል። ፴በዚያም ወራት
የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፤ ያንጊ
ዜም የምድር አሕዛብ ሁሉ ያለቅሳሉ፤ የሰው
ልጅንም በኀይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና
ሲመጣ ያዩታል። ፴፩መላእክቱንም ከታላቅ የመ
ለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤ የተመረጡት
ንም ከሰማይ ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ
መዐዝን ይሰበስቧቸዋል።

፴፪“ምሳሌውንም ከበለስ ዕወቁ፤ ጫፍዋ የለ
ሰለሰ፥ ቅጠልዋም የለመለመ እንደሆነ እነሆ
መከር እንደ ደረሰ ታውቃላችሁ። ፴፫እንዲሁ
እናንተ ይህን ሁሉ ባያችሁ ጊዜ፥ እንደ ቀረ
በና በዳጃፍ እንዳለ ዕወቁ። ፴፬እውነት እላችኋ
ለሁ፤ ይህ ሁሉ እስኪደረግ ድረስ ይቺ ትው
ልድ አታልፍም። ፴፭ሰማይና ምድር ያልፉሉ፥
ቃሌ ግን አያልፍም።

## ስለ ሰዓትዋና ስለ ዕለቲቱ

(ማር. ፲፫፥፴፪-፴፯፤ ሉቃ. ፲፯፥፳፮-፴)

፴፮“ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን
ከአብ ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፥
ወልድም ቢሆን የሚያውቃት የለም። ፴፯በኖኅ
ዘመንም እንደ ሆነ የሰው ልጅ አመጣጡ እን
ዲሁ ይሆናል። ፴፰ያንጊዜ ከጥፋት ውኃ በፊት፥
ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ ሲበ
ሉና ሲጠጡ፥ ሲያገቡና ሲጋቡ እንደ ነበሩ፥
፴፱የጥፋት ውኃ መጥቶ ሁሉን እስከ አጠፋ
በት ጊዜ ድረስ እንደ አላወቁ፤ የሰው ልጅም
አመጣጡ እንዲሁ ይሆናል። ፵ያንጊዜ ሁለት
ሰዎች በአንድ እርሻ ላይ ይኖራሉ፤ አንዱን
ይወስዳሉ፤ ሁለተኛውንም ይተዋሉ። ፵፩ሁለት
ሴቶች በአንድ ወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱን
ይወስዳሉ ሁለተኛይቱንም ይተዋሉ፤ ሁለት
ሰዎች በአንድ አልጋ ይተኛሉ፤ አንዱን ይወ
ስዳሉ፤ ሁለተኛውንም ይተዋሉ።፩ ፵፪እንግዲህ
ትጉ፤ ጌታችሁ በምን ሰዓት እንደሚመጣ አታ
ውቁምና።

፵፫“ነገር ግን ይህን ዕወቁ፤ ባለቤት ሌባ የሚ
መጣበትን ሰዓት ቢያውቅ ተግቶ በጠበቀ ነበር፤
ቤቱም እንዲቈፈር ባልተወ ነበር። ፵፬ስለዚህ
እናንተም ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፤ የሰው
ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።

፵፭“እንግዲህ ምግባቸውን በየጊዜዉ ይሰጣ
ቸው ዘንድ ጌታው በቤተሰቦቹ ላይ የሚሾመው
ታማኝና ብልህ አገልጋይ ማን ነው? ፵፮ጌታዉ
በመጣ ጊዜ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ
አገልጋይ ብፁዕ ነው። ፵፯እውነት እላችኋለሁ፤
በገንዘቡ ሁሉ ላይ ይሾመዋል። ፵፰ነገር ግን
ያ ክፉ አገልጋይ፦ ‘ጌታዬ ከመምጣት ይዘገ
ያል’ ብሎ በልቡ ቢያስብ፥ ፵፱ባልንጀሮቹን አገ
ልጋዮች ቢደበድብ፥ ከሰካሮች ጋርም ቢበላና
ቢጠጣ፥ ፶የዚያ አገልጋይ ጌታዉ ባልጠረጠው

---

፩ “ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይተኛሉ፤ አንዱን ይወስዳሉ፤ ሁለተኛውንም ይተዋሉ” የሚለው በግሪኩ የለም።

፳፬፥፲፭ ዳን. ፱፥፳፯፤ ፲፩፥፴፩፤ ፲፪፥፲፩። ፳፬፥፲፯-፲፰ ሉቃ. ፲፯፥፴፩ ፳፬፥፳፩ ዳን. ፲፪፥፩ ራእ. ፯፥፲፬። ፳፬፥፳፮-፳፯፤ ሉቃ. ፲፯፥፳፫-፳፬። ፳፬፥፳፰ ሉቃ. ፲፯፥፴፯። ፳፬፥፳፱ ኢሳ. ፲፫፥፲፤ ፴፬፥፬፤ ሕዝ. ፴፪፥፯ ኢዩ. ፪፥፲፥፴፩፤ ፫፥፲፭፤ ራእ. ፮፥፲፪-፲፫። ፳፬፥፴፥ ዳን. ፯፥፲፫፤ ዘካ ፲፪፥፲-፲፬፤ ራእ. ፩፥፯። ፳፬፥፴፯ ዘፍ. ፮፥፭-፰። ፳፬፥፴፱ ዘፍ. ፯፥፮-፳፬። ፳፬፥፵፫-፵፬ ሉቃ. ፲፪፥ ፴፱-፵።

ዕለትና ባላወቀው ሰዓት ይመጣል። ፶፩ከመካከ
ሉም ይሰነጥቀዋል፤ ዕድሉንም ከግብዞች ጋር
ያደርግበታል፤ በዚያም ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት
ይሆናል።

## ምዕራፍ ፳፭

### ስለ ዐሥሩ ደናግል

፩“ያንጊዜም መንግሥተ ሰማያት መብራታ
ቸውን ይዘው ሙሽራውን ለመቀበል የወጡ
ዐሥሩን ደናግል ትመስላለች። ፪ከእነርሱም
ውስጥ አምስቱ ሰነፎች፥ አምስቱም ልባሞች
ነበሩ። ፫ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ዘይት
አልያዙም ነበር። ፬ልባሞቹ ግን ከመብራታ
ቸው ጋር በማሰሮቻቸው ዘይት ይዘው ነበር።
፭ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉም አንቀላፉና
ተኙ። ፮መንፈቀ ሌሊት በሆነም ጊዜ ‘እነሆ
ሙሽራ መጣ፤ ልትቀበሉት ውጡ’ የሚል
ጩኸት ሆነ። ፯ያንጊዜ እነዚያ ደናግል ሁሉ
ነቁና መብራታቸውን አዘጋጁ። ፰እነዚያ ሰነ
ፎችም ልባሞችን፡- መብራታችን ሊጠፋብን
ነውና ከዘይታችሁ ስጡን አሉአቸው። ፱ልባሞ
ችም፡- ለእኛና ለእናንተ የሚበቃ የለም፤ ነገር
ግን ወደሚሸጡ ሂዱና ለራሳችሁ ግዙ ብለው
መለሱላቸው። ፲ሊገዙም እንደ ሄዱ ሙሽራው
መጣ፤ እነዚያም የተዘጋጁት ከእርሱ ጋር ወደ
ሰርጉ ገቡ፤ ደጁም ተዘጋ። ፲፩በኋላም እነዚያ
ደናግል መጥተው፡- አቤቱ አቤቱ ክፈትልን
አሉ። ፲፪እርሱ ግን መልሶ፡- እውነት እላች
ኋለሁ፤ አላውቃችሁም አላቸው። ፲፫እንግዲህ
ትጉ፤ የሰው ልጅ የሚመጣባትን ቀኒቱንና ሰዓ
ቲቱን አታውቁምና።

### ምሳሌ ስለ መክሊቶች
(ሉቃ. ፲፱፥፲፩-፳፯)

፲፬“መንገድ እንደሚሄድ፥ አገልጋዮቹንም
ጠርቶ ሊያተርፉበት ገንዘቡን እንደ ሰጣቸው
ሰው እንዲሁ ይሆናልና፤ ፲፭ለእያንዳንዱ እንደ
ችሎታው ለአንዱ አምስት፥ ለአንዱ ሁለት፥
ለአንዱም አንድ ሰጠና ወዲያውኑ ሄደ። ፲፮ያ
አምስት መክሊት የተቀበለውም ሄደ፤ ነግዶም
ሌላ አምስት መክሊት አተረፈ። ፲፯እንዲሁም
ሁለት የተቀበለው ሌላ ሁለት አተረፈ። ፲፰አንድ
መክሊት የተቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቈፈ
ረና የጌታዉን ወርቅ ቀበረ። ፲፱ከብዙ ጊዜም
በኋላ የእነዚያ አገልጋዮች ጌታ ተመልሶ ተቈ
ጣጠራቸው። ፳አምስት መክሊት የተቀበለውም
ቀረበና፡- አቤቱ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ
ነበር፤ እነሆ ሌላ አምስት አተረፍሁ ብሎ አም
ስት መክሊት አስረከበ። ፳፩ጌታውም፡- መል
ካም፥ አንተ የታመንህ በጎ አገልጋይ በጥቂት
የታመንህ ስለ ሆንህ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ
ጌታህ ደስታ ግባ አለው። ፳፪ሁለት መክሊት
የተቀበለውም መጥቶ፡- አቤቱ፥ ሁለት መክሊ
ትን ሰጥተኸኝ አልነበረምን? እነሆ ሌላ ሁለት
መክሊትን አተረፍሁ አለ። ፳፫ጌታውም፡- መል
ካም፥ አንተ የታመንህ በጎ አገልጋይ በጥቂቱ
የታመንህ ስለ ሆንህ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ
ጌታህ ደስታ ግባ አለው። ፳፬አንድ መክሊት
የተቀበለውም መጣና እንዲህ አለ፡- አቤቱ፥
አንተ ካልዘራህበት የምታጭድ፥ ካልበተንህበ
ትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው እንደ ሆንህ
አውቃለሁ፤ ፳፭ስለ ፈራሁም ሄድሁና መክሊት
ህን በምድር ውስጥ ቀበርሁ፤ እንግዲህ እነሆ፥
መክሊትህ። ፳፮ጌታውም መልሶ አለው፡- አንተ
ክፉና ሰነፍ አገልጋይ፥ እኔ ካልዘራሁበት የማ
ጭድ፥ ካልበተንሁበትም የምሰበስብ ጨካኝ
ሰው እንደ ሆንሁ ታውቃለህን? ፳፯ገንዘቤን ለለ
ዋጮች መስጠት በተገባህ ነበር፤ እኔም ራሴ
መጥቼ ገንዘቤን ከትርፉ ጋር በወሰድሁ ነበር።
፳፰ከዚያ የቆሙትንም እንዲህ አላቸው፤ ይህን
መክሊት ከእርሱ ተቀብላችሁ ዐሥር መክሊት
ላለው ስጡት። ፳፱ላለው ሁሉ ይሰጡታልና፤
ይጨምሩለታልም፤ ለሌለው ግን ያንኑ ያለውን
ይወስዱበታል። ፴ክፉውን አገልጋይ ግን፥ ልቅ
ሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት በውጭ ወደ አለ
ጨለማ አውጡት።

### ስለ ክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት

፴፩“የሰው ልጅ በጌትነቱ ቅዱሳን መላእክትን
ሁሉ አስከትሎ በሚመጣበት ጊዜ፥ ያንጊዜ
በጌትነቱ ዙፋን ይቀመጣል። ፴፪አሕዛብ ሁሉ
በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎችን ከፍየሎች
እንደሚለይ እየራሳቸው ይለያቸዋል። ፴፫በጎችን
በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል። ፴፬ያን
ጊዜ ንጉሡ በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፡-

፳፭፥፩ ሉቃ. ፲፪-፴፭። ፳፭፥፲፩-፲፪ ሉቃ. ፲፫፥፳፭። ፳፭፥፲፬-፴ ሉቃ. ፲፱፥፲፩-፳፯።
፳፭፥፳፱ ማቴ. ፲፫፥፲፪፤ ማር. ፬፥፳፭፤ ሉቃ. ፰፥፲፰። ፳፭፥፴ ማቴ. ፰፥፲፪፤ ፳፪፥፲፫፤ ሉቃ. ፲፫፥፳፰።
፳፭፥፴፩ ማቴ. ፲፮፥፳፯፤ ፲፱፥፳፰።

እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ዓለም ሳይፈጠር[፩] የተ
ዘጋጀላችሁን መንግሥት ትወርሱ ዘንድ ኑ።
፴፭ ተርቤ አብልታችሁኛልና፤ ተጠምቼም አጠ
ጥታችሁኛልና፤ እንግዳም ሆኜ ተቀብላችሁኛ
ልና። ፴፮ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፤ ታምሜም
ጐብኝታችሁኛልና፤ ታስሬም ወደ እኔ መጥታ
ችሁ ጠይቃችሁኛልና። ፴፯ ያንጊዜም ጻድቃን
መልሰው እንዲህ ይሉታል፦ አቤቱ፥ መቼ ተር
በህ አይተንህ አበላንህ? መቼስ ተጠምተህ አይ
ተንህ አጠጣንህ? ፴፰ መቼስ እንግዳ ሆነህ አይ
ተንህ ተቀበልንህ? መቼስ ታርዘህ አለበስንህ?
፴፱ መቼስ ታመህ አይተንህ ጐበኘንህ? መቼስ
ታስረህ ወደ አንተ መጥተን ጠየቅንህ? ፵ ከዚ
ህም በኋላ ንጉሡ መልሶ እንዲህ ይላቸዋል፦
እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ ካመኑ ከእነዚህ
ከታናናሾች ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁትን
ሁሉ ለእኔ አደረጋችሁት። ፵፩ ከዚህም በኋላ በግ
ራው ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የተረ
ገማችሁ፥ ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ ወደተዘ
ጋጀው ወደ ዘለዓለም እሳት ሂዱ። ፵፪ ተርቤ አላ
በላችሁኝምና፤ ተጠምቼም አላጠጣችሁኝምና።
፵፫ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፤ ታርዤም
አላለበሳችሁኝምና፤ ታምሜም አልጐበኛችሁኝ
ምና፤ ታስሬም ወደ እኔ መጥታችሁ አልጠየ
ቃችሁኝምና። ፵፬ ያንጊዜም በግራው ያሉት እን
ዲህ ብለው ይመልሳሉ፦ አቤቱ መቼ ተርበህ
ወይስ ተጠምተህ፥ ወይስ እንግዳ ሆነህ፥ ወይስ
ታርዘህ፥ ወይስ ታመህ፥ ወይስ ታስረህ አይ
ተን አላገለገልንህ? ፵፭ ከዚህም በኋላ ንጉሡ እን
ዲህ ብሎ ይመልስላቸዋል፥ "እውነት እላችኋ
ለሁ ከእነዚህ ከታናናሾች ለአንዱ ያላደረጋች
ሁትን ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም። ፵፮ እነዚ
ያም ወደ ዘለዓለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ
ዘለዓለም ሕይወት ይሄዳሉ።"

## ምዕራፍ ፳፮

### ስለ አይሁድ ምክር

(ማር. ፲፬፥፩፡፪፤ ዮሐ. ፲፩፥፵፭-፶፫)

፩ እንዲህም ሆነ፤ ጌታችን ኢየሱስ ይህን ሁሉ
ነገር ከፈጸመ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ
አላቸው፦ ፪ "ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እን
ደሚሆን ታውቃላችሁ፤ የሰው ልጅም ሊሰ
ቀል ተላልፎ ይሰጣል።" ፫ ከዚህም በኋላ፥ የካ
ህናቱ አለቆች ጻፎችና የሕዝብ ሽማግሌዎች
ስሙ ቀያፋ በሚባለው በሊቀ ካህናቱ ግቢ ተሰ
በሰቡ። ፬ ጌታችንን ኢየሱስንም በተንኰል ይዘው
ይገድሉት ዘንድ ተማከሩ። ፭ "ነገር ግን፥ በሕ
ዝቡ መካከል ሁከት እንዳይነሣ በበዓል አይ
ሁን" አሉ።

### ጌታችንን ሽቱ ስለ ቀባችው ሴት

(ማር. ፲፬፥፫-፱፤ ዮሐ. ፲፪፥፩-፰)

፮ ጌታችን ኢየሱስም በቢታንያ በለምጻሙ በስ
ምዖን ቤት ሳለ፥ ፯ ዋጋው እጅግ ብዙ የሆነ
ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ብርሌ የያዘች ሴት
ወደ እርሱ መጣች፤ ጌታችን ኢየሱስም በማ
ዕድ ተቀምጦ ሳለ በራሱ ላይ አፈሰሰችው።
፰ ደቀ መዛሙርቱም ይህን ባዩ ጊዜ ተቈጥተው
እንዲህ አሉ፥ "ይህች ሴት ለምን ይህን ያህል
ሽቱ አጠፋች?[፪] ፱ ይህ በብዙ ዋጋ ተሽጦ ለድ
ሆች ምጽዋት ይሰጥ ዘንድ ይቻል ነበርና።"
፲ ጌታችን ኢየሱስም ዐወቀባቸውና እንዲህ አላ
ቸው፥ "ይህችን ሴት ለምን ታደክሙአታላ
ችሁ? ለእኔ መልካም ሥራ ሠርታልኛለችና።
፲፩ ድሆችንስ ዘወትር ታገኙአቸዋላችሁ፤ በወደዳ
ችሁም ጊዜ በጎ ታደርጉላቸዋላችሁ፤ እኔን ግን
ዘወትር የምታገኙኝ አይደለም። ፲፪ እርስዋ ይህን
በራሴ ላይ ያፈሰሰችውን ሽቱ ለቀብሬ አደረገ
ችው። ፲፫ እውነት እላችኋለሁ፤ ይህ ወንጌል በዓ
ለሙ ሁሉ በሚሰበክበት ቦታ ይህች ሴት ያደ
ረገችው ለእርስዋ መታሰቢያ ሆኖ ይነገራል።"

### የአስቆሮቱ ሰው ይሁዳ ጌታን እንዳስያዘው

(ማር. ፲፬፥፲-፲፩፤ ሉቃ. ፳፪፥፫-፮)

፲፬ ከዚህም በኋላ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙ
ርት አንዱ ይሁዳ የሚባለው የአስቆሮቱ ሰው
ወደ ካህናት አለቆች ሄደ። ፲፭ "ምን ትሰጡኛላ
ችሁ? እኔም አሳልፌ እሰጣችኋለሁ" አላቸው።
እነርሱም ሠላሳ ብር መዘኑለት[፫] ፲፮ ከዚያ ጊዜ
ጀምሮ ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ ምቹ
ጊዜ ይሻ ነበር።

---

፩ ግሪኩ "ዐለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ..." ይላል።

፪ ግሪኩ "ይህ ጥፋት ለምንድነው?" ይላል።

፫ አንዳንድ የግሪክና የግእዝ ዘርዕ "... ሠላሳ ብር ሊሰጡት ከእርሱ ጋር ተስማሙ" ይላል።

፳፭፥፵፮ ዳን. ፲፪፥፪። ፳፮፥፪ ዘፀ. ፲፪፥፩-፳፯። ፳፮፥፯ ሉቃ. ፯፥ ፴፯-፴፰። ፳፮፥፲፩ ዘዳ. ፲፭፥፲፩።
፳፮፥፲፭ ዘካ. ፲፩፥፲፪።

### ስለ ፋሲካ በዓል

(ማር. ፲፬፥፲፪-፳፩፤ ዮሐ. ፲፫፥፳፩-፴)

፲፯ከፋሲካም በመጀመሪያው ቀን ደቀ መዛ
ሙርቱ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ቀርበው፥ "ፋሲ
ካን ትበላ ዘንድ በየት ልናዘጋጅልህ ትወዳ
ለህ?" አሉት። ፲፰ጌታችን ኢየሱስም አላቸው፥
"ወደ ከተማ ወደ እገሌ ዘንድ ሂዱ፤ መም
ህር፡- ጊዜዬ ቀርቧልና ከደቀ መዛሙርቶቼ
ጋር ፋሲካን በአንተ ዘንድ አደርጋለሁ ብሎ
ሃል" በሉት። ፲፱ደቀ መዛሙርቱም ጌታችን
ኢየሱስ እንደ አዘዛቸው አደረጉ፤ ፋሲካንም
አዘጋጁ።

### ስለ አስያዘው ሰው የተናገረው ነገር

፳በመሸም ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛ
ሙርቱ ጋር በማዕድ ተቀመጠ። ፳፩ሲበሉም፥
"እውነት እላችኋለሁ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ
ይሰጠኛል" አላቸው። ፳፪እጅግም አዘኑ፤ እያ
ንዳንዱም "አቤቱ፥ ምናልባት እኔ እሆን?"
ይሉ ጀመር። ፳፫እርሱም መልሶ እንዲህ አለ፥
"ከእኔ ጋር እጁን ወደ ወጭቱ የሚያገባ እርሱ
አሳልፎ ይሰጠኛል። ፳፬የሰው ልጅስ ስለ እርሱ
እንደ ተጻፈ ይሄዳል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ
አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያ
ሰው ባልተወለደ በተሻለው ነበር።" ፳፭አሳልፎ
የሚሰጠው ይሁዳም መልሶ፥ "መምህር ሆይ፥
እንግዲያ እኔ እሆን?" አለ፤ ጌታችን ኢየሱ
ስም፥ "አንተ ራስህ አልህ" አለው።

### ስለ ምሥጢረ ቍርባን ሥርዐት

(ማር. ፲፬፥፳፪-፳፮፤ ሉቃ. ፳፪፥፲፬-፳)

፳፮ሲበሉም ጌታችን ኢየሱስ ኅብስቱን አን
ሥቶ፥ ባረከ፤ ቈረሰ፤ ለደቀ መዛሙርቱም
"ይህ ሥጋዬ ነው እንኩ ብሉ" ብሎ ሰጠ።
፳፯ጽዋዉንም አንሥቶ አመስግኖ ሰጣቸው፤
እንዲህም አለ፥ "ሁላችሁም ከእርሱ ጠጡ።
፳፰ኀጢአትን ለማስተስረይ፤ ስለ ብዙዎች
የሚፈስ፥ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።
፳፱በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር አዲሱን
እስከምጠጣበት እስከዚያች ቀን ድረስ ከዛሬ
ጀምሮ ከዚህ የወይን ፍሬ አልጠጣም።"
፴መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት
ወጡ።

### ስለ እረኛው መሞትና ስለ በጎቹ መበተን

(ማር. ፲፬፥፳፯-፴፩፤ ዮሐ. ፲፫፥፴፮-፴፰)

፴፩ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ
አላቸው፤ "በዚች ሌሊት ሁላችሁም ትከዱ
ኛላችሁ፤ መጽሐፍ፡- እረኛውን እገድለዋለሁ፤
በጎቹም ይበተናሉ ብሎአልና። ፴፪ከተነሣሁም
በኋላ ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ።" ፴፫ጴጥሮ
ስም መልሶ፥ "ሁሉም ቢክዱህ እንኳ እኔ ከቶ
አልክድህም" አለው። ፴፬ጌታችን ኢየሱስም፥
"እውነት እልሃለሁ በዚች ሌሊት ዶሮ ሳይ
ጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ" አለው። ፴፭ጴጥ
ሮስም፥ "ከአንተ ጋር እሞታለሁ እንጂ አልክ
ድህም" አለው፤ ደቀ መዛሙርቱም ሁሉ እንደ
እርሱ አሉ።

### ጌታችን ኢየሱስ በጌቴሴማኒ እንደ ጸለየ

(ማር. ፲፬፥፴፪-፵፪፤ ሉቃ. ፳፪፥፴፱-፵፮)

፴፮ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ከእነርሱ
ጋር ጌቴሴማኒ ወደሚባል ቦታ ሄደ፤ ደቀ መዛ
ሙርቱንም፥ "ወደዚያ ሄጄ እስክጸልይ ድረስ
በዚህ ተቀመጡ" አላቸው። ፴፯ጴጥሮስንና ሁለ
ቱን የዘብዴዎስን ልጆች ወሰደ፤ ያዝንና ይተ
ክዝም ጀመር። ፴፰ከዚህም በኋላ፥ "ነፍሴ እስከ
ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ተቀመጡ፤
ከእኔም ጋር ትጉ" አላቸው። ፴፱ከዚያም ጥቂት
ፈቀቅ አለና በግንባሩ ሰግዶ ጸለየ፤ እንዲህም
አለ፥ "አባቴ ሆይ፥ የሚቻልስ ከሆነ ይህች
ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን ፈቃድህ ይሁን
እንጂ የእኔ ፈቃድ አይደለም።" ፵ወደ ደቀ
መዛሙርቱም ሄደ፤ ተኝተውም አገኛቸው፤
ጴጥሮስንም እንዲህ አለው፥ "አንድ ሰዓት
እንኳ ከእኔ ጋር መትጋት እንዲህ ተሳናችሁን?
፵፩ወደ ፈተናም እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ፤
መንፈስ ይሻልና፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው።"
፵፪ዳግመኛም ሄዶ፥ ጸለየ፤ እንዲህም አለ፥
"አባቴ ሆይ ይህች ጽዋ ሳልጠጣት ከእኔ ልታ
ልፍ የማይቻል ከሆነ ፈቃድህ ይሁን።" ፵፫ዳግ
መኛም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመለሰ፤ ተኝተ
ውም አገኛቸው፤ ዐይኖቻቸው በእንቅልፍ ፈዝ
ዘው ነበርና። ፵፬ደግሞም ለሦስተኛ ጊዜ ትቶ
አቸው ሄደና ያንኑ ቃል ብቻ ደግሞ ጸለየ።
፵፭ዳግመኛም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሶ
እንዲህ አላቸው፥ "እንግዲህስ ተኙ፤ ዕረፉም፤

---

፳፮፥፳፫ መዝ. ፵፩፥፱። ፳፮፥፳፰ ዘፀ. ፳፬፥፰፤ ኤር. ፴፩፥፴፩-፴፬። ፳፮፥፴፩ ዘካ. ፲፫፥፯።
፳፮፥፴፪ ማቴ. ፳፰፥፲፮።

እነሆ ጊዜው ደረሰ፤ የሰውንም ልጅ በኀጢአተ
ኞች እጅ አሳልፈው ይሰጡታል። ፵፮ተነሡ እን
ሂድ፤ እነሆ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል።”

### ጌታችን ስለ መያዙ
(ማር. ፲፬፥፵፫-፶፤ ዮሐ. ፲፰፥፫-፲፪)

፵፯ይህንም ሲናገር፥ እነሆ፥ ከዐሥራ ሁለቱ
አንዱ ይሁዳ መጣ፤ ከእርሱም ጋር ከካህናት
አለቆችና ከሕዝብ ሽማግሌዎች ዘንድ ሾተልና
ጎመድ የያዙ ብዙ ሰዎች መጡ። ፵፰አሳልፎ
የሚሰጠውም፥ “የምስመው እርሱ ነው፤ እር
ሱን ያዙ” ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር።
፵፱ያንጊዜም ይሁዳ ወደ ጌታችን ኢየሱስ
ቀርቦ፥ “መምህር ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን”
አለና ሳመው። ፶ጌታችን ኢየሱስም፥ “ወዳጄ
ሆይ፥ ለምን ነገር መጣህ?” አለው፤ ያንጊ
ዜም ቀረቡ፤ እጃቸውንም አንሥተው ጌታችን
ኢየሱስን ያዙት። ፶፩እነሆም፥ ከጌታችን ከኢ
የሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ እጁን ዘርግቶ ሰይ
ፉን መዘዘና፤ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ መትቶ
ጆሮውን ቈረጠው። ፶፪ጌታችን ኢየሱስም እን
ዲህ አለው፥ “ሰይፍህን ወደ አፎቱ መልስ፤
ሰይፍን የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይሞታሉና።
፶፫ወይስ ከዐሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላ
እክትን አሁን ይልክልኝ ዘንድ አባቴን ልማል
ደው የማልችል ይመስልሃልን? ፶፬እንዲህ ከሆ
ነስ፦ ይህ ሊሆን ይገባል የሚለው የመጽሐፍ
ቃል እንዴት ይፈጸማል?” ፶፭ጌታችን ኢየሱ
ስም ያንጊዜ ሕዝቡን እንዲህ አላቸው፥ “እንደ
ሌባ በሾተልና በጎመድ ልትይዙኝ መጣችሁን?
በመቅደስ ዘወትር ሳስተምር ከእናንተ ጋር
እኖር ነበር፤ አልያዛችሁኝምም። ፶፮ነገር ግን
ይህ ሁሉ የሆነ የነቢያት መጻሕፍት ይፈጸሙ
ዘንድ ነው፤” ከዚህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ
ሁሉ ትተውት ሸሹ።

፶፯ጌታችን ኢየሱስን የያዙትም ጻፎችና ሽማ
ግሌዎች ወደ ተሰበሰቡበት ወደ ካህናቱ አለቃ
ወደ ቀያፋ ወሰዱት። ፶፰ጴጥሮስም እስከ ሊቀ
ካህናቱ ግቢ ድረስ ከሩቅ ተከተለው፤ ወደ ውስ
ጥም ገብቶ የነገሩን መጨረሻ ያይ ዘንድ ከሎሌ
ዎቹ ጋር ተቀመጠ። ፶፱የካህናት አለቆችና ሽማ
ግሌዎች፥ ሸንጎውም ሁሉ ጌታችን ኢየሱስን
ሊገድሉት የሐሰት ምስክሮች ይፈልጉ ነበር፤
ነገር ግን አላገኙም።

### ጌታችን ኢየሱስ በሊቀ ካህናቱ ፊት እንደ ቆመ

፷ብዙዎች የሐሰት ምስክሮችም መጡና አላገ
ኙበትም፤ በኋላም ሁለቱ መጥተው፦ ፷፩“ይህ
ሰው የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ላፈርሰው፥
በሦስተኛውም ቀን ልሠራው እችላለሁ ብሏል”
አሉ። ፷፪ሊቀ ካህናቱም ተነሥቶ፥ “እነዚህ
በሚመሰክሩብህ አንድ ስንኳ አትመልስምን?”
አለው። ፷፫ጌታችን ኢየሱስ ግን ዝም አለ፤
ሊቀ ካህናቱም፥ “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ
ክርስቶስ እንደ ሆንህ ትነግረኝ ዘንድ በሕያው
እግዚአብሔር አምልሃለሁ” አለው። ፷፬ጌታችን
ኢየሱስም፥ “አንተ አልህ፤ ነገር ግን እላችኋ
ለሁ ከእንግዲህ ወዲህ የሰውን ልጅ በኀይል
ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይ ደመናም ሲመጣ ታዩታ
ላችሁ” አለው። ፷፭ያንጊዜም ሊቀ ካህናቱ ልብ
ሱን ቀደደ፤ “እነሆ ተሳደበ፤ ከእንግዲህ ወዲህ
ምን ምስክር ትሹለታላችሁ? እነሆ፥ አሁን
ስድቡን ሰምታችኋል፤ እንግዲህ ምን ትላላ
ችሁ?” አለ። ፷፮እነርሱም መልሰው፥ “ሞት
ይገባዋል” አሉ። ፷፯ከዚህም በኋላ በፊቱ ላይ
ተፉበት፤ ራሱንም በዘንግ መቱት፤ ፊቱንም
በጥፊ መቱት፤ እንዲህ እያሉ፦ ፷፰“ክርስቶስ
ሆይ፥ ንገረን፤ በጥፊ የመታህ ማን ነው?”

### ጴጥሮስ ስለ መካዱና ስለ መመለሱ
(ማር. ፲፬፥፷፮-፸፪፤ ሉቃ. ፳፪፥፶፭-፷፪)

፷፱ጴጥሮስ ግን ከቤት ውጭ በግቢው ተቀ
ምጦ ነበር፤ አንዲት ብላቴናም ወደ እርሱ
መጥታ፥ “አንተም እኮ ከገሊላዊው ከኢየሱስ
ጋር ነበርህ” አለችው። ፸እርሱም፥ “የምትይ
ዉን አላውቀዉም” ብሎ በሁሉም ፊት ካደ።
፸፩ወደ በርም በወጣ ጊዜ ሌላዪቱ አየችውና
ከዚያ ለቆሙት፥ “ይህም እኮ ከናዝሬቱ ኢየ
ሱስ ጋር ነበር” አለቻቸው። ፸፪ዳግመኛም
ካደ፤ ያን ሰውም እንደማያውቀው ማለ። ፸፫ከጥ
ቂት ጊዜም በኋላ ቆመው የነበሩ መጡና ጴጥሮ
ስን፥ “በእውነት አንተም ከእነርሱ ወገን ነህ፤
አነጋገርህም ያስታውቅብሃል” አሉት። ፸፬ያን
ጊዜም ያን ሰው እንደማያውቀው ይምልና ይረ
ገም ጀመር፤ ወዲያውኑም ዶሮ ጮኸ። ፸፭ጴጥ
ሮስም “ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ”
ያለውን የጌታችን የኢየሱስን ቃል አሰበ፤ ወደ
ውጭም ወጥቶ መራራ ልቅሶን አለቀሰ።

---

፳፮፥፶፭ ሉቃ. ፲፱፥፵፯፤ ፳፩፥፴፯። ፳፮፥፷፩ ዮሐ. ፪፥፲፱። ፳፮፥፷፬ ዳን. ፯፥፲፫።
፳፮፥፷፮-፷፯ ዘሌ. ፳፬፥፲፮።

## ምዕራፍ ፳፯

### ጌታችን ለጲላጦስ ተላልፎ ስለ መሰጠቱ

(ማር. ፲፭፥፩፤ ሉቃ. ፳፫፥፩-፪)

፩በነጋም ጊዜ የካህናት አለቆችና የሕዝቡ
ሽማግሌዎች ሁሉ ጌታችን ኢየሱስን ሊገድሉት
ተማከሩ። ፪አስረውም ወሰዱት፤ ለገዢው ለጰን
ጤናዊው ጲላጦስም አሳልፈው ሰጡት።

### ስለ ይሁዳ የሕይወት ፍጻሜ

(ሐ.ሥ. ፩፥፲፰፡፲፱)

፫ከዚህም በኋላ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደ
ፈረዱበት ባየ ጊዜ "ንጹሕ ደምን አሳልፌ የሰ
ጠሁ እኔ በድያለሁ" ብሎ ለካህናት አለቆችና
ለሕዝቡ ሽማግሌዎች ሠላሳውን ብር መለሰ።
፬እነርሱ ግን፥ "እኛ ምን አግዶን አንተ ለራ
ስህ ዕወቅ" አሉት። ፭ያንም ብር በቤተ መቅ
ደስ በትኖ ሄደና ታነቀ። ፮የካህናት አለቆችም
ያን ብር አንሥተው "የደም ዋጋ ነውና በመባ
ውስጥ ልንጨምረው አይገባንም" አሉ። ፯ተማ
ክረውም ለእንግዳ መቃብር የሸክላ ሠሪ መሬት
ገዙበት። ፰ስለዚህም ያ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ
"የደም መሬት" ተብሎ ተጠራ። ፱ያንጊዜ የነ
ቢዩ የኤርምያስ ቃል "የእስራኤል ልጆች የተ
ስማሙበትን የክቡርን ዋጋ ሠላሳውን ብር
ወሰዱ፤ ፲እግዚአብሔር እንደ አዘዘኝም ለሸክላ
ሠሪ እርሻ ሰጡት" ያለው ተፈጸመ።

### ጌታችን ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት እንደ ቆመ

(ማር. ፲፭፥፪-፭፤ ሉቃ. ፳፫፥፫-፭)

፲፩ጌታችን ኢየሱስም በመስፍኑ ፊት ቆመ፤
መስፍኑም፥ "የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን?"
ብሎ ጠየቀው፤ ጌታችን ኢየሱስም፥ "አንተ
አልህ" አለው። ፲፪የካህናት አለቆችና የሕዝቡም
ሽማግሌዎች ሲከስሱት ምንም የሰጠው መልስ
የለም። ፲፫ከዚህም በኋላ፤ ጲላጦስ፥ "ይህን
ያህል ሲመሰክሩብህ አትሰማምን?" አለው።
፲፬መስፍኑ እጅግ እስኪያደንቅ ድረስ አንዲት
ቃል ስንኳ አልመለሰለትም። ፲፭በዚያም በዓል
ለሕዝቡ ከእስረኞች መካከል አንዱን የወደዱ
ትን እንዲፈታላቸው ለመስፍኑ ልማድ ነበረው።
፲፮ያንጊዜም በጣም የታወቀ ስሙ በርባን የሚ
ባል አንድ እስረኛ ነበር። ፲፯እነርሱም ተሰብስ
በው ሳሉ ጲላጦስ ሕዝቡን፥ "ማንን እንድፈ
ታላችሁ ትፈልጋላችሁ? በርባንን? ወይስ ክር
ስቶስ የሚሉት ኢየሱስን?" አላቸው። ፲፰በቅን
ዐት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።

### በመከራው ጊዜ ስለ ሆነው ምስክርነት

፲፱ጲላጦስም በአደባባይ ተቀምጦ ሳለ፥
"በዚህ ጻድቅ ሰው ላይ እንዳትበድል ዕወቅ፤
ዛሬ በዚች ሌሊት በሕልሜ ስለ እርሱ ብዙ
ተሠቃይቻለሁና" ስትል ሚስቱ ላከችበት።
፳የካህናት አለቆችና ሽማግሌዎች ግን በርባንን
እንዲፈታላቸው፥ ኢየሱስን ግን እንዲገድሉ
ሕዝቡን አባብለው እሺ አሰኙአቸው፤ ፳፩መስፍ
ኑም መልሶ፥ "ከሁለቱ ማንኛውን ልፈታላችሁ
ትወዳላችሁ?" አላቸው፤ እነርሱም፥ "በርባ
ንን" አሉ። ፳፪ጲላጦስም፥ "እንግዲህ ክርስቶስ
የተባለውን ኢየሱስን ምን ላድርገው?" አላ
ቸው፤ ሁሉም፥ "ስቀለው!" አሉ። ፳፫መስፍ
ኑም፥ "ምን ክፉ ሥራ ሠራ?" አላቸው፤ እነ
ርሱ ግን "ስቀለው! ስቀለው!" እያሉ ጩኸት
አበዙ። ፳፬ከዚህም በኋላ ጲላጦስ ሁከት ከሚ
በዛ በቀር የሚጠቅም ነገር እንደሌለ ባየ ጊዜ፥
ውኃ ወስዶ፥ "እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም
ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ለራሳችሁ ዕወቁ" ብሎ
በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ። ፳፭ሕዝቡም ሁሉ
መልሰው፥ "ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ
ይሁን" አሉ። ፳፮ከዚህም በኋላ በርባንን ፈታ
ላቸው፤ ጌታችን ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቅ
ሉት ሰጣቸው።

### ጭፍሮች በጌታ ኢየሱስ ላይ ስለ መዘባበታቸው

(ማር. ፲፭፥፲፮-፳፤ ዮሐ. ፲፱፥፪-፫)

፳፯ከዚህም በኋላ የመስፍኑ ጭፍሮች ጌታ
ችን ኢየሱስን ተቀብለው ወደ ፍርድ ሸንጎ ወሰ
ዱት፤ ጭፍራውንም ሁሉ ወደ እርሱ ሰበሰቡ።
፳፰ልብሱንም ገፍፈው ቀይ ልብስ አለበሱት።
፳፱የእሾህም አክሊል ጐንጕነው በራሱ ላይ አቀዳ
ጁት፤ በቀኝ እጁም ዘንግ አሲያዙት፤ በፊቱም
ተንበርክከው፥ "የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም
ለአንተ ይሁን" እያሉ ተዘባበቱበት፤ ፴በላዩም
ተፉበት፤ ዘንጉንም ነጥቀው ራሱን መቱት።
፴፩ከተዘባበቱበትም በኋላ፥ ቀዩን ልብስ ገፍፈው
ልብሱን አለበሱት፤ ሊሰቅሉትም ወሰዱት።
፴፪ሲወጡም ስምዖን የሚባል የቀሬና ሰው
አገኙ፤ መስቀሉንም ይሸከም ዘንድ አስገደ

፳፯፥፫-፰ ሐ.ሥ. ፩፥፲፰-፲፱። ፳፯፥፱-፲ ዘካ. ፲፩፥፲፪-፲፫። ፳፯፥፳፬ ዘዳ. ፳፩፥፮-፱።

ዱት። ፴፫ትርጓሜው የራስ ቅል ወደሚሆን ጎል
ጎታ ወደሚባል ቦታ በደረሱ ጊዜ፥ ፴፬ከሐሞት
ጋራ የተቀላቀለ ወይንን ሊጠጣ አቀረቡለት፤
ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም።

## ጌታችን ስለ መሰቀሉ
(ማር. ፲፭፥፳፩-፴፪፤ ዮሐ. ፲፱፥፲፯-፳፯)

፴፭በሰቀሉትም ጊዜ ዕጣ ተጣጥለው ልብሱን
ተካፈሉ፤ ይህም "ልብሶቼን ለራሳቸው ተካ
ፈሉ፤ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ" ያለው
የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው። ፴፮በዚ
ያም ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር። ፴፯በራሱ
ላይም "ይህ የአይሁድ ንጉሥ ኢየሱስ ነው"
የሚል የክሱን ጽሕፈት ጽፈው አኖሩ። ፴፰ያን
ጊዜም ሁለት ወንበዴዎችን አንዱን በቀኙ አን
ዱንም በግራው ከእርሱ ጋር ሰቀሉ። ፴፱የሚያል
ፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበር።
፵"ቤተ መቅደስን የምታፈርሰው፥ በሦስተኛ
ውም ቀን የምትሠራው አንተ ሆይ፥ ራስህን
አድን፤ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህስ እስኪ
ከመስቀልህ ውረድ" ይሉት ነበር። ፵፩እንዲ
ሁም የካህናት አለቆች ከጻፎችና ከሽማግሌዎች
ጋር እንዲህ እያሉ ይዘብቱበት ነበር፤ ፵፪"ሌላ
ውን ያድናል፤ ራሱን ማዳን ግን አይችልም፤
የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ አሁን ከመስቀል ይው
ረድና እንመንበት። ፵፫በእግዚአብሔርም ታም
ኗል፤ ይወደውም እንደ ሆነ እነሆ፥ አሁን ያድ
ነው፤ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሏልና።"
፵፬ከእርሱ ጋር የተሰቀሉ ወንበዴዎችም እንዲሁ
ያሽሙአጥጡት ነበር።

## ጌታችን በዕፀ መስቀል ላይ ስለ መሞቱ
(ማር. ፲፭፥፴፫-፵፩፤ ሉቃ. ፳፫፥፵፬-፵፱)

፵፭ከስድስት ሰዓት ጀምሮም እስከ ዘጠኝ
ሰዓት ዓለም ሁሉ ጨለማ ሆነ። ፵፮በዘጠኝ
ሰዓትም ጌታችን ኢየሱስ፥ "ኤሎሄ ኤሎሄ
ላማ ሰበቅታኒ?" ብሎ በታላቅ ቃል ጮኸ፤
ይኸውም፥ "አምላኬ አምላኬ ለምን ተው
ኸኝ?" ማለት ነው። ፵፯በዚያም ቆመው የነበ
ሩት በሰሙ ጊዜ፥ "ይህስ ኤልያስን ይጠራል"
አሉ። ፵፰ያንጊዜም ከእነርሱ አንዱ ሮጠና ሰፍ
ነግ ወሰደ፤ ሆምጣጤም ሞላበት፤ በዘንግም
አስሮ አጠጣው። ፵፱"ተዉ ኤልያስ መጥቶ
ያድነው እንደ ሆነ እንይ" የሚሉም ነበሩ።
፶ዳግመኛም ጌታችን ኢየሱስ በታላቅ ድምፅ
ጮኸ፤ ያንጊዜም ነፍሱ፩ ከሥጋው ተለየች።
፶፩እነሆም፥ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ
ታች ከሁለት ተቀደደ፤ ምድርም ተነዋወጠች፤
ዐለቶችም ተሰነጠቁ። ፶፪መቃብሮችም ተከፈቱ፤
ተኝተው ከነበሩ ከቅዱሳን በድኖችም ብዙዎች
ተነሡ። ፶፫ከመቃብራቸውም ወጡ፤ ከትንሣኤ
ውም በኋላ ወደ ቅድስት ከተማ ገብተው ለብ
ዙዎች ታዩአቸው። ፶፬የመቶ አለቃውና ከእ
ርሱ ጋር ጌታችን ኢየሱስን ይጠብቁ የነበሩት
ግን፤ ንውጽውጽታውንና የሆነውን ሁሉ አይ
ተው እጅግ ፈሩ፤ "በእውነትም ይህ የእግዚአ
ብሔር ልጅ ነው" አሉ። ፶፭የሆነውንም ሁሉ
ከሩቁ የሚመለከቱ ብዙ ሴቶች በዚያ ነበሩ፤
እነርሱም ከገሊላ ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስን የተ
ከተሉትና ያገለገሉት ነበሩ። ፶፮ከእነርሱም ማር
ያም መግደላዊት፥ የያዕቆብና የዮሳም እናት
ማርያም፥ የዘብዴዎስም የልጆቹ እናት ነበሩ።

## ጌታችን ወደ መቃብር ስለ መውረዱ
(ማር. ፲፭፥፵፪-፵፯፤ ዮሐ. ፲፱፥፴፰-፵፪)

፶፯በመሸም ጊዜ ስሙ ዮሴፍ የሚባል ባለ
ጸጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፤ እርሱም የጌታ
ችን የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበር። ፶፰እርሱም
ወደ ጲላጦስ ሄዶ የጌታችን የኢየሱስን ሥጋ
ለመነ፤ ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። ፶፱ዮሴ
ፍም የጌታችን የኢየሱስን ሥጋ ተቀብሎ በን
ጹሕ በፍታ ገነዘው። ፷ለራሱ ከዐለት በአስፈ
ለፈለው በሐዲስ መቃብርም ቀበረው፤ ታላቅ
ድንጋይም አንከባሎ የመቃብሩን አፍ ገጥሞ
ሄደ። ፷፩ከዚያም ማርያም መግደላዊትና ሁለ
ተኛዋ ማርያም በመቃብሩ ፊት ለፊት ተቀ
ምጠው ነበር። ፷፪ከዐርብም በኋላ በማግሥቱ
የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ወደ ጲላጦስ
ተሰበሰቡ። ፷፫እነርሱም እንዲህ አሉት፥ "ጌታ
ሆይ፥ ያ መስሐቲ በሕይወቱ ሳለ፥ 'በሦስተ
ኛው ቀን እነሣለሁ' ያለውን አሰብን። ፷፬እንግ
ዲህ ደቀ መዛሙርቱ ሌሊት መጥተው እንዳ

፩ "ነፍሱን ሰጠ" የሚልም ዘርዕ አለ።

፳፯፥፴፬ መዝ. ፷፰፥፳፩። ፳፯፥፴፭ መዝ. ፳፩፥፲፰። ፳፯፥፴፱ መዝ. ፳፩፥፯፤ ፻፰፥፳፭።
፳፯፥፵ ማቴ. ፳፮፥፷፩፤ ዮሐ. ፪፥፲፱። ፳፯፥፵፫ መዝ. ፳፩፥፰። ፳፯፥፵፮ መዝ. ፳፩፥፩።
፳፯፥፵፰ መዝ. ፷፰፥፳፩። ፳፯፥፶፩ ዘፀ. ፳፮፥፴፩-፴፫። ፳፯፥፶፮ ሉቃ. ፰፥፪-፫።
፳፯፥፷፫ ማቴ. ፲፮፥፳፩፤ ፲፯፥፳፫፤ ፳፥፲፱፤ ማር. ፰፥፴፩፤ ፱፥፴፩፤ ፲፥፴፫-፴፬፤ ሉቃ. ፱፥፳፪፤ ፲፰፥፴፩-፴፫።

ይሰርቁት ለሕዝቡም ከሙታን ተለይቶ ተነሣ
እንዳይሉ፥ እስከ ሦስት ቀን መቃብሩ እንዲ
ጠበቅ እዘዝ፤ የኋለኛዪቱ በደሉ ከፊተኛዪቱ
የምትከፋ ትሆናለችና።” ፷፭ጲላጦስም፥ “ጠባ
ቆች አሏችሁ፤[፪] ሄዳችሁም እንደምታውቁ አስ
ጠብቁ” አላቸው። ፷፮እነርሱም ሄደው ከጠባ
ቆች ጋር ድንጋዩን አትመው መቃብሩን አስ
ጠበቁ።

## ምዕራፍ ፳፰

### ጌታችን ስለ መነሣቱ

፩በሰንበትም ማታ ለእሑድ አጥቢያ ማር
ያም መግደላዊትና ሁለተኛዋ ማርያም መቃ
ብሩን ሊያዩ መጡ። ፪እነሆ፥ ታላቅ የምድር
መናወጥ ሆነ፤ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰ
ማይ ወርዶአልና፤ ቀርቦም በመቃብሩ አፍ
ላይ ድንጋይዋን አንከባሎ በላይዋ ተቀመጠ።
፫መልኩም እንደ መብረቅ፥ ልብሱም እንደ
በረዶ ነጭ ነበረ። ፬እርሱንም ከመፍራት የተ
ነሣ መቃብሩን የሚጠብቁ ታወኩ፤ እንደ በድ
ንም ሆኑ። ፭መልአኩም መልሶ ሴቶችን እን
ዲህ አላቸው፤ “እናንተስ አትፍሩ፤ የተሰ
ቀለውን ኢየሱስን እንደምትሹ አውቃለሁና።
፮በዚህ የለም፤ እርሱ እንደ ተናገረው ተነ
ሥቶአል፤ ነገር ግን ኑና ተቀብሮበት የነበረ
ውን ቦታ እዩ። ፯ፈጥናችሁም ሂዱና፡- ከሙ
ታን ተለይቶ ተነሣ፤ እነሆ፥ ወደ ገሊላ ይቀ
ድማችኋል፤ በዚያም ታዩታላችሁ፤ ብላችሁ
ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው፤ እነሆም፥ ነገር
ኋችሁ።” ፰በፍርሀትና በታላቅ ደስታም ከመ
ቃብሩ ፈጥነው ሄዱ፤ ለደቀ መዛሙርቱም
ይነግሩአቸው ዘንድ ሮጡ። ፱እነሆም፥ ጌታ
ችን ኢየሱስ አገኛቸውና፥ “ሰላም ለእናንተ
ይሁን” አላቸው፤ እነርሱም ቀርበው እግሩን
ይዘው ሰገዱለት። ፲ከዚህም በኋላ ጌታችን ኢየ
ሱስ እንዲህ አላቸው፥ “አትፍሩ ሂዱና ወደ
ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ንገሩአቸው፤ በዚ
ያም ያዩኛል።”
፲፩እነርሱም ከሄዱ በኋላ ጠባቆች ወደ ከተማ
ገብተው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች ነገሩ።
፲፪ተሰብስበውም ከሽማግሌዎች ጋር መክረው
ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጡአቸው። ፲፫እንዲ
ህም አሏቸው፥ “ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙ
ርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ። ፲፬ይህም
ነገር በገገርው ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ እኛ እና
ሳምነዋለን፤ እናንተንም ያለ ሥጋት እንድትኖሩ
እናደርጋለን።” ፲፭ጭፍሮችም ገንዘቡን ተቀብ
ለው እንደ አስተማሩአቸው አደረጉ፤ ይህም
ነገር እስከ ዛሬ ድረስ በአይሁድ ዘንድ ሲነ
ገር ይኖራል።
፲፮ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ጌታ
ችን ኢየሱስ ወደ አዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ
ሄዱ። ፲፯ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ እኩሌቶቹ[፩]
ግን ተጠራጠሩ። ፲፰ጌታችን ኢየሱስም ቀርቦ፡-
እንዲህ ሲል ተናገራቸው፥ “ሥልጣን ሁሉ
በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። ፲፱እንግዲህ ሂዱና
በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመ
ቃችኋቸው አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ። ፳ያዘዝኋ
ችሁንም እንዲጠብቁ አስተምሩአቸው፤ እኔም
እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር
እኖራለሁ።”

ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ሐዋርያ ማቴ
ዎስ በምድረ ፍልስጥኤም በዕብራይስጥ ቋንቋ
የጻፈው ወንጌል ተፈጸመ፤ መንፈስ ቅዱስ እያ
ተጋው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ወደ
ሰማይ ካረገ በኋላ በስምንተኛው ዓመት፤ ቀላ
ውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያዉ ዓመት
ጻፈው።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። አሜን።

[፪] ግእዙ “ንሥኡ ሰገራተ ...” ይላል።
[፩] ግሪኩ “... አንዳንዶቹ ግን ...” ይላል።
፳፰፥፩-፲፰ ማር. ፲፮፥፩-፲፤ ሉቃ. ፳፬፥፩-፲፪፤ ዮሐ. ፳፥፩-፲። ፳፰፥፲፮ ማቴ. ፳፮፥፴፪፤ ማር. ፲፬፥፳፰።
፳፰፥፲፱ ሐ.ሥ. ፩፥፰።